እንኖር ነበር። አሁን ደግሞ ድል አድራጊውን የጣልያንን ባንዲራ ተጠግተን... እንኖራለን እንጂ፣... በአባቶቻችን ሲያያዝ ያልመጣውን አዲስ ነገር አንቀበልም..." አለው። ሌላውም የጠላትን ስብከት ከቁም ነገር ሳይቆጥር ትግሉን ቀጠለ።

አርሶ በሌው፣ የቀንበር በሬውን እየሸጠ ጠመንጃና ጥይት ገዛ። ጣልያን ይህንን ሲሰማ መሣሪያ ያለህ አግባ ብሎ አዘዘ። ገበሬውም አሮጌ ስናድር፣ ውጅግራና ናስማስር ከሦስትና ከአምስት ጥይት ጋር አስረከበ። ጭስ የጠገበ ,ጋሻና ጐራዴ አገባ። ጣልያንም አንጀቱ እያረረ ተቀበለ። ደረቅ ብረት አግቡ ቢል፣ ገበሬ የለንም ብሎ ጠቀጠቀ።

የአርበኞች እንቅስቃሴ እየበረታ፣ የሕዝቡ ልብ ከእሱ እየራቀ እንደሄደ ገባው። የዚህን ጊዜ ወደ ኃይል ሥራ ዞረ። ለመዘርዘር የሚያስቸግር ብዙ የግፍ ሥራ አካሄደ። ሕዝብ እየሰበሰበ በመትረየስ መረሸን፣ እግርን ወደላይ ራስን ወደታች እያደረጉ እየዘቀዘቁ መስቀል፣ ቤተክርስቲያንና የሕዝብ መኖሪያ ቤቶችን ማቃጠል፣ ምስጢር ታውቃለህ በሚል ሰበብ ሰውን በዱላ እየደበደቡ፣ በጅራፍ እየገረፉ መግደል የዘወትር ሥራ ሆነ።

አርበኛውም በበኩሉ ግድያውን አጧጧፈ። አቶ ተፈሪ በላይ ከጐንደር ወደ ስቲት የሚጓዝ ካሚዮን ሰብሮ፣ በውስጡ የነበሩትን ወታደሮች ገድሎ፣ መሣሪያቸውን ማረከ። መምሬ ጌጡ የተባሉ ቄስ የታሠሩበትን ፈትተው ስቲት መንገድ ላይ ሁለት አልቤን ጠመንጃ ነጠቁ። አቶ እሸቴ እውነቱ ከብዙ ወርቅና ብር ይልቅ አሥር ጠመንጃ መርጦ ከጐንደር ግምጃ ቤት ዘርፎ ወጣ። አቶ ተሰማ ድንገት ቆማ በሚባለው ሀገር በዱላ አምስት ጠመንጀ ማረከ፤ አቶ በየነ እምሬ ከፋርጣ ጦርነት ላይ በዱላ ጠመንጀ ማረከ። አቶ ብርሃኑ አብተው በካራ ጀምሮ ከአምስት የጦር ሜዳ ስምንት ጠመንጃ ማረከ። የወንድነት ትርጉም ነጭ መግደል፣ ጠመንጃ መማረክ ሆነ። በእያንዳንዱ ግዳይና ምርኮ የሚካሄደው ፉከራ አስገራሚ ሆነ።

በሐምሌ ወር 1928 ዓ.ም በግራዝማች /ራስ/ ውብነህ ተሰማ የሚመራው አርበኛ ካቶ ማውራ ላይ ገጥሞ ሁለት ቀን ሙሉ ወጋው። ብዙ ወታደርም ገደለበት። የጣልያን ወታደርም ወደ መጣበት ምሽግ ተመለሰ። በዛ፣ ከጠላት እንጂ ከወገን ማንም አልሞተም።

ካህናት የትግሉ ተካፋይ ሆኑ። አባ ገብረ ማርያም የተባሉት የወልቃይት መነኩሴ አራቱን ማዕዘን ባርከው፣ ሰው ለጠላት እንዳይገዛ ገዝተው፣ ግንባራቸውን ለመትረየሱ ሰጥተው በመትረየስ ተደብድበው ሞቱ። አድገርትያ ማርያም፣ ክሣደ ማርያም፣ ምድረ ወይዘሮ ሚካኤል የተባሉት ሦስት ቤተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ በዚያ የነበሩ 55 ክርስቲያኖች እየተገደሉ ከሚነደው እሳት ተጣሉ።

የማህበረ ሥላሴ ጉዳይ ለየት ያለ ስለሆነ በጥልቀት ሊታይ ይገባል። ሁለት የጣልያን አይሮፕላኖች በገዳሙ አካባቢ እየበረሩ ሲቃኙ የነካቸው



ሳይታወቅ ተሰናክለው ወደቁ። የወደቁትም አንዱ ማርዘነብ፣ ሌላው ደግሞ ጉንደዋ ከተባሉት ቦታዎች ነበር። ከአንዱ ውስጥ የነበሩት ሲያልቁ፣ በሁለተኛው የነበሩት ሦስት ሰዎች ስለዳኑ በዚያ የነበሩ መነኮስት ረድተውና ሸኚ ሰጥተው ወደ ጐንደር ላኩአቸው። ጠላት በዚህ ተደስቶ ዱቄትና ስኳር ላከላቸው። እነሱ ግን አንቀበልም ብለው መለሱ። ጣልያን በዚህ ቂም ይዞ፣ ከገዳሙ ገብቶ በየመካነ ፀሎታቸው እየዞረ 22 መናንያት በጥይት ገደለ። ከዚህም በስተቀር ቤተክርስቲያኑን ባቃጠለ ጊዜ ሁለት መነኮሳት በፈቃዳቸው አብረው ተቃጥለዋል።

የአርበኞችን እንቅስቃሴ በእንጭጩ ለመቅጨት የጠላት ጦር በየቦታው ተፍጨረጨረ። አርበኛውም እንደ አመጣጡ ይቋቋመው ጀመር። ነሐሴ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጥናፋ ከተባለው ቦታ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ከጥዋቱ 5 ሰዓት እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ቀጥ አድርጐ ወጋው። ጣልያንም ተመልሶ ደብረ ታቦር ገባ። በዚህ ቀን በተደረገው ጦርነት ሼህ አሊ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማርኮ ነበር። ነገር ግን እሱ መሆኑ ባለመታወቁ ተለቀቀ። ቢሆንም ተሰቀጠጠ።[4]

ጳጉሜ 4 ቀን 1928 ዓ.ም በልጅ አያናያ የሚመሩ አርበኞች ጫንቃ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠሙት። ሠላሳ ሁለት የጠላት ወታደር በመግደልና መሣሪያ በመማረክ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠሩ። ከእነሱ ግን እንኳን የሞተ የቆሰለም አልነበረም።

የ1928 ዓ.ም የጐንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። ከተነገሩት ቃላት፣ ከተካሄዱት ተግባራት የጐንደር ሕዝብ ግንዛቤ አገኘ። ያገኘውም ግንዛቤ የጣልያን ዓላማ፡-

1ኛ. ሀገሪቱን ለትውልደ ትውልድ የቅኝ ግዛት ማድረግ፣
2ኛ. ቤተክርስቲያናትን ማቃጠል፣ ካህናቱን መፍጀትና እምነቱን ማርከስ፣
3ኛ. ሕዝቡን መጨረስ፣
4ኛ. አንድነቱን አጥፍቶ እርስበርሱ ማፋጀት፣
5ኛ. በመሬቱ ላይ የእራሱን ሕዝብ ማስፈር፣

መሆኑን፣ ሰው በነገረው ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ከራሳቸው ተረዳ፤ ከተግባራቸው አየ፤ ከቃላቸው ሰማ።

የ1929 ዓ.ም ትግል ከ1928 ዓ.ምቱ የበረታ ሆነ።

በመስከረም ወር 1929 ዓ.ም ሻለቃ ካሶሎኒ በተባለ መኰንን የሚታዘዝ ወታደር ወደ ደዋ ዘመተ። አርበኛውም ደንጐራ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ደህና ውጊያ ከተካሄደ በኋላ ጣልያን አሸነፈ። የአርበኞቹ መሪ አቶ ከሆና ነጋሽ ከሦስት ባልደረቦቹ ጋር ተማረከ። አሥር አርበኞች ሞቱ። ጣልያን ምርኮኞቹን ወደ ጭልጋ ወስዶ ብዙ ሥቃይ ከፈፀመባቸው በኋላ አይከል ላይ ሰቀላቸው። ነገር ግን በዚህ አደራረጉ የተናደደ አቶ ከፍአለ ብሩ

የተባለ፣ ከአደባባይ ላይ የነበረ ሰላማዊ ሰው፣ ከተሰለፉት የጠላት ወታደሮች ጠመንጃ ነጠቆ፣ 6 ወታደር ገድሎ በማምለጥ አርበኝነት ገባ።

በልጅ ብሬ ዘገየ የሚመሩት አርበኞች ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሣንጃ ከተባለው ቦታ የነበረውን ምሽግ አጠቁ። ከጠዋቱ በ1 ሰዓት ጀምረው ሲዋጉ ውለው፣ በ9 ሰዓት በጨበጣ ጦርነት ምሽጉን ሰብረው ገቡ። ብዙ የጠላት ወታደር ገደሉ፤ ሁለት ሹማምንት ማረኩ፤ የቀረው ሸሽቶ አመለጣቸው። እጅግ ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ የእጅ በምብ ስለተገኘ፣ ሴት ወንዱ ከአባባቢው ወጥቶ ለቀመው። መሣሪያው ለአርበኝነት ሥራ ጠቀመ። ከአርበኞች ወገን አምስት ሰዎች በጀግንነት ወደቁ፤ ጥቂቶቹም ቆሰሉ። ድጋሚ ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ሲፍላ ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት ተደርጐ፣ ድል የአርበኞች ሆነ። ብዙ የጠላት ወታደርና አምስት አርበኞች ሞቱ።

የሣንጃ ምሽግ መስበር የጠላትን ክብር ነካ። በአማራ አገር ገዥ ልዩ ትዕዛዝ 1500 ወታደር ዘመተ። አርበኛው ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም ደብረ ሲና ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ሲዋጋ ከሞተው ይልቅ ሲሸሽ ሰሃራ ከሚባለው ገደል ዓይኑ እያየ ገብቶ ያለቀው ሳይበልጥ አልቀረም። አቶ አዛገ አበራ፣ መቶ አለቃ ድፋስዩ የተባለውን የጦር አዛዥ መትረየስ ከሚተኩስበት ላይ ደርሶበት ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው ከመሬት ወደቁ። አንዳቸውም ረዳት ሳያገኙ አዛገ አበራ ነጭ ገዳይ ብሎ ተነሳ። ሃያ ሦስት አርበኞች በጦሩ ሜዳ ሞቱ፤ ሌሎችም ቆሰሉ። ድል ግን የአርበኛ ሆነ። በዚህ ጦርነት አንድ ማርተጋሻ ልጅ፣ አንድ መቶ አለቃ ስለገደለ ጓደኞቹ ሁሉ ለዚሁ ዓይነት ሥራ ተነሳሱ።

የአርበኞች ኃይል የማይበገርለት ሲሆን፣ ጣልያን ከሸሬ ሌላ ጦር አመጣ። የዚህ አዲስ የመጣው የጦር ሥልት ከአርበኛው ሥልት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ጦርነቱ ከባድ ሆነ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ከአርበኞች ወገን ዋና ዋናዎቹ 17 ነበሩ። ከእልቂት የተረፈው የጠላት ጦር በአዝማቹ በደጃዝማች ፀሐይ መሪነት ጐንደር ገባ። አርበኞች ብዙ መሣሪየ ማረኩ። ሴት ወንዱ ወጥቶ ስምንት ቀን ሙሉ ከዱር ከገደል መሣሪየ ለቀመ።

በሌላው የጦር ግንባር ደግሞ በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ በጥቅምትና ታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ግልቢና፣ አጥገባ እና ማጀ፣ እንደዚሁም ሎዋሪ ከተባሉት ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ ከጠላት ጋር ጦርነት አድርጐ መልካም ሥራ ሠራ። ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ ፊታውራሪ ደሴ ዘለቀ የተባለውን የባንዶች መሪ ጭምር ማረከ።

ጣልያን በጐንዳ መረባ አካባቢ የነበሩትን አርበኞች ለማጥፋት በአንድ በኩል የሚመራ ጦር አንቀሳቀሰ። በልጅ አንዳርጌ ደስታ የሚመራው ጦር ቀደም ብሎ ሰባ ስምንት ሰው በሰቀለበት በአስተርእዮ ሜዳ ላይ ገጠመው።



ጣልያን አፈግፍጐ ጭንጫየ ከተባለው ኮረብታ ላይ ወጣ። አዲስ ጦር በማስመጣት ከበባውን ሰብሮ ወጣ።

ሕዝብ መሣሪያ አላገባ ስለአለ፣ መሣሪያ በግድ የመረከብ ጥያቄ ለጠላት አንገብጋቢ ሆነ። ስለዚህ ጣልያን ብዙ ወታደር ይዞ ከጐንደር ወደ ውዶ ወረደ። ፊታውራሪ አየለ ቁንጬ ህዳር 15 ቀን 1929 ዓ.ም ብቻ፣ ለብቻ ገጠመው በያዙት መውዜር ብዙ ወታደር ገደሉበት። በመጨረሻው እሳቸው ራሳቸው ተመቱ። ሕዝቡ በጽዮን ማርያም ደብቆ ሲያስታምማቸው፣ ጠላት ዓለሙ ይመር በተባለ ሰላይ አማካይነት አግኝቶ ወደ ደብረ ታቦር ወሰዳቸው። እሳቸውም "ይህ ዛሬ በእኔ የደረሰው ነገ በእያንዳንድህ ሳይደርስብህ አይቀርም" ብለው ሕዝቡን በማስጠንቀቅ ከእሥር ቤት ገቡ። ከዚያም በማግሥቱ የተዘጋጀውን ገመድ እሳቸው ራሳቸው፣ በእጃቸው ከአንገታቸው በማጥለቅ ሰማዕትነትን ተቀበሉ።

ጣልያን በአርማጭሆና በጠገዴ ያሉ አርበኞችን ለመደምሰስ ብዛት ያለው ጦር አንቀሳቀሰ። አርበኛውም ህይወቱን ለሀገሩ ለመስጠት ተማማለ። ታህሣሥ 5 ቀን 1929 ዓ.ም ግመኛ ከተባለው ቦታ ገጠመው። አገሬውም ተባብሮ የመጣበትን ጠላት አባረረው። ብዙ የጠላት ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም ወገን ከሁለት የጦር መሪዎች ጋር ብዙ ሰው ሞተ። ቢሆንም ከጥፋት ዳነ። ይህንን ሥራ የሠራውን አርበኛ ለማጥፋት፣ ጠላት በዚሁ በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። ጦሩ ከዳባት ተነስቶ ለእነሱ አመች ከሆነ፣ እልም ከአለው የአዴት ጫካ ውስጥ ሲገባ፣ አርበኞች ሥራቸውን ጀመሩ። ብዙ የጠላት ወታደር ገደሉ። የጦር አዛዥ ሆኖ የመጣው ሻምበል በባለምዋሉ በቀኛዝማች ተስፋዬ መደባይ አማካኝነት እጁን ለመስጠት ጠየቀ። የአርበኞቹ መሪ ልጅ ዳኘው ተፈሪ መሣሪያውን ከአስረከባቸው ምህረት አድርገው እስከ ዳባት ድረስ በሸኚ እንደሚልኩት ቃል ገቡለት። ሻምበሉ ወታደሮቹን በሙሉ አሳልፎ አርበኛው በተቀመጠበት አደባባይ በሰልፍ የክብር ሰላምታ እየሰጠ አልፎ የጦር መሣሪያውንና ተጥቁን አስረከበ። እሳቸውም ቃላቸውን ጠብቀው ሸኚ ሰጥተው በሰላም ዳባት እንዲገባ አደረጉ። መሣሪያውን ለሕዝብ አደሉ።

የሻምበሉን መከበብ የሰማው የወልቃይቱ ጦር አዛዥ፣ አለቃ ግራመሽ ለእርዳታ ቀደም ብሎ ተንቀሳቀሶ ነበር፤ ግን የእጅ መስጠቱ ሥራ ከተከናወነ በኂላ ደረሰ። የአዴት አርበኛ አዲስ በተረከበው ምንሽር እሱኑ ጠዘጠዘው። ሻለቃ ግራምሽ ሁኔታውን ሲረዳ ሸሽቱን ቀጠለ። ልጅ ዳኘው ወኔ ተቀስቅሶባቸው ጠላትን እያባረሩ ከዳባት ምሽግ ገቡ። ዋናውን ለመጣል ባደረጉት ሙከራ እጅ ለእጅ ተያይዘው ትንቅንቅ ገጠሙት። በኂላ ግን ብዙዎች ሆነው ታግለው ጥለው ገደሉአቸው። ከእሳቸው ጋር ሌሎች ሦስት ታዋቂ አርበኞች አብረዋቸው ወደቁ። ልጅ ዳኘው በእልህ፣ ዝግጅት

ባልተደረገበት ሁኔታ ከምሽግ መግባታቸው፣ በዚህ ዓይነት ደግ ሳይወጣው ቀረ።

ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች ቋራ ጋውላ ከተባለው ቦታ ጦርነት አድርገው አሥራ አምስት የጠላት ወታደር ገደሉ። መሣሪያም ማረኩ። ጥር 12 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ መተማ በሚወስደው መንገድ ማብሰጌ በነበረው ምሽግ ላይ የጭልጋ አርበኞች አደጋ ጥለው ከንጋት እስከ ስድስት ሰዓት ተዋግተው ብዙ ወታደር ገድለው ሠላሳ ጠመንጃ ማረኩ። ከእነሱም ብዙ ሰው ሞተ፤ ብዙም ደግሞ ቆሰለ።

ከልጅ ዳኘው ጦርነት ሸሽቶ ያመለጠውን አንድ ክፍል በቀኛዝማች /ቢትወደድ/ አዳነ መኰንን የሚመራው የጠገዴ አርበኛ ተቀብሎ እያጣደፈ ታህሣሥ 12 ቀን 1929 ዓ.ም መሥፈንቶ ላይ ከነበረው የጦር ሠፈር ከተተው። ከዚያም ከብቦ መከራውን ስለአሳየው አዛገፉ በባለምዋሉ በቀኛዝማች ጉላ አማላጅነት መሣሪያውን ለአርበኞች አስረክቦ ወልቃይትን ለቅቆ ቀብትያ ገባ። ጣልያን ለአርበኞች ያስረከበው ስምንት መቶ ጠመንጃ ቁጥሩ ካልታወቀ ጥይት ጋር፣ እንደዚሁም አንድ መቶ ዳውላ እህል ነበር። ጠገዴ ነፃ ሆኖ በቀኛዝማች /ቢትወደድ/ አዳነ አስተዳዳሪነት ይመራ ጀመር። ወልቃይትና ጠገዴንም ነፃ ለማውጣት ብዙ አስተዋጽኦ አደረገ።

መሣሪያውን ለልጅ ዳኛቸው አስረክቦ የተመለሰው የጣልያን ጦር ጐንደር ሲገባ በጦር ወንጀለኝነት ተከሰሰ። ቄሱ "...እንድትዋጉ ተልካችሁ መሣሪያችሁን አስረክባችሁ ከመጣችሁ በነፍሳችሁ ትቀጣላችሁ..." የሚል ሆነ። ሻምበሉ ጥፋቱን አምኖ ቅጣቱን ተከሳሾቹ የሚቀበሉት እሱ ከመራው የበለጠ ወታደርና መሣሪያ ያለው ጦር ተልኮ ከቦታው ደርሶ የኢጣልያን ባንዲራ የሰቀለ እንደሆነ ብቻ እንደሚሆን ገልፆ ተከራከረ። በዚህ የተነሣ አዲስ ከባድ ጦር እንዲዘምት ታዘዘ።

አርበኛው ምሥጢሩን ሰምቶ ነበርና ከዚህ ነው መሞት የሚገባን ብሎ ቆረጠ። በአካባቢው የነበረው አርበኛ በሙሉ ተሰበሰበና አዴት ላይ ደረት ለደረት ገጠመው። ጠላት በመድፍ፣ በብዙ ዓይነት መትረየስና ቁጥሩ በበዛ ወታደር ተዋጋ። አካባቢውን አዘውትሮ በአይሮፕላን አስደበደበ። አርበኛው አልተበገረም፤ አጥብቆ ተጋደለ። የገጠሙት በሰሜን፣ በምዕራብ በደቡብ ሆነው ነበር። ከፍ ከአለ ቦታ እየወጡ አሽቆልቁለው በመተኮስ፣ የጥይት በረዶ ከሰማይ አወረዱበት። ነጋሪታቸውን ከጋራው ላይ ውጋ! ወጋ! ውጋ! እያሰኙ አሰሙ። የመሬቱ አቀማመጥ ለአይሮፕላን ድብደባ የማይመች ሆነ። ከአይሮፕላን የሚጣለውን ስንቅና ትጥቅ ነፋስ እያንገዋለለ ወስዶ ለአርበኞች ሰጠው። አርበኛው ጣልያንን ከወንዝ ውሃ አላስቀዳ ብሎ ሰግጦ ያዘው። ወንዶች ልዩ ልዩ የጀግንነት ሥራ ሠሩ። ከምሽጉ ተጠግተው የጨበጣ ጦርነት አካሄዱ። አቶ ተክሌ እቁበ እግዚእ የተባሉ የሐማሴን ሰው ጣልያኑን ተናንቀው አጋድመው በጕራዴ ስለአረዱት እጅግ ተደነቁ። ጦርነቱ 12



መዓልትና 12 ሌሊት ወሰደ። ከሦስት መቶ በላይ ጣልያን ሞተ። የባንዳ ሞት ከቁጥር አልገባም። በልጅ ሐጐስ ተሰማ ግንባር የተገኘው ምርኮ የሰከረ አሣ መሰለ። ከአርበኞች ወገን ዘጠኝ ታዋቂ ጀግኖች ሞቱ፤ ብዙዎቹ ቆሰሉ። ጣልያን በመላ ጐንደር የነበረውን ጦር አስከትቶ በማዝመት አዴት ላይ የተከበበበትን ጦር አወጣ። የጠገዴ አርበኞች ይህንን አሳዩ። ነገር ግን የጣልያን የጦር ፍርድ ቤት በተከሳሾች የሰጠው ብያኔ ውጤት ህቡዕ እንደሆነ ቀረ።

በእነዚህ መራር የአርበኛ እንቅስቃዎች ላይ ጣልያን አፀፋውን እርምጃ ወሰደ። በመረባ፣ በያይራ፣ በጃኒ ፈንቀራ፣ በአርማጭሆ በድምሩ አንድ መቶ አሥራ ዘጠኝ ሰው በአንድ ሰሞን ጨፈጨፈ። ከእነሱም አንድዋ ሴት ነበሩ። ሌሎች 50 ሰዎች በቋራ ወረዳ ገደለ። ጣልያን የጐንደር ከተማንም ቀስፎ ያዛት። ብዙ ጦር ከየአለበት አመጥቶ አሰፈረባት፤ ዙሪያውን በእሾህም ሽቦ አጠራት። ሰው የሚወጣ፣ የሚገባው በዘጠኝ በሮች ብቻ ሆነ፤ እነሱም፡-

1. በሙሽራ ድንጋይ፣
2. በቀሃ ኢየሱስ፣
3. በቸቸላ፣
4. በልደታ፣
5. በአበራ ጊዮርጊስ፣
6. በአዲስ ዓለም፣
7. በደረቦ፣
8. በአርባዕቱ እንስሳ፣
9. በደብረ ብርሃን።

ነዋሪዎቿ በከተማይቱ ዙሪያ ከነቡሩ አሥራ አራት ምንጮች ከአንዱም ውሃ እንዳይቀዱ ተከለከሉ። ለወታደሩ በቀን ከአንድ መቶ እስከ ሁለት መቶ ፍሪዳ ከፋሲለደስ ሜዳ ላይ እየታረደ፣ ደሙና ፈርሱ በአሸንዳ፣ ቀሃ ወንዝ እንዲገባ ተደረገ። ሀበሻ የሚጠጣው ከዚያ በታች ሆነ። ቤታችሁን እያፈረሳችሁ ቦታውን ለጣልያን ልቀቁ ተባለ። ጣልያኖች የሲጃራ ትርኪሽ በማስመሰል እሳት እየወረወሩ የበዙ ሰው ቤት አቃጠሉ። ሆቴል ቤትና ሲኒማ ቤት ሀበሻ እንዳይገባ ተከለከለ።

ጣልያን የአርበኞችን ኃይል መቋቋም የማይቻለው ሆነ። አጀ ከተባለው ቦታ የነበረው አገረ ገዥ በመልዛ፣ በመቅጠዋ፣ በመና፣ በቋሊሣና በእበናት የሚኖረው ሕዝብ፡- 1ኛ. በእጅ የሚገኘውን መሣሪያ እንዲያስረክብ፤ 2.ኛ አንድ ሺህ አምስት መቶ ወጣቶች መልምሎ እንዲሰጥ አዘዘ። ግንቦት 23 ቀን 1929 ዓ.ም ከምሽቱ አራት ሰዓት ሲሆን፣ አቶ ይግዛው የተባለ ሰው "ጦር በላህ" እያለ ለፈፈ። ሕዝቡም በየሸንተረሩ እሳት በማንደድ እርችት አሳየ። ጣልያን ይህንን ሸሽቶ ደብረ ታቦር ገባ። ከዚያም አዛገፉ ወደ ጐንደር በመሄድ ከአማራ አገር መሪ መመሪያ ተቀበለ። አዲሱን መመሪያ ይዞ አጀ ሰኔ

5 ቀን 1929 ዓ.ም ገባ። እንደገባም ምህረት ተደርጐላችኋልና ግቡ የሚል ቃል አስነገረ። ሕዝቡ የተካሄደ ጦርነት ስለአልነበረ በመዘናጋት በብዛት ገባ። እሱ ግን ትእዛዝ የተሰጠው በምህረት አስመስሎ ከሰበሰበ በኋላ ሕዝቡን እንዲፈጅ ነበረና፣ ከሰኔ 12 እስከ 30 ቀን ድረስ ከሰበሰበ በኋላ ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል በመትረየስ ፈጀው። እስከ አምስት መቶ የሚገመት ሰው አለቀ።

በወቅቱ፣ አካባቢውን አንበጣ ስለበላው፣ አርበኛውን በጦር ላይ ረሃብ ተደረበበት። ጠላት ይህንን በማወቅ ነጋዴ እንዳይተላለፍ ከለከለ። ስለዚህ አርበኛው የሚመገበው ሴንሣ፣ ሣዳ፣ ሜብሴ የሚባሉትንና የመሳሰሉትን ሥራ ሥሮች ሆነ። ወንዱ ለጦር ሲወጣ፣ ሴቱና ልጁ ሥሮችን እየፈለገ፣ እየማሰ ይለቅማል። ፋታ ሲገኝ ወንዱም ይፈልጋል።

አርበኛው በዚህ ሁኔታ ላይ እንደአለ፣ ጣልያን ወደ አርማጭሆ መውረድ ጀመረ። ሻለቃ ካሶሎኒ በተባለ መኰንን የሚመራ 15 ባታልዮን ጦር ተንቀሳቅሶ ጨግ ውሃ ላይ ሠፈረ። ይህንን ሁኔታ አርበኛው የሚታገሰው ስላልነበር፣ አትኳሮ በር ላይ ሰኔ 5 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። ታዋቂ ሃምሣ ዘጠኝ አርበኞች ሞቱ፤ ብዙዎች ቆሰሉ። ከጠላት ወታደርም እንደዚሁ ብዙ አለቀ። ነገር ግን ጣልያንን ማባረር ሳይቻል ቀረ።

ሐምሌ 1 ቀን ደግሞ የቀሩትን ለመፍጀት ሲዘጋጅ፣ አቶ በርሁን ፈረደ የተባለ ሰው የደበቀውን መውዜር ሚስቱ ስለአቀበለችው፣ ሐምሌ 5 ቀን ተኩስ ከፍቶ አዛዡን ጣልያን ገደለው። እሱንም ወንድሞቹ ረዱት። ወንዱም፣ ሴቱም፣ በአጠቃላይ ሕዝቡም ተባብሮ፣ በድንጋይና በዱላ፣ በአፈርና በቅጠል ጠላቱን ደብድቦ በማባረር ቦርድ ተይዘው የነበሩትን ሰዎች አዳነ። በዚህ ቀን ሠላሣ የሚያህል የጠላት ወታደር ተገደለ፤ መሣሪያም ተማረከ። ጣልያንም መቀጠዋ የእያዳ ማርያምን ቤተክርስቲያን አቃጠለ። ጠላት በአጥቢያው የነበረውን ሕዝብ ቤት እያዘጋ አነደደው። አንድ ሕፃን ከእሳቱ አምልጦ ቢወጣ፣ መልሶ ጨመረው።

በሐምሌ ወር 1929 ዓ.ም ጠላት ከዳባርቅ ተንቀሳቀሰ። በአንቃሽ፣ በወደበኝ አድርጐ የአቋሶን ወንዝ ተሻግሮ መረባ ደረሰ። በልጅ አንዳርጌ ደስታ የሚመራው አርበኛ አስተርእዮ ከተባለው ሜዳ ላይ ገጠመው። ባለቤቲቱ፣ ወይዘሮ ከበቡሽ ጥሩንባ እያስነፉ የአካባቢውን ሕዝብ ቀሰቀሱ። ዋናውን፣ አዛዡን ጣልያን፣ ልጅ አንዳርጌ በመውዜር ሽንጡን ቆርጦ ገደለው፤ የባንዳው ሹም በሻ አበበም ተመትቶ ወደቀ። መሪዎቹ ሲያልቁ ባንዳና አርበኛ በጥሪ ተነጋገረ። ባንዳ "...ላትችል በከንቱ የሰው ደም ታፈሳለህ..." አለ። አርበኛ መልሶ "አንተ የአሕዛብ ሎሌ... በአገርህ ጣልያን ቢነግሥባት ትወድ ይሆን" ብሎ ጠየቀ። ጦርነቱም በዚሁ አበቃ።

ጣልያን ጉዞውን በመቀጠል ድርኳዜ ደረሰ። ቆራጥ ጀግኖች ዘጠኝ ሆነው፣ ነሐሴ 17 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት። በመልዛ /ቆላ ደጋ/፣ በቋሊሣ፣



በእብናት የነበረ አርበኛ እየተጠራራ ተሰበሰበ። ጠላቱን ከብቦ እንደ ንብ ጠዘጠዘው። ውጊያው ለአራት መዓልትና ለአራት ሌሊት ያለማቋረጥ ቀጠለ። ጦርነቱ ከጠላት ወገን ከአይሮፕላን በሚጣል ቦምብና በሚተኮስ መትረየስ፣ በምድር ደግሞ በመድፍና በመትረየስ፣ ቁጥሩ እጅግ በበዛ ወታደር ሲሆን፣ በአርበኞች ወገን በጥቂት ጥሩ ጠመንጃና በጐራዴ፣ በጦር፣ በዱላና በድንጋይ ነበር። በአምስተኛው ቀን ጠላት በሻምበል ብራንዲኒ የሚመራ አዲስ ጦር በመላክ የተከበበውን ጦሩን አወጣ። በዚህ ጦርነት ሠላሣ ሦስት እውቅ አርበኞች ወደቁ። በጠላት ወገን ሁለት ሻምበሎች፣ አምስት መቶ አለቆች ሞቱ። ብዙ ወታደር አለቀ። ጣልያን በሚሸሽበት መንገድ ላይ በአጋጣሚ እጁ የገቡትን ሃያ ስምንት ሰዎች በመትረየስ ፈጅቶ ሽሽቱን ቀጠለ።

ሻለቃ ፋሊቲ ታላቅ ጦር ይዞ ከደብረ ታቦር በመነሳት በመና፣ በመቀጠዋ አድርጐ ጉዞውን ቀጠለ። ሃሳቡ ከቋሊሣ ቆላ አንስቶ እስከ ደጋው ድረስ ያለውን አገር ለማጥፋትና ሕዝቡን ለመፍጀት ነበር። ሁኔታውን አርበኞች ደርሰውበታል። ነገር ግን የአቅማቸውን ማነስና የጠላትን መበርታት እያመዛዘኑ ማመንታት አበዙ። ፍርሃት ማየሉን የተመለከተ አቶ ተሾመ የተባለ ደፋር "የፍርሃትመድኃኒት እኔ ላሳያችሁ" ብሎ ቀይ አፈር ላይ አንድ ጥይት ተኮሰ። ሻለቃ ፋሊቲ ለጦር በመዘጋጀት አካባቢውን በመንደር ሲቃኝ፣ ሴቶቹ በተራራ ላይ ሲተረማመሱ አየ። "ወንድ ልጅ ሴት ከአየ ይሞታል እንጂ አይሸሽም። ይህ ጦርነት የበረታ ነው። የበረታ ይዋጋ፣ የፈራ ይሸሽ። እኔ ግን እሞታለሁ እንጂ አልሸሽም፤ አልማረክም።" የሚል ቃል ተናግሮ ጦርነቱን ከፈተ። ጦርነቱ እንዳለውም የበረታ ሆነ። ወንዱ በጥይት ሲዋጋ፣ ሴቱ ከተራራው ላይ መርግ ለቀቀበት። መርጉ ሠራዊቱን ከመፍጀትና ከማስደንገጡም በላይ፣ ሬዲዮ የተጫኑትን አጋሰሶች ገደል ስለጨመራቸው ግንኙነቱ ተቋረጠ። ጦርነቱ ለአምስት ቀን ቆየ። የጠላት ወታደር መሣሪያውን እያመጣ ለአርበኞች እያስረከበ ሽሽቱን ያዘ። ሻለቃ ፋሊቲ ከጦርነቱ ላይ በጀግንነት ሲዋጋ ሞተ። በወታደሩ ፊት የገባውን ቃል ኪዳን ፈፀመ። ሆኖም ሞቱ አንድ ሣምንት ድረስ ለወገኖቹ ሳይሰማ ቀረ። በዚህ ጦርነት አንድ ባለውሃ መትረየስ፣ ስድስት ቀላል መትረየሶች፣ ሦስት መቶ አልቤን ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ተማረከ። ጣልያን አካባቢውን፣ መጃ የተባለውን ቦታ ጭምር ለቅቆ ወጣ። አገሩም ከጠላት ቁጥጥር ነፃ ሆነ። ጦርነቱ የአርበኝነትን ሥራ አደረጀ። በዚህ ታላቅ ጦርነት የሞቱት አሥራ አምስት፣ የቆሰሉት ደግሞ ሰባት አርበኞች ብቻ ነበሩ። ከጠላት ወገን ብዙ ነበር።[5]

የጣልያን መግባት ሲሰማ የመና፣ የመቀጥዋ፣ የመልዛና የሐሙስ ወንዝ ሕዝብ የጐበዝ አለቆቹን መረጠ። በነሐሴ ወር 1929 ዓ.ም ቋሊሣ፣ ድርኳዜ ላይ ተዋጋ። ወደ ኋላ የሸሸው የጠላት ጦር ሁለት መድፍና አምስት ሺህ ወታደር ይዞ መጣ። አርበኛው ጦር ስለከበደበት ማገድ ተሳነው። ስለዚህ ጣልያን በግስጋሴ ጳጉሜ 1 ቀን እብናት ገባ። ጳጉሜ 5 ቀን አገሩን

ለማቃጠልና ሕዝቡን ለመፍጀት ሲንቀሳቀስ አርበኛው ጦርነት ገጥሞ እስከ ደሪባ ድረስ አባረረው። ጠላትም ተመልሶ እብናት ገባ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ አገኙ።

የ1929 ዓ.ም የጐንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1930ው ተተካ። ጣልያን ዓርብ ገበያ ላይ ሠፍሮ መሣሪያህን አግባ እያለ አዘዘ። ሕዝቡ መሣሪያ ከማግባት ቸል ቢል በመቀጠዋ፣ በመልዛ፣ በእብናትና በመና የደረሰው እንዳይደርስብህ እያለ ያስፈራራ ጀመር። ትዕግስት የማይበግረው ሆነ። ከሠፈሩም አልንቀሳቀስ አለ። የነገ አርበኛ መስከረም 2 ቀን 1930 ዓ.ም አርብ ገበያ ድረስ ሄዶ ገጠመው። በመትረየስና በጠመንጃ ጥይት ተለቀቀበት። እምብዛም ሳይቆይ በእጅ ቦምብ ይደበድበው ጀመር። በዚያም የጨበጣ ውጊያ ተተካና በዱላ ይነርተው፣ በጐራዴ ያወራርደው ያዘ። ወዲያው ምሽጉን ሰብሮ በመግባት አረደው። አምስት ጣልያኖች ከብዙ ወታደር ጋር ወድቀው ተገኙ። የተረፉት የጠላት ወታደሮች መሣሪያቸውን እያስረከቡ ተለቀቁ። ከአርበኞች ወገን አርባ ሦስት ታዋቂ ሰዎች ሞቱ፤ ሌሎች ሠላሳ ሰባት ቆሰሉ።

የአርብ ገበያ ጦርነት በደብረ ታቦር ሌላ ድንቅ ሥራ አስከተለ። ለጠላት ተቀጥረው በሊቢያ ሲዋጉ የነበሩ ኤርትራውያን፣ በኢትዮጵያ ላይ ያንኑ ሥራ ቀጥለው ነበር። የዓርብ ገበያ ምሽግ ሲፈታ፣ መሣሪያቸውን እያስረከቡ በመሸሽ ደብረ ታቦር ገቡ። ከዚያ ለነበረው አዛዥ የደረሰውን ሁኔታ ነገሩት። ይራራልናል ብለው እነሱም በርህራሄ እንደተለቀቁ አስረዱት። መቶ አለቃ ሚላኖ ግን "...እናንተ ወገን ስለአላችሁ ተለቃችሁ መጣችሁ። ወገን የሌላቸው የእኛ ሹማምንቶች ከዚያው ሞተው ቀሩ..." ብሎ ከጦር ሜዳ ላይ በመሞት ፋንታ መሣሪያቸውን አስማርከው በመምጣታቸው ሰባ አራቱን ሰዎች ፊታቸውን እንዲያዞሩ አድርጐ በመትረየስ ፈጃቸው። ከጠላት ወዳጅ ይልቅ የወገን ጠላት እንደሚሻል በዚህ ታወቀ።

አርበኞች በተደጋጋሚ በአገኙአቸው ድሎች ተበራትተው፣ ደብረ ታቦርን ለማስለቀቅ ተንቀሳቀሱ። እስቴ ወረዳ ሲደርሱ፣ መካነ ኢየሱስ የነበረው ጣልያን ምሽጉን ለቅቆ ጉዞ ጀመረ። የመልዛ፣ የእብናት፣ የሐሙስ ወንዝ፣ የመቀጥዋ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ከፊትና ከኋላ፣ ከቀኝና ከግራ ከብቦ በጥይት እየደበደበ ደብረ ታቦር አገባው። ይህንን ሲያይ፣ አገር ሲገዛ በየቦታው የተሠራጨው ጣልያን እየበረረ ደብረ ታቦር ተከተተ።

አርበኛው የደብረ ታቦርን ከተማ ከበበ። የጋይንር፣ የነገላ፣ የፋርጣ፣ የእስቴ፣ የሙጃ፣ የስማዳ፣ የቆማ፣ የጥናፋ፣ የሐሙስ ወንዝ፣ የመልዛ፣ የእብናት፣ የመቀጥዋ፣ የቋሊሣ አርበኛ በጠላቱ ላይ ክንዱን ዘረጋ። ከመስከረም 15 እስከ 19 ቀን 1930 ዓ.ም ድረስ ተዋጋ። ጣልያንም በበኩሉ እየተከላከለ ከጐንደርና ከደሴ ረዳት ጠራ። ከጐንደር የመጣው የጠላት ጦር መሬቱን እያጥለቀለቀ በእግርና በፈረስ መጣ። አርበኛው ዓለም ሥጋ ላይ



ገጠመው። ፈረሰኛውን በጥይት ከፈረሱ ላይ ዘነጠፈው። ሳይሞት የሞተ እየመሰለ ከሬሣ ውስጥ ከተደበቀው በስተቀር፣ እግረኛውን ለወሬ ነጋሪ ሳያስተርፍ ፈጀው። ብዙ ቀላል መትረየስና ጥይት፣ የእጅ ቦምብ ተማረከ። ያም ሆኖ ግን ደብረ ታቦርን ማስለቀቅ ሳይቻል ቀረ። ከአርበኞችም ወገን ዓርብ ገበያ፣ ዳንትና ገረገራ የወደቁትን ጨምሮ ሰባ አራት ታዋቂ አርበኞች ሞቱ፤ ብዙዎች ቆሰሉ።

በግራዝማች አረዳ ተሰማ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው የአርበኞች ቡድን መስከረም 15 ቀን 1930 ዓ.ም አማኒት ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አካሂዶ የመጣበትን ጠላት መለሰ። በዚሁ ወርና ዘመን ጠላት ወደ ቋራ ለመሄድ በሚንቀሳቀስ አንድ የአርበኞች ቡድን ላይ አደጋ ጣለ። በጦርነቱ የአርበኞቹ መሪ ዓይናቸውን ተመቱ። ቢሆንም ሳራቆ ሄደው በማገገም ከወር በኋላ የአርበኝነት ሥራቸውን ለመቀጠል ቻሉ።

ከደሴ የተጠራው ጦር የወሎን፣ የየጁን፣ የአምባሰልን ባንዳ አጋትሎ ተንቀሳቀሰ። በጄነራል ቶሲቲ እየተመራ በደላንታና በዋድላ አድርጎ ጋይንት፣ ጨጨሆ ከተባለው ቦታ ሠፈረ። አርበኞች ጋንጋ የተባለውን ተራራ ይዘው ጥቅምት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። ከወሎ የመጣው የጠላት ጦር የመጀመሪያው ነበርና ውጊያው ከባድ ሆነ። ጠላት በቦምባርድ፣ በመድፍና በመትረየስ፣ እጅግ ብዛት ባለው ሠራዊት በመዋጋት የገጠሙትን አርበኞች ከአለቃ እስከ ጭፍራ ደምስሶአቸው አለፈ። የደብረ ታቦሩ የጦር አዛዥ የአርበኞችን የጦር ሥልት ስለተላመደው የመጣለትን ረዳት እንዳይጨርሱበት ሊቀበለው ወጣ። ክምር ድንጋይ ሲደርስ የፋርጣ፣ የስማዳ፣ የሰዴ፣ የሙጃ፣ የቆማ አርበኛ በየአለቃው እየተሰለፈ ወጋው። ቢሆንም የጠላት ጦር በኃይል እየገፋ ክምር ድንጊይ ደረሰ። ከደሴ የመጣውን ጦር ደግሞ የጋይንት አርበኞች በስተምዕራብ፣ የነገላ በስተሰሜን ሆነው ጠዘጠዙት። እሱም በእጅ ቦምብና በመትረየስ ብዛት ማህሉን ጥሶ ነፋስ መውጫ ደረሰ። የደብረ ታቦሩና የደሴው የጠላት ጦር ጉሎጊ ወንዝ ላይ ተገናኘ።

አርበኛውም በበኩሉ ተስፋ አልቆረጠም። ከወደ ወሎ ወገን የጋይንት፣ የነገላ፣ የመቂት አርበኛ፤ ከጐንደር ወገን ደግሞ የፋርጣና የስማዳ፣ የቆማ አርበኛ ገጠመው። የማደና የማዶውን የጠላት ጦር በጥይት ሸነቆጠው። ጦርነቱ ዚእከ ለዚአየ የተባለውን የገንፎ አበላል አይነት ሆነ። ቢሆንም ጣልያንን ማገድ አልተቻለም። ሁለቱም ጦር ተቀላቅሎ እየተዋጋ ጥቅምት 15 ቀን 1930 ዓ.ም ደብረ ታቦር ገባ። በልጅ አበራ ረዳ የሚመሩ አርበኞች ጥቅምት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ጭልጋ፣ መቀነት ኪዳነ ምህረት በጠላት ላይ አደጋ ጥለው ሃያ ጠመንጃ ከነጥይቱ ማረኩ።

ከጐንደር ወደ ደብረ ታቦር የሚወስደውን የመኪና መንገድ ዓለም ሥጋ ላይ አርበኞች መስከረም 29 ቀን 1930 ዓ.ም ቆርጠውት ስለነበር ጣልያን እሱን አልሶ ለመሥራት መጣ። ሀገሩን ለማሳመን አላምን ካለም

ለማጥፋት የሚያስችለው ከፍተኛ ጦር አምጥቶ መደብና ውዶ ከሚባሉት ቦታዎች ላይ አሠፈረ። አርበኛው ኮካ የተባለውን በር ይዞ ሲቻለው እያጠቃ፣ ሳይቻለው እያፈገፈገ ተከላከለ። ጥቅምት 18 ቀን 1930 ዓ.ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ቀን ተዋጋ። አሞራ ገደል፣ አልጋ ጭንጫ ከተባለው ቦታ ለመገናኘት ተቃጥሮ፣ መደብና ውዶ ከተባሉት ሁለት ቦታዎች የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር፣ ከተቃጠረበት ቦታ ሳይደርስ መሸበት። ጥሶ ለመሄድም የማይቻለው ስለሆነ ደንጉርሣ ከተባለው ተራራ ላይ ሠፍሮ አደረ። ምሽቱ ስለአገዛቸው ተከበው የነበሩት አርበኞች ሰብረው ወጡ። በዚህ ቀን በተደረገው ጦርነት ሼህ አሊ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተገደለ። ከደብረ ታቦር እስከ ጩጩሆ በተደረገው ጦርነት አርባ አምስት አርበኞች ሞቱ፤ ሁለቱ የጦር ፊታውራሪዎች ነበሩ።

ጣልያን በጥቅምት ወር 1930 ዓ.ም አውሣ፣ ጀጉል ባንባ በተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አደረገ። ሳይቀናው ስለቀረ አውሣ ከነበረው ምሽጉ ተመልሶ ገባ። በድጋሚ ሊዘምት ሲዘጋጅ በአቶ ባሕታ አሥራት የሚመራው አርበኛ ሐሙስ ቀን የከበበ እስከ ዓርብ ማታ ድረስ ያለዕረፍት ወጋው። ጣልያንም በሌሊት አምልጦ መተማ ገባ። በዚህ ጦርነት አርበኞች አንድ የውሃ መትረየስ፣ አንድ ቢዛንቲ መትረየስ፣ አሥራ ስድስት ረጃጅም አልሜን ማረኩ። አሥራ አምስት ካሚዮኖች በእሳት እንዲቃጠሉ ተደረገ። ሦስት አርበኞችና አሥራ አምስት የጠላት ወታደሮች ሞቱ።

በስማዳ ወረዳ የነበሩትን አርበኞች ለመደምሰስ ጣልያን ጦሩን አንቀሳቀሰ። አርበኞችም ቀንበር በር ላይ ጠብቀው ህዳር 13 ቀን 1930 ዓ.ም ጥዋት ገጠሙት። ቦታው ተመርጦ የተያዘ ነበርና ለአርበኞች አመቸ። ጦርነቱ እስከ ስምንት ሰዓት ቀጠለ። እረይ መንግሥቱ የተባለ በአንድ መዝገብ /ካርታ/ መትረየስ፣ አምስት የጠላት ወታደሮች በመጣል፣ የዕለቱን ጀብዱ ጨበጠ። የጠላት ጦር አዛዥ ተከቦ አድሮ፣ በማግስቱ ጥዋት እጁን ሰጠ። ብዙ መሣሪያ ተገኘ። ከአርበኞች ወገን የቆሰለ እንጂ የሞተ አልነበረም።

የስማዳ፣ የጥናፋና የቆማ አርበኛ፤ እስቴ፣ ቁት አምባ የነበረውን የጠላት ጦር ህዳር 22 ቀን 1930 ዓ.ም አጠቃ። የጠላትን ጦር ከአካባቢው ለመንቀል ዙሪያውን ከብቦ፣ በአለው መሣሪያና ኃይል ተዋጋ። በሦስተኛው ቀን ጠላት በላላበት ወገን ሰብሮ በመውጣት፣ ወደ ደበረ ታቦር ሸሸ። አርበኛው እየተከታተለ ቢወጋውም ከደብረ ታቦር ኮሎኔል አንጀሊኒ ፈረሰኛ ጦር ይዞ መጥቶ ስለረዳው ዳነ። በዚህ ቀን ብቻ 18 አርበኞች ሞቱ። መሰንበቻውን በተካሄደው ያለቀው ግን ብዙ ነው። ከቆማ አርበኛ ብቻ አርባ አምስት አርበኞች ሲሞቱ፣ ሌሎች ስድሣ ሰባት ቆስለዋል። ሰባት ተማርከው በጠላት እጅ ተገድለዋል። ከጠላት ወገን የሞተው እጅግ ብዙ ነበር።

በህዳር ወር 1930 ዓ.ም ጠለምት አድ ወሰኔ ላይ የነበረው ጣልያን የአርበኞችን ቤተሰቦች ሰብስቦ እሥር ቤት አጐረ። ምሥጢሩ አርበኞቹ



ለዘመዶቻቸው ብለው ሲገቡ አብሮ ለመጨረስ መሆኑ ታወቀ። አርበኞች በፊናቸው ምሽጉን አጥቅተው ወገኖቻቸውን በኃይል የሚያስለቅቁበት ዕቅድ አዘጋጅተው ከሌሊቱ በስምንት ሰዓት አደጋ ጣሉ። ከንጋቱ በሦስት ሰዓት ጠላት ምሽጉን ለቅቆ ሸሸ። ከታሠሩት ስምንት ቤተሰቦች አንዲቱ ብቻ ስትቆስል የቀሩት በጤና ወጡ። ሁለት መቶ አልቤን ጠመንጃ ከነጥይቱ ከምሽጉ መጋዘን ተገኝቶ አርበኞች እጅ ገባ። ጣልያን እነዚህን አርበኞች ለማጥፋት ብዙ ጦርና ባንዳ አስከትቶ መጣ። አርበኞችም ጠለምት ወይላ ከተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ መጣበት መለሱት። ቦታው የመሬት አንጋዳ ስለሆነበት ጠላት ብዙ ጉዳት ደረሰበት። አርበኞች ከጥዋቱ አምስት ሰዓት ጀምረው እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ባካሄዱት በዚህ ጦርነት ከድል ጋር ብዙ ምርኮ አገኙ።

ቀደም ብሎ የደረሰበትን ሽንፈት ከሕዝብ መንፈስ ለመፋቅ ጣልያን ተንቀሳቀሰ። አርበኞች ምቹ ቦታ ይዘው በመጠበቅ ቤዛሆ ላይ ታህሥሥ 3 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። የተወለደበትን ቀን እስኪረግም በጥይት ቀጥቅጠው አባረሩት። ሃምሣ ለበን ጠመንጃዎች ማረኩበት።

ጣልያን ሃያ ሺህ ጦር ይዞ ከደብረ ታቦር ተነሣ። ስምንቱ ሺህ እጅጉ አያሌው በተባለ ሰው የሚመራ ባንዳ ነበር። የጦሩ ብዛት በሀገሩ ላይ ጭንቀት አሳደረ። አርበኞች የቻልነውን ያህል ሠርተን እንሙት ብለው ለጦርነቱ ተዘጋጁ። ታላቅ ፀሎት አድርገው ታህሣሥ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ስምና ከተባለው ቦታ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ጦርነቱ ሲደራ ሽማግሌው፣ ሴቱ፣ ልጁ፣ አሮጊቱ፣ መንቀሳቀስ የማይችለው ሽባው ሁሉ በያለበት ሆኖ ጮኸ፤ በለው! ወጣልህ! ወረደልህ! በማለት ተንጫጫ። ጫጫታው ስለአስደነገጠው ባንዳው ተፈታ። የባንዳው መሪ እጅጉ አያሌውም ከፈረሱ ላይ ሆኖ ሸሽቱን ያዘ። መደበኛው የጣልያን ጦርም በሁኔታው በረገገና ሸሽቱን ያዘ፤ አርበኛው በየጉጡ በጥይት ጠበሰው። የጠላት ጦር ሲጨንቀው መሣሪያውን በጫርቁ ላይ እየደረደረ ለአርበኛው ያስረክብ ገባ። ገሚሱም ዓይኑ እያየ ገደል ገባ። አጋምና ቀጋ፣ ጉመሮና ቀንጠፋ እየጠለፈ ያስቀረው መሣሪያ ብዙ ነበር። በየቦታው የተደረደረውን መሣሪያ አርበኛው አነሣ። በየጥሻው የወደቀውን መሣሪያና በየሜዳው የፈሰሰውን ጥይት ሴቱ፣ ልጁ እየለቀመ በጠፍር፣ በገመድ እንደ እንጨት እያሠረ በመሸከም አጋዘው።

አርበኛው ልቡ እየደነደነ ስለሄደ፣ የማጥቃቱን ሥራ አጠናከረ። ጣልያንም በበኩሉ ባንዳን አበረታታ። ለምሣሌ ልጅ ሐደራ ረዳ የተባሉትን፣ አርበኛ የነበሩትን ሰው፣ በጓደኞቻቸው ላይ ያደረባቸውን ቅያሜ ተጠቅሞ አስከዳቸው። ከዚያም "ደጃዝማች ብትገድል ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ ብትገድል ፊታውራሪ እልሀለሁ" የሚል ደብዳቤ ፃፈላቸው። ሞኝ እንደመከሩት ገድዬ እሾማለሁ ብለው ሲውተረተሩ፤ የጥንፍራ አርበኛ፣ አዘነብ በተባለው ቦታ ላይ በተደረገ ጦርነት ማረካቸው።

በአዝማች ታጅቦ ካሣ መሪነት የዘመተው ባንዳ፣ ካርዋ ላይ፤ በፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም የሚታዘዝ ጦር ይዞ የመጣው ጣልያን፣ ሱባ ላይ፤ በፊታውራሪ ኮከቤና በፊታውራሪ አውደው ፈለቀ እየተመራ የመጣው፣ ግልቢና ላይ፤ በፊታውራሪ መንገሻ የሚመራው፣ ጭንፍራ ላይ፤ በፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም አዝማችነት ለሁለተኛ ጊዜ የዘመተው፣ ጥጉና ላይ፤ በመምህር ገብረዋህድ አስናቀው የሚታዘዘው ባንዳ፣ ደንቆላኮ ረድ ላይ፤ በሙሉ ድል እየተመታ አለቀ። ዮሴፍ አባዘርጋው የተባለውን የባንዶች አለቃ ፊታውራሪ ከዴ የተባሉት አርበኛ ብቻ ገጥመው ገድለውት ሞቱ። የቆሰለውም ከጣልያን ማገገሚያ እንኳን ሳያገኝ ደምና መግሉን እያንጠፈጠፈ ከጥቅም ውጭ ሆነ። በዚህ ሁኔታ ባንዳ ልብ ወረደው። ጣልያን ጥሩምባ ባስነፋ ቁጥር፣ ማረጥረጡን ተወ።

ይህ ሲሆን ጣልያን መደበኛ ወታደር በየጦሩ ጐራ ማዝመት ያዘ። ጥር 5 ቀን 1930 ዓ.ም በሁመራ ወደ ቀብትያ ወታደር በካሚዮን ሲያመጣ፣ በፊታውራሪ መሥፍን ረዳ የሚመራው አርበኛ ክሣድ መልአ ከተባለው ቦታ በጥይት ጠመደው። ብዙ ጣልያኖች ሞቱ። ሳያነሣ ጥሎአቸው የሄዱ ሰባት ቁስለኞች ከሜዳ ላይ ወድቀው ሞሶሎኒንና የተወለዱበትን ቀን ሲረግሙ ታይተዋል። የተረፉት ጣልያኖች በመኪና ጐራውን ሰብረው ቀብትያ ገቡ። ጥር 10 ቀን 1930 ዓ.ም ደንቢያ ላይ እንደዚሁ ጦርነት ተደረገ። አርበኞች ደንቢያ ቸንክል ከተባለው ቦታ የነበረውን የጣልያን ምሽግ በዚህ ዕለት አጥቅተው ሽብር ለቀቁበት። በጦርነቱም ጥቂት ከብትና አሥር ጠመንጃ ከጥይት ጋር ማረኩ።

አርበኞች ከቀብትያ ወደ ኤርትራ የሚወስደውን መንገድ ለመቁረጥ ድልድዩን መሥበር ጀመሩ። ጣልያን በድብቅ መጥቶ ጥር 12 ቀን 1930 ዓ.ም እጣን እብኒ ላይ አደጋ ስለጣለባቸው፣ በድንገት ጦርነት ተከፈተ። አርበኞች በፍጥነት ተበትነው በየሥርቻው በመግባት ተከላከሉ። ጣልያን ያሰበው በሥራ ላይ እንደአሉ ለመፍጀት ነበርና፣ እንዳመለጡት ሲያይ ተመልሶ ቀብትያ ገባ። በዚሁ በጥር 12 ቀን ሌላው የአርበኞች ቡድን ጭልጋ በነበረው የጠላት ምሽግ ላይ አደጋ ጥሎ አካባቢውን አሸበረ።

ጥር 1 ቀን 1930 ዓ.ም በግራዝማች ረዳ ተሰማ የሚመራው የጭልጋ አርበኛ፣ አንጓባ ላይ መሽጐ የነበረውን ጣልያን ከብቦ በብዙ አስጨነቀው። ይኸው የአርበኞች ቡድን የአይከልን ምሽግ ከብቦ ሲዋጋ ሰንብቶ፣ ሠብሮ ለመግባት እንደ አልተቻለው ሲገነዘብ ወደ ይዛ ተመለሰ። እንደዚሁም ሚያዝያ 25 ቀን 1930 ዓ.ም አውጋ፣ ወገሚት ወንዝ አደጋ ጥሎ፣ በጠላት ላይ ጉዳት አድርሶአል። ይህ ቡድን የሚጠቀምበት ሥልት በየአለበት፣ በየጊዜው አደጋ እየጣሉ ጠላትን ማጥቃት፣ ማበሳጨትና በሕዝብ ዘንድ የነበረውን ተአምር መቀነስ ነበር።



የጀንዋራ፣ የቆላ ወገራ፣ የአርማጭሆ፣ የጠገዴ፣ የደለሎ፣ የደብረ ሐዋርያ፣ የቀብትያ፣ የአውሣ፣ አርበኞች ተሰብስበው የወልቃይትን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት ተማከሩ። ምክሩ 5 ቀን ወሰደ። የአድረመድን ምሽግ በመስበር በዚያ የነበረውን የጠላት ኃይል ለመደምሰስ ተወሰነ። ጣልያን ምክሩን ሰምቶ አድ ኮከብ ላይ ሠፈረ። አርበኛው ሌሊቱን ሲሣብ አድሮ የካቲት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ከንጋቱ 11 ሰዓት አደጋ ጣለበት። ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ከጠላት ሠራዊት እኩሉ ፊቱን ወደ ማይ ወላሞ፣ እኩሉ ወደ አውራ፣ እኩሉ ወደ አድረመጥ ሸሸ። አርበኛ እግር በእግር እየተከታተለ በጥይት ደበደበው። የጠላት ወታደር ሬሣ በአንዳንድ ቦታ እንደ ክምር ተቆልሎ ነበር። ከአርበኞች ወገን ሃምሣ ስድስት ታዋቂ አርበኞች ሞቱ። ከአድ ረመጥ በስተቀር ሌላው የወልቃይት ወረዳ ነፃ ወጣ። አርበኛው ነፃ ለወጣው ሀገር አስተዳዳሪ ፊታውራሪ መሥፍን ረዳን መርጦ ወደየስፍራው ተመለሰ። ጣልያን ይህንን ጦርነት ለመበቀል ልጅ አዋቂ፣ ወንድ ሴት ሳይል ብዙ ሰው ፈጀ። ብላንባ ከተባለው ቀበሌ ብቻ ሃምሣ ስምንት ነፍስ ገደለ።

የቋራው የጣልያን አገረ ገዥ በአካባቢው የነበሩትን አርበኞች የሚያጠፉለት ጦር ላከ። ጦሩ ጥቂት ባንዶች የተቀላቀሉበት መደበኛ ጦር ስለነበር ቀላል አልነበረም። አርበኞች ጀሆ ላይ ጠብቀው መጋቢት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ወግተው መልሰው ወደ መጣበት አባረሩት። ጠላት ይህንን ጥቃት ለመመለስ ሌላ አዲስ ጦር ይዞ መጣ። በደጃዝማች አያና ቸኮል የሚመራው አርበኛ አዲስ የመጣውን ጦር ሠራቆ አባዬ ከተባለው ቦታ ላይ ገጠመው። ጦርነቱ ስለአየለ የአውሣ፣ የጫቆ፣ የተንከል፣ የአርማጭሆ አርበኞች ለእርዳታ በግሥጋሴ ደረሱ። ጣልያን ቀን ሲመሽለት ሌሊት አምልጦ ጧራ ገባ። አርበኛው ተከታትሎ ሄዶ ምሽጉን ከበበ። ከመጋቢት 25 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 1930 ዓ.ም በመዓልትና በሌሊት ሳያቋርጥ ወጋው። በሩን ሠብሮ በመግባት የአገረ ገዥውን ቤት የሚጠብቁትን ዘበኞች መሣሪያ እስከ መንጠቅ ደረሰ። ሆኖም ጠላት ከመተማ ሌላ ጦር አስመጥቶ ከባባውን አፈረሰ። አርበኞችም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ሠራቆ ተመለሱ። በዚህ ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም አምስት ጀግኖች ወደቁ።

ጣልያን ግንቦት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ከጭልጋ ወደ መተማ ለመውረድ ተነሣ። ዋሊ ደባ ከተባለው ቦታ ሲደርስ አርበኞች ገጥመው በጦር ኃይል ወደ መጣበት ምሽግ መለሱት። ምርኮም አገኙ፤ በርካታ የጠላት ወታደር ገደሉ፣ አቆሰሉ። ከእነሱ የሞቱባቸው ሁለት ጀግኖች ብቻ ሲሆኑ አንዱ ቄስ ናቸው።

ወልቃይት የተባለው አገር ለማጥፋት ጣልያን በሻለቃ ፍራንቻሊ የሚመራ አምስት ባታልዩን ጦር ከወልቃይት አንቀሳቀሰ። ይህንን የመሰለው አገር የማጥፋት ዘመቻ መቆም ስለነበረበት ሰባት አርበኞች በደጃዝማች ደስታ ማሩ መሪነት ግንቦት 5 ቀን 1930 ዓ.ም አዲ ገርትየ ከተባለው ቦታ

ገጠሙት፡፡ ምንም ቦታው ምቹ ቢሆንላቸው አርበኞች የመጣውን ጦር ማገድ አልቻሉም፡፡ ስለዚህም እያፈገፈጉ እርምጃ በእርምጃ በመከላከል የሁለት ሰዓት መንገድ ሦስት ቀን እንዲወስድበት አደረጉ፡፡ የአካባቢው አርበኛ እየተባበራቸው ቁጥራቸው እስከ አርባ አምስት ደረሰ፡፡ አርበኛው በትንንቅ አንድ መትረየስ ማረከ፡፡ ያለማቋረጥ ከአፋፍ ላይ የሚተኮሱት የጣልያን መድፎች አንዳች ፍንዋት አላስገኙም፡፡ በዚህ ታላቅ ትንቅንቅ ስለተጠመደ ጠላት ከአሰበበት መድረስ ሳይቻለው ቀረ፡፡ ወደኋላው ተመልሶ አድ ረመጥ ገባ፡፡ አርበኛው ሁለት ሻምበሎች፣ አንድ መቶ አለቃ፣ አንድ ሃምሣ አለቃ ከብዙ ወታደር ገደለ፡፡ ሁለት መትረየስና ሠላሳ አምስት ጠመንጃ ከበርካታ ጥይት ጋር ማረከ፡፡ መትረየስ ለመንጠቅ በመተናነቅ በቻ ስምንት ጀግኖች ወደቁ፡፡ ሌሎች ብዙዎች በፍልሚያ ላይ ሞቱ፤ አገሩ ግን ከጥፋት ዳነ፡፡

ወልቃይት፣ አድ ኮከብ በተደረገው ጦርነት ለደረሰበት ውርደት፣ ሰላማውያን ሰዎችን እንደ ማካካሻ የመፍጀት ሥራው ሳያዋጣው ቀረ፡፡ አዲስ ጦር በማምጣት፣ በታማኝ የወልቃይት ሰላዮች እየተመራ የአዲገርትየን ቁልፍ በር አርበኞች ሳይሰሙ አልፎ ምድረ ወይዘሮ ደረሰ፡፡ ለአርበኛው ዱብ ዕዳ ሆነበት፡፡ ደግሞም መሪው ልጅ ደስታ ማሩ ታመው ነበርና፣ ለጊዜው ተደነጋገረ፡፡ ሆኖም ልጅ ደስታ በቶሎ ተነስተው የአዋጊነት ሥራቸውን ያዙ፡፡ የጠገዴ፣ የደለሎ አርበኛም ለዕርዳታ ደረሰ፡፡ አባ ብሩ፣ አባ ገብራይ፣ አባ ወልደ ሚካኤልና አባ ገብረ ማርያም የተባሉ መነኮሳት በመስቀሎቻቸው ምድሪቱን እየባረኩ፣ የሚሸሸውን እየገዘቱ ከማህል ቆመው አዋጉ፡፡ የጣልያኑ ጦር አዝማች ራውጂኒ የተባለ ጉበዝ ኰሎኔል ነበር፡፡ እንደእሱ ያለ ተዋጊ አርበኞችን ገጥሞአቸው አያውቅም፡፡ የሠሩትን የጦር ብልሀት በመትረየስ እያስደበደበ ያፈርስባቸው ነበር፡፡ ቢሆንም አርበኞች ተስፋ አልቆረጡም፤ በርትተው ተዋጉ፡፡ ጦርነቱ ሰኔ 10 ቀን የጀመረ ምንም ሳያቋርጥ እስከ ሰኔ 21 ቀን 1930 ዓ.ም ድረ ስ ቀጠለ፡፡ ኮሎኔል ራውጂኒ ምንም ጀግና ቢሆን መሸሽ ግድ ሆነበት፡፡ አርበኞች የያዙትን የወለል በር በኃይል ሰብሮ ጠገዴ መስፍናት ገባ፡፡ በጦርነቱ ጣልያን ቢሸሽም ድል የእሱ እንደሆነ ተቆጠረ፡፡ አርበኞች ተጠቅተው ነበር፡፡ ከጠላት ያለቀው እጅግ ብዙ ነው፡፡ ከአርበኞች ወገን አርባ ስድስት ሞቱ፤ ሌሎች ብዙዎች ቆሰሉ፡፡ ምርኮም አልተገኘም፡፡

የአርበኞች ጥንካሬ ጣልያንን ስላስቆጣው፣ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት ሊደመስሳቸው አሰበ፡፡ የጉንደሩ፣ በትክል ድንጋይ፤ የአምባ ጊዮርጊሱ፣ በመረባ፤ የዳባቱ፣ በጀንዋራ፤ የደባርቁ፣ በቦዛ፤ የወልቃይቱ፣ በጠገዴ፤ የጭልጋው፣ በዋሊዳባ፤ ለመውረድ ማቀዱ በአሞራው ውብነህ ተሰማ፡፡ አርበኛውም በበኩሉ የጠላቱን ዕቅድ የማሰናከያ ዕቅድ አደራጀ፡፡ ዕቅዱም ጠላትን በየወጣበት በር እየወጉ ወደ የመጣበት መመለስ፤ ከተቻለም እየተከታተሉ ከምሽጉ በመግባት ማጥቃት፤ ይህንንም ለማድረግ እርስበርስ መረዳዳት ነበር፡፡ እንደ አቀደውም አደረገ፡፡ ከጉንደር የተነሣውን



የአርማጭሆና የከች በዱር አርበኛ፣ በደጃዝማች ብሬ ዘገየ መሪነት፤ የጀኔ ፈንቀራ አርበኛ፣ በደጃዝማች ጫኔ መሪነት፤ በአምባ ጊዮርጊስ የመጣውን የመረባ አርበኛ፣ በደጃዘማች ዋናው አንዳርጌ መሪነት፤ በዳባት የወረደውን፣ በደጃዝማች ጌታው ዘረፉ መሪነት፤ በደባርቅ የወረደውን የቆላ ወገራና የበዛ አርበኛ፣ በደጃዝማች ሀጐስ ተሰማ መሪነት፤ በወሊደባ የወረደውን የጭልጋና የጫቆ፣ የሣቤራ፣ የአዳኝ አገር አርበኛ፣ በግራዝማች ረዳ ተሰማ መሪነት፤ በዳዋ የወረደውን የዳዋ አርበኛ፣ በደጃዝማች በላይ መኰንን መሪነት ገጠመው፡፡

ከሜዳው ላይ ሲያቅተው፣ በሥልት እያፈገፈገ ከቆላው አስገባው፡፡ ሁለትና ሦስት፣ ሦስትና አራቱ በቡድን፣ በቡድን እየሆነ፣ ከዛፍ ላይ እየተሰቀለ፣ ከድንጋይ ውስጥ እየተቀረቀረ ተለቀቀበት፡፡ ከአንዱ ቦታ ሲያጠቃ፣ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወረ በነፍሱ ተጫወተበት፡፡ የጣልያን ጦር ኃይልና ስንቁን፣ መሣሪያውን ሲጨርስ ወደየመጣበት ተመለሰ፡፡ በተለይ በበዛ የወረደው ግን፣ ድብል ገሣ ከተባለው ቦታ ላይ ሠፍሮ፣ እስከ መስከረም ድረስ ሲዋጋ ቆይቶ፣ የማይዘልቀው መሆኑን ሲረዳ ጥሎ ሄደ፡፡ አገሩ ከጥፋት ዳነ፡፡ ከጠላትም፣ ከአርበኞችም ወገን ብዙ ሰው ሞተ፡፡

ሃያ አምሰተኛ፣ ሰባ ሰባተኛና አርባ ስድስተኛ ተብሎ የተመደበው የጣልያን መደበኛ ጦር፣ አርበኞችን ለማጥፋት በአራት ተከፍሎ ዘመተ፡፡ አርበኛውም በአራት ቡድን ተዘጋጅቶ፣ አማኒት ላይ ሰኔ 22 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው፡፡ ሁለት ቀን ሙሉ ወግቶ፣ ብዙ ወታደር ገድሎ፣ ወደ መጣበት መለሰው፡፡ ቦታው ስለተመቻቸው አርበኞች፣ እምብዛም አልተጐዱም፡፡ ሁለት አርበኞች ሲሞቱ አንድ ሰው ቆሰለ፡፡

ደብረ ታቦር የነበረው የጣልያን ሠራዊት የጭካኔ ሥራውን በሕዝብ ላይ ለመሥራትና አርበኞችን ለመደምሰስ፣ የአምስት ወር ስንቅ ይዞ ከደብረ ታቦር ሰኔ 21 ቀን ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህ ሁኔታ ከባድ ስለሆነ፣ አርበኛው ከየአለበት ተጠራርቶ ተሰበሰበ፡፡ የነገሴና የጋይንት፣ የፋርጣ አርበኛ ለሠርግ እንደተጠራ በደስታ ወጣ፡፡ ጠላት አሸማ ከተባለው ኮረብታ ላይ መድፍ እንዳይጠምድ ተከላከለ፡፡ የቤገምድር አርበኛም ደረሰ፡፡ ጠላትም ኪና ከተባለው ቦታ ተነስቶ፣ ፍቼ ከተባለው ቦታ ከነበረው ወገኑ ጋር ተቀላቀለ፡፡ በዚህ ጊዜ ጦርነቱ በረታ፡፡ ከከባድ ውጊያ በኋላ የጠላት ጦር ሽሽት ጀመረ፡፡ ምሽት ገላገለው፡፡ በበነጋታው ሰኔ 22 እና ሰኔ 23 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ ሰኔ 24 እና ሰኔ 25 ቀን 1930 ዓ.ም ቀንም ውጊያው ሳይበርድ ሰነበተ፡፡ የቤገምድር አርበኞች ለእርዳታ የደረሱ ቢሆንም፣ አዛውር የነበረውን ምሽጉን ማስለቀቅ አልተቻለም፡፡ ጣልያንም ከምሽጉ ወጥቶ መንቀሳቀስ አልቻለም፡፡ ከጠላት ወገን ያለቀው ወታደር በጣም ብዙ ነበር፡፡ በአዛውርና በፍቼ ከሰኔ 22 እስከ 26 በተደረገው ጦርነት፣ ሃምሣ ሦስት ታዋቂ አርበኞች መሞታቸው

ተዘግቦአል፡፡ በመጨረሻም ጣልያን ሰኔ 26 ለ27 አጥቢያ ሌሊት ሸሽቶ ደብረ ታቦር ገባ፡፡ አርበኞች አልጠረጠሩም ነበርና ጉዳት አላደረሱበትም፡፡

ጦርነቱን ለማፋፋም ባንዳውን ማስታገስ አስፈለገ፡፡ ባንዳውን ለማስታገስ የሚቻለው ደግሞ፣ እጅጉ አያሌው ሲካክም ሆኖ ተገኘ፡፡ ስለዚህ በስምንት የጎበዛዝት አለቆች የሚመራው ጦር በህብረት መከረ፡፡ እሺ ቢል በፍቅር፣ እምቢ ቢል በጦር የእጅጉ አያሌውን ትብብር ለማግኘት ተወሰነ፡፡ የአዝማቾቹ አለቃ የነበሩት አቶ ጊዜ በሀሳቡ ተስማምተው እንቅስቃሴ ተደረገ፡፡ የአርበኛው ቀዳሚ ጦር ደራ ሰኒ ከተባለው ቦታ ሲደርስ ከጠላት ጦር ጋር በ1930 ዓ.ም ተገናኝና ተኩስ ተከፈተ፡፡ ድብልቅልቁ ወጣ፡፡ አርበኛው በከፊል ሽሽት ጀመረ፤ ገሚሱ ቆሞ ተዋጋ፡፡ ጠላትም የነበረበትን ቦታ ጥሎ ፈረጠጠ፡፡ ነገር ግን አቶ እጅጉ አያሌውን መያዝ ሳይቻል ቀረ፡፡ ከጠላት ወገን በርካታ ባንዳ ሞተ፡፡ ከአርበኞች ሦስት ጀግኖች ወደቁ፡፡

ጣልያን ጉራዲት የተባለውን ቦታ ለመያዝ፣ ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ፡፡ አርበኞች የጉራዲት መያዝ ሥራቸውን ወደ ኋላ የሚገታባቸው ስለሆነ፣ ተቃወሙ፡፡ የዘመተውን የጠላት ጦር በ1930 ዓ.ም ወለላ ባሕር ላይ ገጥመው አጥብቀው ተዋጉት፡፡ ቢሆንም ጠላት በኃይል ጥሶ ገባ፡፡ ጉራዲት ላይ ጠንካራ ምሽግ ሠራ፤ የአይሮፕላን ሜዳም አዘጋጀ፡፡ ነገር ግን ሊጠቀምበት አልቻለም፡፡ አርበኞች በየቀኑ ወጉት፤ በጥይት ነዘነዙት፡፡ ጠላት ሲሰለቸው፣ በዚያው በመሸገበት ዓመት ጥሎ ደብረ ታቦር ገባ፡፡ በተደጋጋሚ በተካሄዱት የሽምቅ ውጊያዎች፣ ስምንት አርበኞች ሞቱ፤ ሌሎች አራት ቆሰሉ፡፡

ጣልያን መፈናፈኛ ለማግኘት፣ የአርበኞችን ኃይል መቀነስ አስፈለገው፡፡ በለሣ ላይ ደጐማ ካለው ምሽጉ ብዙ ባንዳና መደበኛ ጦር አዘመተ፡፡ በአርበኛውም ላይ በ1930 ዓ.ም ተደጋጋሚ አደጋ ጣለ፡፡ ቢሆንም አርበኛው በፈጣን እንቅስቃሴ ራሱን ከጥቃት እያዳነ መልሶ ወጋው፡፡ ጣልያንም ሸሽቶ ከዚያው ከምሽጉ ተከተተ፡፡ ደጎማ ላይ የነበረው የጣልያን ጦር እንደገና ተንቀሳቀሰ፡፡ አርበኛው ነሐሴ 11 ቀን 1930 ዓ.ም ከምሽጉ ብዙም ሳይርቅ ገጥሞ፣ አዛዡን አቁስሎ አባረረው፡፡ ብዙ መሣሪያም ተማረከ፡፡

አርበኛው በተደጋጋሚ በተካሄዱት ውጊያዎች ስለቀናው፣ እርምጃ በርምጃ ወደ ጐንደር ከተማ እየተቃረበ ሄደ፡፡ አርበኞች ከምሥራቅ በኩል በከተማይቱ ላይ አደጋ ለመጣል እንደሚችሉ ስለገባው፣ ሁኔታው የሚያሰጋው ሆነበት፡፡ ስለዚህ ጣልያን አምባ ማልዲባና ከተባለውና ከሌሎችም ጉብታዎች ላይ መድፍ ጠምዶ ይደበድብ ጀመር፡፡

ሁኔታው በእንዲህ እንደአለ ልጅ /ደጃዝማች/ አሰጋኸኝ አርአያ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወረቀት ይዘው በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም ደረሱ፡፡ ይህ አጋጣሚ በአንድ ወገን የአርበኛውን ልብ ሲያደነድን፣ በሌላ ወገን የአርበኞቹን



አያያዝ የሚያስረዳ ፅሑፍ ለዓለም መንግሥታት ማህበር እንዲቀርብ በማድረጉ፤ የጣልያንን ውሸተኛነት በዓለም ህብረተሰብ ፊት ለማረጋገጥ አስቻለ፡፡

በደጃዝማች ዋናው ተሰማ የሚመራው አርበኛ ነሐሴ 25 ቀን 1930 ዓ.ም ጭህራ በነበረው ጣልያን አደጋ ጣለ፡፡ ጣልያንም አልበገርም ብሎ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት የፈጀ ጦርነት ተካሄደ፡፡ በመጨረሻው ጣልያን አካባቢውን ለቅቆ ጐንደር ገባ፡፡ በጐንደር የተካሄደው የ1930 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ፡፡ ውሎም ሳያድር የ1931 ዓ.ም ተወጠነ፡፡

መስከረም 7 ቀን 1931 ዓ.ም የደንብያ አርበኞች ወቀራኮ ከተባለው ቦታ ሊያጠፋቸው የመጣውን የጠላት ጦር ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት ድል አድርገው ወደ መጣበት መለሱት፡፡ ሆኖም ጣልያን እስከ ምሽጉ እየሄዱ መውጋት በአርበኞች ላይ ጉዳት አመጣ፡፡ ሙጃ አንቆሽ የነበረውን ምሽግ ለማጥቃት የተደረገው ሙከራ በዚህ ምክንያት ሳይሳካ ቀረ፡፡ ስለዚህ ፊታውራሪ በረደድ አስፋው እንታረቅ የሚል መልዕክት አስተላለፉ፡፡ ጣልያንም እውነት መስሎት ሰማይ አፋፍ ከነበረው ምሽጉ ወጣ፡፡ ከተመቸ ቦታ ሲደርስ አርበኞች ከፊት ከኋላ መስከረም 12 ቀን 1931 ዓ.ም ከበው ጠዘጠዙት፡፡ ጣልያን ሸሽቶ ከምሽጉ ገባ፡፡ ምርኮው ያማረ ሆነ፡፡

መስከረም 14 ቀን 1931 ዓ.ም ቤዛሆ ላይ ጦርነት ተደረገ፡፡ ነገር ግን ምንም ያህል ሳይዋጋ ጠላት ወደ ኋላው ተመልሶ አይከል ከተማ ገባ፡፡

በአማራ አገረ ገዥ፣ በጄነራል ማዜቲ የሚመራ ጦር ጥቅምት 25 ቀን 1931 .ዓ.ም ጀምሮ ተንቀሳቀሰ፡፡ ስምንት ቀን ሙሉ ሳያቋርጥ ተጉዞ አምባ ጊዮርጊስ ሠፈረ፡፡ ከዚህ በኋላ የጦር አዛዡ ከጐንደር ሲነሳ ሊሸኘው በትዕዛዝ ለወጣው ሕዝብ ፎከረ፡፡ የኢጣልያንን መንግሥት የሚቃወመውን ሕዝብ ሥሩን ነቅሎ ዳግመኛ እንዳያቆጠቁጥ እንደሚያደርገው ገለፀ፡፡ እንቁላል፣ ዶሮ፣ ወተት፣ እንጀራ እየያዘ የቀረበውን ሕዝብ እያስፈጀ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ በበለሣ አንድ መቶ፣ በአይበ ሰባ ሰላማውያን ስዎች ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል ፈጀ፡፡ ማርያም ውሃ ላይ አንድ አርበኛ ብቻውን ገጥሞ የቻለውን የጠላት ወታደር ረፍርፎ ሞተ፡፡ ምንም ከአቅም አንፃር ጣልያንን መክቶ ለመያዝ ባይችል በደጃዝማች ዳኘው የሚመራው አርበኛም ወጋው፡፡ በጠቅላላው ሃምሣ ሰባት አርበኞች መውደቃቸው በታሪክ ተመዝግቦአል፡፡ ከእነሱም ውስጥ አራት ካህናት፣ ሦስት ሴት መነኮሳት ነበሩ፡፡ ይህንን ያህል የጭካኔ ሥራም አካሂዶ ጄነራል ማዜቲ ውጤት ሳያገኝለት ቀረ፡፡ እራሱም ከሹመቱ ተሽሮ፣ ጄነራል ሉዊጂ ፍሩሺ ተሾመ፡፡

ጥቅምት 16 ቀን 1931 ዓ.ም በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ የሚመራው አርበኛ ጣልያንን እንፍዝራዝ ላይ ወግቶ ድል አድርጐ፣ ዘርፎ አባረረው፡፡ ጠላት የሀገር ማጥፋት ሥራውን ቀጠለ፡፡ አርበኞች ተሰባበስበው በህብረት በለሣ ጉለና ላይ ወግተው አባረሩት፡፡ የጣልያን አመጣጥ እብናትና ሊበን

ለማጥፋት ነበር። ድል ከአደረጉት በኋላ የሚሸሸውን የጠላት ወታደር አርበኛው ከህዳር 28 እስከ ታህሣሥ 5 ቀን ድረስ ያለማቋረጥ ከበለሣ ጉለና እስከ አርብ ድረስ እያባረረ ወጋው።

በኮሎኔል አንጀሊኒ የሚመራ ጦር ከደብረ ታቦር ተነስቶ ተንቀሳቀሰ። ጥፍርና አንበሳ በር ሲደርስ፣ አርበኛው ጦርነት ገጠመው። በአንድ ኮሎኔልና በሁለት ሻምበሎች ከሚመራው ጦር አንድም ሳያመልጥ በአርበኞች እጅ ተደብድቦ እንደወጣ ቀረ። አንዱ ሲያልቅ ጠላት ሌላ ጦር እየተካ እምብዛም እረፍት ሳይኖር ውጊያው እስከ ህዳር 7 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። በዚህ ጦርነት ከተማረኩት መሣሪያዎች ዋነኛው በለሣ ላይ የተማረከው መድፍ ነበር። እሱም በአርበኛ እጅ እየተተኮሰ የጠላትን ምሽግ ለማፍረስና ለማቃጠል በጣም ረድቶአል። ጠላት በአካሄደው የአይሮፕላን ድብደባ የክልቢ አቦ፣ የጅማ ጊዮርጊስ፣ የጉልቶች ተክለ ሃይማኖት፣ የአብናት ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል።

አርበኞች ጣልያንን የውሂ ከተባለው ቦታ በህዳር ወር 1931 ዓ.ም ገጥመው በመውጋት ድል አድርገው ወደ መጣበት መለሱት። በዚህ ጦርነት ላይ የታየው አንድ አስደናቂ ነገር፣ ግራዝማች ረታ የተባሉት አርበኛ አትኩሮ ይመለከታቸው የነበረውን፣ አሥራቴ ጥሩነህ የተባለውን ባንዳ ተንተርሰውት መውደቃቸው ነው።

በዚሁ በ1931 ዓ.ም ጠላት በደጃዝማች ዳኘው የሚመራው አርበኛ ላይ አደጋ ጥሎ ለመደምሰስ ከደጎማ ተንቀሳቀሰ። አላጌ በር የነበረው አርበኛ ምሥጢሩን ቀደም ብሎ ደርሶበት ነበርና፣ ጉሉ ምሽግ ላይ ሳያስበው ገጠመው። ጦርነቱ ከጥዋት ሦስት እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ወሰደ። ከሩቅ የነበሩ አርበኞች ተኩሱን በመስማት ለእርዳታ እየመጡ ተሳተፉ። ከጠላት ወገን 25 ወታደር ሞተ፤ ሰባት ቆሰለ። ከአርበኞች ወገን ግን ሁለት ሞቱ፤ አንድ ቆሰለ።

በህዳር ወር 1931 ዓ.ም አጠቃላይ ስብሰባ ተጠራ። በየወረዳውና አውራጃው የነበረው አርበኛ ተወካዮችን ላከ፤ የቻለም መጣ። ስለ ጦር ሥልትና ጠላትን በበለጠ ለማጥቃት ስለሚቻልበት መንገድ ምክር ተደረገ። በምክሩም ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ነጥቦች ስምምነት ተደረገ።

1ኛ. በበጌምድር ያለውን ጠላት መደምሰስና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስኪመጡ የመረረ ትግል መቀጠል፣

2ኛ. የአንዱ ክፍል አርበኛ በጠላት ሲጠቃ ሌላው እንዲረዳ፣

3ኛ. ጀግንነታቸው ለተረጋገጠላቸው የአርበኞች መሪዎች ሹመት እንዲሰጥ።

በዚህ ስምምነት መሠረት ግራዝማች አሞራው ውብነህ ራስ አሞራው ውብነህ ተብለው ጠቅላይ አዛዥ ሆኑ። በእሳቸውም ሃምሣ ሁለት ደጃዝማች፣ ዘጠና ስምንት ፊታውራሪዎች ተሾሙ። ሹመቱ የተሰጠው በአርበኛው ምርጫ



ሲሆን፤ የምርጫው መሥፈርት ከትልቅ መወለድ ብቻ አልነበረም። አብሮት የተሰለፈው ሠራዊት ብዛት፣ ሠራዊቱን የሚያስተዳድርበት ጥረት፣ የተጎዳን የሚረዳ፣ ለጋሥ፣ ልበ ሙሉና ደፋር መሆን ነበረበት። ለእያንዳንዱ ተሿሚ ሀገር እየተለየ ተሰጠው። የሥራ ኃላፊነቱ በጦር የተጎዳውን መርዳትና ተለይቶ የተሰጠውን አገር በጠላት አለማስደፈር ነበር። የዚህ ሹመት መስጠት የአርበኝነትን ሥራ በእጅጉ አጠናከረ። ለመሪዎቹ ክብርና ሞገስ ሰጠ። ጠላትን ደግሞ አስደነገጠው።

በአፀፋው ጣልያንም ሹመት ሰጠ። በእሱ በኩል ከተሾሙት ደጃዝማች አያሌው ብሩ ራስ ተባሉ። አሥራ ሰባት ደጃዝማች፣ ሦስት ከቫለር፣ አንድ ቢትወደድ፣ አንድ ጽራግማሠሬ፣ አንድ መልአከ ሕይወት፣ አምስት የአድባራት አለቆች በከፍተኛ ደረጃ ተሾሙ። ከእነሱም በታች ስድሳ አንድ ፊታውራሪዎች፣ አንድ አዝማች፣ አንድ አፈንጉሥ ነበሩ። የቀኛዝማች፣ የግራዝማችና የባላምባራስነት ማዕረግ የተሰጣቸው እጅግ ብዙ ነበሩ።

ለአርበኞች መሪዎች የተሰጠው ሹመት ሙቀትና ድምቀት ጣልያን ከሰጠው የበለጠ ሆነ። ጣልያን ሹመት ለመስጠት የተገደደው በአርበኞች በኩል የተሰጠውን ሹመት ለማርከስ አሥራ ሁለት ቀን ሙሉ ጦርነት አካሂዶ እንዳልተበገሩለት ካየ በኋላ ነበር።

ጣልያን ብዙ ሠራዊት ከጐንደር ሰብስቦና ከአሥመራ አስመጥቶ በአዲስ ኃይል አንቀሳቀሰ። በራስ ውብነህ የሚመራው አርበኛ ቦታ እየለዋወጠ ብዙ በማንከራተት ከአደከመው በኋላ፣ ዘመቻውን ትቶ ሊመለስ ሲዘጋጅ አርበኛው ዐዚያው በህዳር ወር 1931 ዓ.ም ጉረንክ ላይ አደጋ ጣለበት። ብዙ ወታደር ፈጅቶ፣ ካሚዮኖች እኩሉን አቃጥሎ እኩሉን ዘርፎና ሰባብሮ ወደ አምባ ጊዮርጊስ አባረረው።

ጣልያን ገበሬውን እያስገደደ ማዝመቱን ትቶ፣ መደበኛ ውታደር ብቻ ያዘምት ጀመር። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የሚረዳው ጦሩን በካሚዮን ማንቀሳቀስ ሆነ። አርበኛው ይህንን ሲያይ መንገዱን መቁረጥ፣ ድልድዩን ማፍረሱን ያዘ። ይህ ደግሞ ለጦርነቱ ጊዜያዊ ጥቅም ቢሰጥም፣ ለሀገሪቱ ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል ሆነ። ስለዚህ ራስ አሞራው ውብነህ ተቃወሙ። “ጎዳናዎችንና ድልድዮችን ለመሥበር እጅህን አትዘርጋ” የሚል ትዕዛዝ ሰጡ። አርበኛው መኪናዎችን ወደ መሥበርና ማቃጠል ዞረ።

በአንድ ኰሎኔል የሚመራ ጦር ወደ ደጋ መልዛ ለመውጣት፣ ከአብናት ምሽግ ተነሣ። ጦሩ ከደጋው ላይ ከወጣ፣ ብዙ ጥፋት ሊያደርስ እንደሚችልና ለመከላከልም እንደሚያዳግት ታወቀ። ስለሆነም አርበኛው ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም ገጥሞ ከቀኑ 6 እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ወጋው። ጣልያንም በማግስቱ ተመልሶ ከወጣበት ምሽግ ተከተተ። በዚህ ጦርነት ገበሬው በሬውን እንደተጠመደ ትቶ፣ አርበኛውን ሲረዳና ከጐኑ ቆሞ ሲዋጋ፣ በሮችም ሞፈር ቀንበር ተሸክመው ሲንከዋረሩ ውለዋል። ጣልያን በበኩሉ ከጥር 1 እስከ 30

ድረስ አካባቢውን ቁጥራቸው እስከ 12 በሚደርስ አይሮፕላኖች ሳያቋርጥ፣ በየቀኑ ሲደበድብ ሰነበተ። በድብደባው የመበላ ኢየሱስና የግብጣዊት ማርያም ቤተ ክርስቲያኖች ተቃጠሉ።

ጦርነቱ እየተጋጋመ ሄደ። ግለቱ ጠላትን ለበለበው፤ የውስጥ እግር እሳት ሆነበት። በየሄደበት የሚፈጀው፣ በየመንደሩ የሚያስለፍፈው የሽንገላ ወሬ፣ ምንም ፋይዳ ሳያገኝለት ቀረ። ስለዚህ የእርቅ ሥራ በገሐድ ለማካሄድ አሰበ። ከጣልያን ይህንኑ ሥራ የሚያካሂዱ ሹማምንት መጡ። መጋቢት 19 ቀን 1931 ዓ.ም ከአማራ አገር የፖለቲካ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ ከጎንደር ከተማ አዋጅ ወጣ። የአዋጁ ፍሬ ነገር፤

1ኛ. በእሪም በእሪሙ አምሾውን እንዲቀበል፣

2ኛ የመስቀል መሬቶች እንደቀድሞው እንዲሆኑ፣

3ኛ. ለተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት ደመወዝ እንዲሰጥ፣

4ኛ. የአብያተ ክርስቲያናት አለቆች የሚሾሙት በመንግሥት እንዲሆን፣

5ኛ. ሊቃነ ካህናት የመቀጮና የዳኝነት ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ ነበር።

ይህንኑ የሚያስፈፅሙ፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው ሹማምንት በአገሩ ላይ ተሰማሩ። ይህ አዋጅ በሕዝብ ላይ አፍራሽ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል በጉልህ በመታወቁ፣ አርበኛው በየግንባሩ ጦርነቱን አጋጋመ። ጣልያንም የሰላምና የማረጋጋቱን ሥራ በአንድ እጁ፤ ከአርበኞች ከሚደርስበት ጥቃት መከላከልን በሌላው እጁ ያዘ። በዚህም መሠረት ሚያዝያ 2 ቀን 1932 ዓ.ም አርበኞችን ለማጥቃት ከአይከል ምሽግ ተንቀሳቀሰ። አዋጅ ከአወጣና የሰላም ቡድን ከአሠማራ በኋላ ጥቃት መሠንዘሩ፣ ለጤና አልነበረም። አርበኛው መቀነት ከተባለው ቦታ ገጥሞ ጥቃቱን በጥቃት በመመለስ ወደ መጣበት ምሽግ አባረረው።

አርበኞች በበኩላቸው ከጠላት ጎን የቆሙትን ኢትዮጵያውያን ለማስከዳት ልዩ ጥረት አደረጉ። ከአቀወት ምሽግ ብዙዎች መትረየስና ሌላም መሣሪያ እንደያዙ፣ ጠላትን ከድተው ከአርበኞች ጋር ለመቀላቀል አሰቡ። ምሥጢሩን ጠላት ደርሰበት። ነገር ግን ከብዛታቸውና ከዝግጅታቸው የተነሣ ፈራ። ስለዚህ እሱ ከኋላ ደጀን ሆኖ በቆመበት ውጊያ፣ በደጃዝማች ታየ ጉላ አዛዥነት በአርበኞች ላይ አዘመታቸው። አብዛኛው አርበኛ ከሰቲት ወደ ጎንደር የሚያመጣውን የመኪና መንገድ ለመሥበር ሄዶ ነበርና በአካባቢው የነበሩት ቁጥር ጥቂት ነበር። ቢሆንም አርበኞች በቆራጥነት ገጠሙት። ባንዳውን ለማስጨረስ ደንበኛው የጠላት ጦር ከውጊያ ሳይገባ በደጀንነት ቆየ። ባንዳው ቀደም ብሎ እንደመከረው ከጠላት ከድቶ ወደአርበኞች መቀላቀሉን ትቶ ተዋጋ። ቀኛዝማች አምይም ተስፋጽዮን የተባሉት አርበኛ ሦስት ወታደር ገድለው ሞቱ። በየጊዜው ልብ የሚነኩ ጽሑፎች በማውጣትና በቃል ምክር በመስጠት አርበኝነቱን ያጠናከሩ ነበሩና፣ ሞታቸው ጉዳት አስከተለ።



ሚያዝያ 18 ቀን 1931 ዓ.ም ሥልሚና ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደረገ። በዚህ ጦርነት አንዳርጌ ወርቅነህ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማረከ። ግብሩ ሲመረመር 12 አርበኞች ገድሎ፣ ራሳቸውን ቆርጦ ቀንዲር በመውሰድ ለጣልያን ግዳይ እንደጣለ ስለተረጋገጠበት፣ በስቅላት ሞተ።

በጦርነቱ በኩል እንዲህ ሲደረግ፤ በሰላሙ በኩል የጠላት ስብከት በተጠናከረ ሁኔታ ቀጠለ። "...ሽማግሌው በሰላም እንዲቀበር፣ ሕፃናት እንዲያድጉ፣ ቤታችሁና ቤተክርስቲያናችሁ እንዳይቃጠል፣ ቀዬአችሁ እንዳይጠፋ ለጣልያን ግቡ እመኑ..." እያሉ መልዕክተኞቹ ሰበኩለት። የስብከቱን ሥራ በግብር ለማጠናከር ሁለት ኮሎኔሎች፣ አንድ ሻለቃና ሁለት መቶ አለቆች ያሉበት ቡድን በየቦታው እየዞረ "...ጦርነት ይቁም።...በመኪና ላይ አደጋ መደረጉ ይቅር።...የመንገድ ሠራተኞች በእናንተ እየተጠበቁ ይሥሩ።..." ብሎ ማነጋገር ጀመረ፤ አንዳንዶችም ተቀበሉአቸው። ቡድኑ ደጃዝማች ዳኘውን ለማነጋገር ከደብረ ታቦር በ1931 ዓ.ም በለሣ ደረሰ።

ይህ ሁኔታ ከቀጠለ አርበኞች የቋጠሩት ቁጥር ተፈታ ማለት ሆነ። ያም ሆኖ እያለ፣ ቡድኑ በለሣ ሲደርስ ተቀባይ በፊታውራሪ ደምስ ኃላፊነት ተላከ። አርበኛው እንግዶቹን አጅቦ ወረሐላ ገበያ ላይ ሲደርስ፣ በቀኛዝማች ኃይሉ እጅ ሌላ መልእክት ደረሰ። መልእክቱም እንግዶቹ "...በሰንሰለት ታሥረው ይቅረቡ" የሚል ነበር። ደብዳቤው ከተነበበ በኋላ አርበኛው ከበቅሎዎቻቸው አስወርዶ በሰንሰለት አሥሮ እየነዳ ከደጃዝማች ዳኘው ተሰማ ችሎት አደረሰላቸው።

መልእክተኞቹ ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ተፈቀደላቸው። ኮሎኔል በኔሊ "በእናንተና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጥል ቀርቶ ሁለቱም ወገን በስምምነት ሆኖ እንዲተዳደር..." አለ። ከዚያም አያይዞ የኢጣልያን መንግሥት ቢፈልግ በለሣን በአንድ ቀን ለማጥፋት እንደሚችል ገልፆ ደነፋ። ደጃዝማች ዳኘውም "...በእናንተና በእኛ መንግሥት መካከል ያለው ጥል ከጥንት ጀምሮ ተያይዞ የመጣ በመሆኑ እርቁ በእናንተ የሚወሰን አይደለም..." ብለው ከእሥር ቤት ከተቱአቸው። ኮሎኔል አንጀሊኒ ስቅስቅ ብሎ እንደ ሕፃን አለቀሰ። ለአርበኛው፣ እብናት ላይ ተሰብስቦ ነገሩን እንዲሰማና ውሣኔ እንዲያደርግ ጥሪ ተላለፈ።

በቀነ ቀጠሮው የቤጌምድር አርበኛ ተሰበሰበ። በምዕራብ ክፍል ያለው እዚያው በአለበት ጉዳዩን አይቶ ይገደሉ የሚል ውሣኔውን ላከ። ደጃዝማች ብሬ ዘገየ ገዳይ ጠፍቶ እንደሆነ ወደ እኛ ላኩአቸው የሚል የቁጣ መልእክት አስተላለፉ። ጉባኤው ነገሩን መረመረ። ለሰላማዊ ነገር የመጡ እንጂ በጦርነት ያልተማረኩ ስለሆነ ሊገደሉ አይገባም የሚለውን የደጃዝማች ሞላ መሻሻን አስተያየት በድምጽ ደገፈ። የእርቁን ጉዳይ ከፈለገ ጣልያን የደብረ ታቦርን፣ የይፋግን፣ የጣራ ገዳምን፣ የደጎማን፣ የአምባ ጊዮርጊስን ጦር አንስቶ ወደ ጎንደር እንዲወስድ፤ በእነዚህ ምሽጎች የሚገኘውንም መሣሪያ ለሀገር

መጠበቂያ እንዲሆን ለአርበኞች እንዲያስረክብ ቆረጠ። ይኸው ቃል የእርቅ ሥራ ለማካሄድ ተልኮ መጥቶ አብሮ በተማረከው፣ በሻለቃ ኺኮኒ እጅ እንዲላክለት ተወሰነ። እሥረኞች በለሣ ደራማርያም ከነበረው እሥር ቤት ገቡ።

ለጣሊያኑ የአማራ አገር ገዥ መልእክት ደረሰው። የአርበኛው ብዛት አሥራ ሁለት ክፍለ ጦር እንደሚሆን ተነገረው። እሱ ግን የቀረበለትን ሃሳብ በቀጥታ ሳይቀበል፣ የጠየቃችሁት ውል የሚፈፀመው የተያዙት አምስት ሹማምንት በተለቀቁ ጊዜ ነው አለ። አርበኞች የጣልያንን ቃል አምነው እሥረኞቹን ለመልቀቅ አልፈለጉም፤ ነገር ተካረረ። በመሀል ለአስታራቂነት የመጣው ሻለቃ ወደሀገሩ ተመልሶ ሄደ።

የአማራ አገር ገዥ፣ ጄነራል ፍሩሺ ግንቦት 12 ቀን 1931 ዓ.ም አዋጅ አወጣ። አዋጁ ኢጣልያ እርቅ ቢጠይቅ፣ አርበኞች እምቢ ብለው የእርቅ ሥራ ለመሥራት የተላኩትን ሹማምንት እንደ አሠሩአቸው ከዘረዘረ በኋላ፣ የኢጣልያ መንግሥት የኃይል ሥራ ለማካሄድ መገደዱን የሚያስረዳ ነበር፤ አያይዞም ሕዝብ ለደጃዝማች ዳኘው እሥረኞችን እንዲለቁ እንዲመክር፣ ምክሩን ካልተቀበሉት ወደ ኢጣልያ ሠራዊት እንዲጠጉ የሚያሳስብ ነበር። ለእስከዛሬውም ምሕረት እንደተሰጠ ያረጋግጥ ነበር። በዚህ ጊዜ የጐንድ ተክለሃይማኖት ካህናት እሥረኞች እንዲለቀቁ መስቀል ይዘው ቆሙ። ነገር ግን ተቀባይነት ሳያገኙ ቀሩና ጦርነቱ ቀጠለ።

ጣልያን በአማራ አገር ያለውን ጦር አስከትቶ ተንቀሳቀሰ። አሥራ ስድስት ባታልዮን ጦር፣ ፈረሰኛ ጭምር አሰለፈ። አርባ የጦር አይሮፕላኖች አስነስቶም አካባቢውን የቦምብ ውርጅብኝ አወረደበት። እግረኛው በእግር፣ ፈረሰኛው በፈረስ ሀገር የማጥፋት ሥራውን አካሄደ። በጄነራል ቶሊቲ የሚመራው ይህ ጦር ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ፣ አዋቂ ሳይለይ ሕዝቡን ፈጀው። ደብረ ከተባለው ቀበሌ ብቻ ዘጠና ስድስት ሰው ገደለ። ሌላው አልተቆጠረም። የዳሑጭ ማርያምን፣ የአረብሰና በአታን፣ የእርብአረገ ጊዮርጊስን፣ የሣንኪ ኪዳነ ምህረትን፣ የመንቲ መርቆሬዎስን፣ የአርባዕቱ እንስሳን፣ የደብረ ተክለሃይማኖትን፣ የጥሊ ኢየሱስን፣ የዛራይ ሰሆ ማርያምን አብያተ ክርስቲያናት አቃጠለ። የጦር ክብደት ስለአስበረገጋቸው፣ ወደ በለሣ የሚያወርደውን በር ይጠብቁ የነበሩት አርበኞች አወላወሉ። ቆራጥ እርምጃ ባለመውሰዳቸው እሥረኞቹ አመለጡ።

ከዚህ ሁኔታ ትምህርት ሊወሰድበት ስለሚያስፈልግ የታሪክ ጥሬ ዘሩ ብቻ ተነግሮ ሊታለፍ አይገባም። ሊተችበት ይገባል። ፍርዱ ትክክል ነው፤ በሰላም፣ ለሰላም የመጡት ሰዎች ሊገደሉ አይገባም። እንኳን በሰላም የመጡትን፣ በጦር ሜዳ የተማረኩትንም ቢሆን ከተያዙ በኋላ መግደል አይገባም። በእበናት ጉባዔ የተሰጠው ፍርድ ትክክል ነው የተባለው ስለዚህ ነው።



ነገር ግን የእርቁ ሃሳብ ከባድ ነበር። አምስት ምሽጐች እንዲለቀቁ ማድረግ (መጤቅ) ቀላል አልነበረም። በዚህ ጄነራል ፍሩሺ ቢጨነቅ አግባብ አለው። በዚያ ላይ ደግሞ ጦሩ መሣሪያውን እንዲያስረክብ መጠየቁ ነገሩን በይበልጥ እንደአከበደው ሊታመን ይገባል። የጉንድ ተክለ ሃይማኖት ካህናትን ቃል አለመስማቱ ሌላው ስህተት ነበር። ከጣልያኖቹ ጋር አብረው የመጡ ኢትዮጵያውያን ሳይኖሩ አልቀሩም። ስለእነዚህ ሰዎች አንዳች አልተደረገም። ሀገራቸውን ክደው፣ የጠላትን ዓላማ ለማስፈፀም በመቆማቸው፣ እንግዲያው እነሱም በአብናት ጉባኤ ፊት ሊቀጡ በተገባ ነበር። ይህ አለመደረጉ ጉድለት መኖሩን ያሳያል። የስህተቱ መደምደሚያ ጠላት እርቁን አፍርሶ ጦርነት ሲያነሳ፣ በእሥረኞቹ ላይ አንዳች እርምጃ አለመወሰዱ ነበር። የለቀቁአቸው ሰዎች በርግጥ ወገናቸውን በድለዋል። ሕዝብ ምንም ፍንዋት በሌለው ነገር ማለቁ ያሳዝናል። በምክሩ ሽማግሌ ያልተቀመጠበት፤ የእሥረኞቹ ጥበቃም፣ ጀግና ያልቆመበት የሚያስመስል አሳፋሪ ሥራ ተሠራ።

ጉዳዩ በእልህ ሳይሆን በፊሊጥ ቢያዝ ኖሮ፣ የተሻለ አማራጭ በተገኘ ነበር። እነዚህም አማራጮች፤ አንድም ፍርዱን አስፈርዶ የዕርቅ መደራደሪያ ነጥቦችን በማስፈፀም አቅም ደረጃ መጠን ማድረግ፤ አለበለዚያ ደግሞ የፍርዱን ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ በአመክሮ በሰላም መልቀቅ። ሌላው አማራጭ፦ አንድም ፍፃሜው እስኪታወቅ ድረስ እሥረኞቹን ወደ ሌላ ቦታ፤ ለምሣሌ ወደ ጐጃም ማዛወር፤ አለበለዚያ ደግሞ ጦርነቱ ቁርጥ ሆኖ በተነሳ ጊዜ፣ መግደል ነበር።

በጦርነቱ ግንባር ግን አርበኞች የሠሩት ሥራ አቃቂር የሚወጣለት አልነበረም። ጨውጫዊት ላይ አርበኛው በዚሁ በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም የጣልያንን ጦር ከሌሊቱ ከአሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ወጋው። እንደገና ደግሞ በሁለተኛው ቀን በሁለት ክፍል ተመድቦ ገጠመው። አንዱ በጠላት ላይ አደጋ ጥሎ አንድ ሻለቃና አንድ አነጋጋሪ ገደለ። አነጋጋሪው የሞተው ጥይት በአፉ ገብታበት መሆኑ አስደነቀ። ጠላትም በበኩሉ ከልጅ ዮሐንስ ኢያሱ አሽከሮች ዘጠኙን ገድሎ፣ ራሳቸውን ቆርጦ፣ ደጎማ ወሰዶ ጊጤ ተጫወተበት።

የእርቁ ድርድር መውደቅ፣ ጠላት የኃይል ሥራውን ለመቀጠል ምክንያት ሆነው። ከጐንደር ሰባት ባታልዮን ጦር አንቀሳቀሰ። የፋርጣ፣ የመቀጥዋ፣ የስማዳ፣ የእስቴ አርበኞች ተጠራርተው አምጃ ላይ ግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ገጠሙት። ሳባት መዓልትና ሰባት ሌሊት ያለማቋረጥ ወጉት። የጠላት ጦር ወደ ደብረ ታቦር ሽሽቱን ሲቀጥል፣ አርበኞች እየተከታተሉ፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ እየሆኑ፣ በየጉጡ በጥይት ደበደቡት። ብዙ ወታደር ገደሉ። አንዳንድ የጠላት ወታደሮች እጃቸውን ለአርበኞች ሰጡ። ብዙ ምርኮም ተገኘ።

በጠገዴው የጦር ጐራ ደግሞ ሌላ መልካም ስራ ተሠራ። ጣልያን በግራዝማች /ቢትወደድ/ አዳነ መኰንን ላይ ግንቦት 25 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለ። አደጋ የጣለው ከሌሊቱ 11 ሰዓት በመሆኑ አርበኛው ራሱን ለማዳን ተበተነ። ወዲያው በሚተዋወቅበት ጥሪ ተሰብስቦ ሲነጋ ተንፋች ከምትባለው ቦታ ላይ ገጠመው። ቦታው ደጋና ውርጫማ ከመሆኑ ጋር እረግረግ ስለነበር ለአርበኛው አመቸ። አርበኛው በጥይት ሲጠዘጥዘው የጠላት ጦር ሽሹቱን ያዘ፤ አጋሰሱ ከእረግረጉ እየተዘረነቀ ቆመ። ስድሳ አጋሰስ ትጥቅና ስንቅ ተማረከ። ብዙ የጠላት ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም አራት መሪዎችና ሃምሣ ያህል ጀግኖች ወደቁ።

በሌላው ግንባር ደግሞ ጠላት ደጃዝማች ሰጥ አርገው ዋሴን ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። ሆኖም አርበኞች ካላሰበበት ቦታ ወግተው አባረሩት። የመጀመሪያውን ጦር አዛዥ የነበረውን ጣልያን ገድለው፣ ከወታደሩ የሚበዛውን ገድለው ሲያባርሩት ሌላ አዲስ የጠላት ጦር ደረሰ። እሱንም ከ4 ሰዓት በላይ ወግተው አባረሩት። የሞተውን ጣልያን ሬሣ ገደል ስለሰቀቁት የዳባቱ ገዥ መጥቶ ቢፈልግ አጣው። እንደገና ጥቂት የጠገዴ አርበኞች ተቃጥረው በመሄድ ዝዋ በተባለው ቦታ በነበረው የጠላት ጦር ላይ አደጋ በመጣል የተከናወነ ሥራ ሠሩ።

ከሣንጃ ጦርነት ሸሽቶ የተመለሰውን የጠላት ጦር አርበኛው አጋም ዱና ከተባለው ቦታ ገጠመው። ብዙ ጉዳትም አደረሰበት። ጫቅሌ አየለ የተባለ የ15 ዓመት ማርተጋሻ አንዱን የጠላት ወታደር ከኋላው ተንደርድሮ ከወገቡ ላይ ጨምድዶ ያዘው። በዚህ ጊዜ ሌላው አርበኛ ወታደሩን አነጣጥሮ በጥይት ስለመታው ትንቅንቁ አበቃና ልጁ መሣሪያውን ገፈፈ።

ደኅማ የነበረው ጣልያን በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ በሚመራው አርበኛ ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞች ለብዙ ሰዓት ተከላክለው መለሱት ነገር ግን አቶ በላይ ወንዴ የተባለ ጀግና ዘጠኝ ባንዳ ጥሎ ወደቀ። ለጠላት ጦር መሪ ሆኖ የመጣው መርዕድ መሸሻ ቆሰለ።

በአርበኛው ዘንድ ረሃብ ስለፀና፣ እህል ለመሸመት አንድ ቡድን በሰኔ ወር 1931 ዓ.ም ወደ ሱዳን ወረደ። አሜህራን ተሻግሮ እንደሠፈረ፣ የጣልያን ጦር ወሰን ጥሶ ገባ። በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ ቀኛዝማች መልኬ ዘለቀ እና፤ ከጠላት ወገን ደግሞ፤ ኢብራሂም ደውራ ሞቱ። የተረፉት አርበኞች በጋለባት በኩል ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገቡ።

በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም ወገራ ደንጉር በር ጣልያን በራስ ውብነህ ተሰማ ላይ አደጋ ጣለ። በልዩ ልዩ ሁኔታ ጦርነቱ ከሌሊት እስከ ምሽት ቀጠለ። ብዙ የጠላት ወታደሮችና ጥቂት አርበኞች ወደቁ። የጣልያኑ መሪ በጣቱ እየጠቆመ ለጌታው ሲያሳይ አርበኛው አነጣጥሮ በመተኮስ የቀሠራትን ጣቱን ከመካከልዋ በጠሰበት።



በአርበኛው ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣ ቀላል አልነበረም፤ ዓይነቱም የተለያዩ ነበር። ብዙ ሰው በጦርና በበሽታ ይሞታል። መድኃኒት የለም። ሀገሩ እየጠፋ ስለሄደ ምግብ አተተ። ቤቱ፣ ቤተክርስቲያኑ፣ ክምር ሳይቀር ይቃጠልበታል። ነገር ግን ከሀገሩ ነፃነት በስተቀር ምንም ዓላማ ለሌለው አርበኛ፣ ይህ ምንም ማለት አልነበረም። የሚፍጨረጨረው ገድሎ ለመሞት፣ ጥሎ ለመውደቅ ብቻ ሆነ። ሳይገድሉ መሞት፣ ሳይጥሉ መቁሰል እንደ መከነን ተቆጠረ። የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፅሞ የ1932 ዓ.ምቱ ተተካ።[7]

ከውጭ አገር፣ ከካርቱም በገደሪፍ በኩል፣ ኢትዮጵያውን ወደ ኢትዮጵያ ከሐምሌ ወር 1931 ዓ.ም ጀምሮ ገቡ። ከቡድኖች አንዱ በብላቴንጌታ ሎሬንዞ ትዕዛዝ፤ ሌላው ደግሞ በአቶ ሕይወት ኀደሩ የሚመራ ነበር። በክረምቱ በብዙ ቦታ ምክር ተካሄደ። እነዚህ ከውጭ አገር የተመለሱ ኢትዮጵያውያን አላማ በሦስት ይጠቃለላል። እነዚህም፦ በአርበኞች መካከል የመረዳዳትና የመተባበር መንፈስ መፍጠር፤ አርበኛው ሌላ መሪ ለማውጣት የነበረውን አዝማሚያ አስትቶ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መምጣት እንዲጠባበቅ ማድረግ፤ በኢትዮጵያ ጦርነቱ እንደቀጠለ መሆኑን ለዓለም ማህበር ለማስረዳት የሚያስችል ማስረጃ ማግኘት ነበሩ።[8] ይህ ከአውሮፓ በሱዳን በኩል የሚነፍሰው ወሬ የአርበኛውን ልብ አጠናከረው።

በአገር ውስጥ ግን ጣልያን የሀገር ማጥፋትና የሕዝብ መፍጀት ሥራውን አላቆመም፤ ያንኑ በመቀጠል መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። የጠላት ጦር በኰሎኔል አንጀሊኒ የሚመራና ብዛት ያለው ነበር። የዓርብን ወንዝ ተሻግሮ ከአጉበር በታች ያለውን ሰባቱን አገር አጠፋው። የመልዛ፣ የመቀጥወና የሐሙሳ ወንዝ አርበኛ በልጅ ዮሐንስ ኢያሱ እየተመራ በየወንዙ በየዳገትና ቁልቁለቱ እየቆረጠና እየነጣጠለ በጥይት ቆላው። ወቅቱ ክረምት ስለሆነ ወንዞቹና ጭቃው የጠላትን ጦር ብዙ አጠቃው። ዓርብ ወንዝ የወሰደው በጦር ሜዳ ከወደቀው አያንስም። በዚህም የጠላትን ጦር እንቅስቃሴ አርበኛው ወደ ኋላ ስለገታው፣ እስከ ህዳር ወር መንቀሳቀስ አልቻለም።

ሆኖም በእግር መንቀሳቀስ ሲያዳግተው፣ አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። ከሁለት ወር ያላቋረጠ ውጊያ በኋላ በነጭ ድንጋይ በኩል ዞሮ ቁስቋም ከተባለው ሥፍራ ህዳር 7 ቀን 1932 ዓ.ም ገብቶ ሠፈረ። አርበኛውም ወደዚያው ሄዶ አብናት ከተባለው ሜዳ ላይ ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ድረስ ወግቶ ወደ ቁስቋም መለሰው። ብዙ ምርኮ ስለተገኘ በአርበኞች ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። ጠላት በየአለበት መበታተኑ ለአርበኞች ጥቃት እንደ አጋለጠው በመረዳት ትልልቅ ምሽጎችን እያጠናከረ ተቀመጠ። ዘመቻ የሚያደርገውም ብዛት ያለው ጭር እያሠለፈ ሆነ። በዚህ

ምክንያት ጦርነት የሚያደርግባቸው ቦታዎች ተቀነሱ። ጊዜዎቹም አልፎ አልፎ ሆኑ። በአንፃሩ ግን የአይሮፕላን ድብደባውን አጠናከረ።

ቁስቋም የነበረው ጦር እንደገና ተንቀሳቀሰ። ሀሳቡ ወደ ደጋ መልዛ ለመውጣት ነበር። አርበኛው ደሪገ ከተባለው በር ላይ ገጠመው። ውጊያው ከቀኑ ስድስት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው በጠላት ላይ ጉዳት አድርሶ ብዙ ምርኮ አገኘ።

በጀነራል ጉሲቲ የሚመራ ጦር እንደ ልማዱ ከጐንደር ከተማ፣ ከደብረ ታቦር እንደዚሁም ከዋግና ከላስታ ብዙ ጦር አሠልፎ ተንቀሳቀሰ። እንቅስቃሴው በሦስት ረድፍ ስለነበር ቀላል አልነበረም። አርበኛው የእንቅስቃሴውን ክብደት፣ የጦሩን ብዛት መጥኖ በየቦታው እየከፋፈለ እየነጣጠለ ጠዘጠዘው። ከየካቲት 1 እስከ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ ያለማቋረጥ ሌት ተቀን ወጋው፤ ብዙ ጉዳትም አደረሰበት።

በዚህ ግንባር የነበረው ጦርነት በእንዲህ እንደ አለ በመተማ በኩል አርበኞች ሌላ ጦርነት ከፈቱ። ከካርቱም ወገን ለሚደረገው እንቅስቃሴ የመተማ በር መከፈት እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ፤ በዚያ ያሉ ኢትዮጵያውያን አጥብቀው ያሰቡበት ጉዳይ ነበር።[9] ይህ ሁኔታ ለጣልያኖችም ታውቆአቸው ስለነበር በሐሙስ ወንዝ፣ በአተከና በአጤ ጫማ ይዘውት የነበረውን ጦርነት ትተው ወደ መተማ ዘመቱ። ይህም ለአርበኞች ፋታ ሰጣቸው።

ሣህለ በሚባለው ቦታ የነበሩ አርበኞችን ለመደምሰስ ጣልያን ከደርጌ ምሽግ ተነሣ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ ሻ ከተባለው ወንዝ ላይ ገጠመው። ጦር ከጠላት ወገን አየለ ስለዚህ ለማሸነፍ ተቃርቦ የነበረው አርበኛ ሽሽት ጀመረ። የደጃዝማች ነጋሽ ትዕዛዝ፣ መምህር ፋንታዬ የተባሉት የፊንዝራራ ተክለኃይማኖት ቂስ ግዝት የማይመልሰው ሆኖ ተበተነ። ጥቂቶች ግዝት ጥሰን አንሄድም ብለው እስከ መጨረሻው ተዋጉ። እሉቱ በጣልያን አሸናፊነት ተደመደመ። ብዙ ሰው አለቀ፤ እልቂቱም በአርበኛው ላይ አመዘነ። ከሞተና ከቆሰለው በስተቀር፣ ዘጠና ሰድስት ሰው ተማረከ። ከተማረኩት ውስጥ አሥራ ስድስቱ በሞት ተቀጡ፤ ሰማንያዎች ለእሥራት ወደ ናኩራ ተላኩ። ከኒለኞች መካከል፣ ሰባ አምስቱ በናኩራ እሥር ቤት አለቁ።

ሁኔታው አሰቃቂ ነበር። አርበኛው ሻጌ ከተባለው ቦታ ስብሰባ አድርጎ ወደ ፊት ምን ማድረግ እንደሚሻል መከረ። ሁለት ሀሳቦች ቀረቡ። አንደኛው ደጃዝማች ነጋሽ ያቀረቡት ነበር። እሱም "በየዳን ለቅቀን አደጋ እየጣልን እንዋጋ እንጂ፤ ግንባር ለግንባር እየገጠምን ሰው አናስጨርስ። ለጣልያን ለመግባት የፈለገም ይግባ!" የሚል ነበር። ሌላው ሃሳብ የቀረበው በፊታውራሪ ካሣ ንጉሤ ነበር። እሳቸው ደግሞ ያለ ሀብታቸውን በሙሉ እንደሚሰጡ አስታውቀው፣ እዚያው በየዳ ከበራቸው ላይ ማለቅ እንደሚሻል ገለፁ።



ፊታውራሪ አስፋው፣ ወንድማቸው ነበሩና፤ ለጣልያንም በምንም ምክንያት እንደማይገቡ በመሐላ አስታወቁ።

ሁኔታው በእንዲህ ዓይነት እየተበቀ ሲመጣ፣ ጠላት የቀቢፀ ተስፋ መፍጨርጨር ተፍጨረጨረ። በተለይ ባንዳው የሕልውናው ፍፃሜ እንደተቃረበ ስለተረዳው፣ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። በፊታውራሪ አብርሃ ረዳ መሪነት፣ ጤና ከተባለው ቦታ፤ በደጃዝማች ታጅቦ ካሣ መሪነት፣ ካርዋ ላይ፤ በፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም መሪነት፣ ሉባ ላይ፤ በፊታውራሪ ኮከቤ መሪነት፣ ግልቢና ላይ፤ በፊታውራሪ መንገሻ ገብረመድህን መሪነት፣ ጭንፍራ ላይ፤ በመምህር ገብረዋህድ አስናቀው መሪነት፣ ደንቆላከ ላይ፤ በልጅ ሐደራ ረዳ መሪነት፣ አዘነበ ላይ ታላላቅ ውጊያ ተዋጋ። ቢሆንም ድል በተደጋጋሚ ለአርበኞች ሆነ። ባንዳም እንደ ጌታው፤ እንደ ጣልያን፤ ልብ ወረደው።

መጋቢት 5 ቀን 1932 ጣልያን ያንኑ የተለመደ ሀገር የማጥፋትና ሰው የመፍጀት ሥራውን ለማካሄድ ቁስቋም ከሚባለው ምሽጉ ወጣ። አርበኛው ደርጣ በር ላይ ጠብቆ አጥብቆ ስለወጋው ወደ ምሽጉ ተመለሰ። አሥር አርበኞች ሲሞቱ፣ ከጠላት ወገን ያለቀው ግን ብዙ ነበር። አርበኞች ቀላል መትረየስና ጠመንጃዎች ማረኩ።

ጣልያን በ1932 ዓ.ም በጠገዴ ሕዝብ ላይ ከመቸውም ይልቅ ድብደባ አበዛ። ሕዝቡ ስለሰለቸው፣ አርበኞችን ማቀፉን እንደ ቀነሰ ሰምቶ ነበር። ይህን ክፍተት ለመጠቀም በደሉል፣ በካሣ፣ በደብረ ሐዋርያ አድርጐ ዘለቀ። አርበኞች ጉዳዩን ቀደም አድርገው ተረድተውት ነበርና፣ ተዘጋጅተው ጠበቁት። በሦስት ረድፍ ተሰልፎ ከመጣው የጣልያን ጦር፣ ሁለቱ ግንባሩን እያጠፈ አፈገፈገ። ከሽሬ የመጣው ጦር ብቻ ምድረ ገበታ ላይ ተዋጋ። እሱውም ከስድስት ሰዓት ብርቱ ጦርነት በኋላ እየቀዘቀዘ ሄደና ተሸነፈ። ከሽሬ ባንዳ ብዙ ሰው አለቀ፤ ከተረፈውም ብዙ ተማረከ። አለቃቸው ነጋሽ ንጉሤ ቆስሎ አመለጠ። አርበኞች ብዙ መሣሪያና ጥይት ማረኩ።

ውጊያው ከተደመደመ በኋላ ደጃዝማች አዳነ መኰንንና ደጃዝማች ሀጐስ ተሰማ በተቀመጡበት አርበኛው ጉባኤ አደረገ። በጦርነቱ የተማረከው መሣሪያ ተደረደረ፤ ጥይቱ ተከመረ። ምርኮኛ ታሠረ፤ ፍርድ ተጀመረ። እኩሉ ሀገራቸውን ከድተው፣ ወገናቸውን ወግተዋልና ይቀጡ አለ። እኩሉ መሪ ሆነው ከአድያቦ፣ ከሽሬ የመጡት ይቀጡ፤ ሌላው ተገድዶ የመጣ ነውና ይለቀቅ አለ። ብዙ ጊዜ የወሰደ የርስበርስ ክርክር ተካሄደ። ክርክሩ በጠነነ ጊዜ፣ ደጃዝማች ሐጐስ ተሰማ እስረኞቹ በአርበኞች እጅ ያለውን አገር ከጎበኙና፣ በየአለበት አርበኛው የሚያካሂደውን ትግል ከአዩ፣ ከተገነዘቡ በኋላ፣ በሽኚ ወደ ሀገራቸው ይግቡ፤ ይህም በእኔ በኩል እንዲፈፀም እሥረኞቹ ለእኔ ይሰጡኝ አሉ። አርበኛው በሙሉ ድምፅ ተስማማና ሰጣቸው። እሳቸውም እንደቃላቸው ስለአደረጉ ከትግሬ የሚዘምተው ባንዳ ተቀነሰ።

የጣልያን ጦር፣ በኪሮስ በኩል፤ የደረስጌው ደግሞ፣ በመሸሐ በኩል ሄደው፣ ሁለቱም በየዳ ሊገናኙ ተነሱ። አርበኛው ከሦስት ተከፍሎ ለጦር ተዘጋጀ። አንዱ ክፍል በኪሮስ በኩል የመጣውን፣ ሌላው ክፍል በመሸሐ የመጣውን ሊወጋ፤ ሦስተኛው በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ አዛዥነት ለሁለቱም ክፍል በደጀንነት ትብሬ ከተባለው ቦታ ሆኖ እንዲጠባበቅ ተመደበ። ሁለቱም ጦር ውጊያ ገጠመ። በፊታውራሪ አበበ ወልደዳዊት የሚመራው አርበኛ ማይ ጠሐሉ ላይ ጠላትን ድል አድርጐ፣ አምስት መቶ ብረትና ሃያ ስምንት ሰው ማረከ። በመሸሐ ላይ የተዋጋው አርበኛ ግን ድል ሆነ። አለቃው ፊታውራሪ ነጋሽ መርሻ ቆስለው ተማረኩ። ከብዙ መፃፃፍ በኋላ ጣልያን ፊታውራሪ ነጋሽና ቀኛዝማች ዓለማየሁን ስለለቀቀ፣ ሃያ ስምንቱ ባንዶች ተፈቱ።

ወደ አደዛ ለመውረድ የተንቀሳቀሰውን የጠላት ጦር፣ በግራዝማች ረዳ ተሰማ የሚመራው አርበኛ ግንቦት 27 ቀን 1932 ዓ.ም ቢዛሆ ላይ ለአራተኛ ጊዜ ባካሄደው ውጊያ ድል አድርጐ መልሶታል።

ከፍ ሲል እንደ ጠቀስሁት፣ ራስ አሞራው ውብነህ በሕዝብ ተመርጠው የጠቅላይ አዛዥነት ሥልጣን ከተሰጣቸው በኋላ፣ በይበልጥ ኃላፊነት ሳይሰማቸው አልቀረም። የመኪና መንገድ እንዳይነካና ድልድይ እንዳይሠበር መመሪያ መስጠታቸውን ቀደም ብለን አንብበናል። የመተማን ምሽግ በመስበር በር ለመክፈት ከሱዳን ከመጣው ቡድን ጋር መነጋገራቸውም ይታወሳል። ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ርዳታ ለማግኘት ከሚስስ ሲልቪያ ፓንክረስትና ከሱዳን የእንግሊዝ አገረ ገዥ ጋር መፃፃፋቸው ታውቆአል። ካርቱም በነበረው አገረ ገዥ በኩል የፃፉት ደብዳቤ፣ ሞሶሎኒ ከሂትለር ጋር መቆሙን ከአረጋገጠ በኋላ የተፃፈ እንደ መሆኑ፣ ከእንግሊዝ ጋር ለተደረገው ግንኙነት ጥሩ መቆናጥጥ ሊሆንላቸው ቻለ። ይህም ለመሆኑ፣ ድሮ ከነበረው የእንግሊዝ ጦር አዛዥ ሰኔ 9 ቀን 1932 ዓ.ም ከተፃፈላቸው ደብዳቤ ይዘት ለማወቅ ይቻላል። የአዛዡ ይህ ደብዳቤ፣ እሳቸው ሚያዝያ 13 ቀን የፃፉትን ደብዳቤ ይጠቅስና፣ መልዕክታቸው ወደለንደን መላኩን ይገልፃል። አያይዞም እንግሊዝ ምክርና እርዳታ ልትሰጣቸው መዘጋጀቷን ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ነፃነትዋን በቶሎ እንደምትቀዳጅ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ተስፋ እንደአለው ያስረዳል።

ይህ ደብዳቤ አዲስ ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ሳለ፣ ሌሎች የትግሉን መቀናጀት የሚያውኩ ችግሮች አጋጠሙ። ራስ /አሞራው/ ውብነህ ከልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ጋር መሣሪያ እስከ መማዘዝና እስከ መዋጋት ደረሱ። እሳቸው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊ ከመሆናቸው የተነሣ ሳይሆን አልቀረም። ከእንግሊዝ ጋር አዲስ የተጀመረውም ወዳጅነት አልጣማቸውም። እንግሊዞች ለሠራዊቱ መሣሪያ እየሰጡ፣ በዚያው ሰበብ አዛዥ መሆን ከጀሉ። ራስ ውብነህ በበኩላቸው ሕዝብ የሚፈልገው ንጉሠ ነገሥቱን እንጂ መሣሪያ አለመሆኑን ገለፁ። እንዲያውም የነጭ፣ ነጭ ጣልያን ምን አለኝ? ብለው



ስብሰባውን ሰብረው (ጥለው) ወጡ። ከአርበኛውም አብዛኛው የእሳቸውን ሐሳብ ደገፈ። እንግሊዞች በጉዳዩ ተቸገሩ። ስለዚህ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እስከ 15 ቀን ድረስ ካርቱም እንደሚገቡ በምሥጢር ገለጡላቸው እና ቁጣቸውን አበረዱ። ጠቡም ቀዝቅዞ፣ የትብብሩ ሥራ ቀጠለ።

ጣልያን በበኩሉ አርበኛው ወደ እርሻው መሠማራቱን በመረዳት፣ በደጃዝማች ተድላ አበጋዝ ይመራ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃት ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። ደጃዝማች ተድላም በሞታቸው ቆርጠው፣ በአካባቢያቸው የነበሩትን ጥቂት አርበኞች ይዘው፣ ሰኔ 12 ቀን 1932 ዓ.ም አፈረዋናት ላይ ገጠሙት። ብዙ የጠላት ወታደር ገድለው፣ በሦስት ጥይት ተመትተው ወደቁ። ከቆሰሉ በኋላ እንኳን አምስት ጠላት ገድለው ሞቱ። ስድስት ባልደረቦቻቸው፣ የጌታችንን ሬሣ ጥለን አንሄድም ብለው አብረዋቸው ሞቱ። በጠቅላላው አሥራ ሁለት ምርጥ አርበኞች ወደቁ። ሌሎች ሁለት ቆስለው አመለጡ። ደጃዝማች ተድላ አበጋዝ፣ ጠላት ሳይባረር ቤት አልሠራም! በማለት፣ ያለቤት የኖሩ ጀግና ነበሩ።

እንግሊዞች የኢትዮጵያን ጦር በመደገፍ የአየር ድብደባ የጀመሩ ጊዜ፣ ጣልያኖች ከፍተኛ ድንጋጤ አደረባቸው። ሰው በጊዜ ከቤቱ እንዲከተት፣ መብራት እንዳያበራ፣ መስኮቶች ጥቁር ቀለም እንዲቀቡ አዘዙ። ለራሳቸው ዋሻ ቆፈሩ። አይሮፕላን በመጣ ጊዜ ማንም ሰው እንዳይንቀሳቀስ አደረጉ። የተጠበቀው አደጋ ሰኔ 24 ቀን 1932 ዓ.ም ደረሰ። ዘጠኝ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ከቀኑ በ11 ሰዓት በሦስት፣ በሦስት እየተከፈሉ የአዘዞን አይሮፕላን ማረፊያ ደበደቡ። ጣልያኖች ብዙ ፀረ አይሮፕላን መሣሪያ ቢተኩሱም፣ አንዳች መፈየድ አልቻሉም። አይሮፕላኖቹ ሥራቸውን አከናውነው በደህና ወደ መጡበት ተመለሱ። ከባንዳ በስተቀር፣ ሕዝብ በደስታ ልቡ ተነካ። በወቅቱ ባንዳ ራሱን ከማዳን በተረፈ ሌላ አልተመኘም። የአይሮፕላን ማረፊያው የሌሊት ድብደባ ለብዙ ጊዜ ቀጠለ።

በጐንደር የነበሩትን ጣልያኖች ሰብስቦ፣ አሳልፎ ወደ መተማ አዘመታቸው። ነገር ግን ጭልጋ ሲደርሱ፣ እምቢ ብለውት ወደ ጐንደር ተመለሱ። ጣልያን ደጃዝማች ተድላ አበጋዝን ከገደለ በኋላ በአፈረዋናት በኩል ያለውን ኃይሉን ማጠናከር ያዘ። በደጃዝማች ካሣ ገብሬ የሚመራው አርበኛ ነሐሴ 7 ቀን 1932 ዓ.ም ደብረ ሲና ላይ ገጠመው። የጠላት ጦር የተሰለፈው በአምስት ረድፍ ነበር። አርበኞችም እንደእርሱ በአምስት ረድፍ ገጠሙት። አዝማቹ ደጃች ካሣ ከጥቂት ባልደረቦቻቸው ጋር ደጀን ሆነው ይጠባበቁ ሳሉ፤ በደጃዝማች እጅጉ አያሌው የሚመራ የጠላት አንድ ክፍል ጦር ባልተጠበቀ ቦታ ተጠግቶ ገጠማቸው። እሳቸውም በጀግንነት የጦሩ ማሕል ገብተው ተዋጉ። ከጦሩ ሜዳ በመግባታቸው፣ ለይተው አወቁአቸውና በሮምታ ተኩስ መቱአቸው። በአርበኝነት ሥራ በቆዩበት ዘመን ሁሉ ተሸንፈው የማያውቁት ደጃዝማች ገብሬ ካሣ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ድል ሆነው በጦር ሜዳ ላይ ሞቱ።

አሥራ ሁለት እውቅ አርበኞች ሞቱ፤ ሌሎች አምስት ቆሰሉ። ከቆሰሉት ውስጥ አራቱ ሴት አርበኞች ነበሩ። በሌሎች አምስት የጦር ጉራዎች የሞተና የቆሰለው እጅግ ብዙ ነው። ቢሆንም በዛ ውጊያ ከጠላት ወገን ያለቀው ይበልጥ ነበር።

ጣልያን በመሐል አገር የነበረውን ጦሩን ለማጓጓዝ እንዲረዳው የደሴ ጐንደርን መንገድ በፍጥነት ያሠራ ጀመር። መንገድ ሠራተኞቹን የሚጠብቅ ጦር በየቦታው አስቀመጠ። ጐንደር በተከማቸው የጠላት ጦር ላይ የመሐል ሀገሩ ከተጨመረበት በቀላል የሚበገር ስለማይሆን፣ የመንገዱ ሥራ በችልታ የሚታይ፣ ከሀገር ልማት የሚቆጠር አልነበረም። ስለዚህ በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ፣ በደጃዝማች በላይ ተሰማና በደጃዝማች ከበደ የሚመራው አርበኛ ክምር ድንጋይ ላይ ገጠመው። የጠላት ጦርም በቀላል መትረየሶች አብዝቶ በመተኮስ ተከላከለ። ቢሆንም ድል የአርበኞች ሆነ። አንድ ኰሎኔል፣ አንድ ሻምበልና ሦስት መቶ አለቆች፣ ከአንድ መቶ ሃያ አምስት ጣልያናውያን ወታደሮች ጋር ሞቱ። ምርኮ በጣም አመቸ።

ከእንግሊዝ ጠቅላይ ጦር ሠፈር ነሐሴ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ለደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ደብዳቤ ደረሰ። ደብዳቤውም ሰላምታ ካቀረበ በኋላ፣ የሚያስፈልጋቸውን የጦር መሣሪያ የእንግሊዝ መንግሥት ሊሰጣቸው የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልጽና ንጉሠ ነገሥቱ በቅርብ ጊዜ ከአርበኞች ጋር እንደሚሆኑ የሚያበስር ነበር። ደጃዝማች ነጋሽም ደስታውን ለሠራዊታቸው ገልፀው፣ እንደ አገልግሎቱና እንደጀግንነቱ እያዩ እስከ ፊታውራሪነት ድረስ የማዕረግ ስምና ሽልማት ሰጡት።[10]

የ1932 ዓ.ም የጐንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። የ1933 ዓ.ምቱ በላቀ ተስፋና በበለጠ ብርታት ቀጠለ።

የመስከረምና የጥቅምት ወራት ለአርበኞችም ለጣልያንም የመዘጋጃ ጊዜ ሆነ። አርበኞች ከንጉሠ ነገሥቱ የሚላላኩበት፣ መመሪያ የሚቀበሉበት፣ መሣሪያ የሚያነሱበት ሆነ። ጣልያኖችም በበኩላቸው ከትናንሽ ምሽጐች ወደ ታላላቅ ከተሞች እየተሰበሰቡ ለመጨረሻው ፍልሚያ መዘጋጀት ነበረባቸው።

ማጠቢያ ላይ የነበረው ጣልያን በሠራቶም ሆነ በሌላው አካባቢ የሚተላለፈውን አርበኛ፣ ስደተኛና የእንግሊዝ ጦር ለማገድ ሙከራ አደረገ። ይህ ሙከራ በአስቸኳይ መገታት ስለነበረበት በቀኛዝማች ወርቁ ስንቄ የሚመራው አርበኛ ህዳር 1 ቀን 1933 ዓ.ም ማጠቢያ ድረስ ሄዶ ገጠመው። ሙከራው የጣልያንን ጦር ከዚያ አካባቢ ለማባረር ነበር። ከጥዋቱ አንድ ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት ተዋጉ። አዝማቹ ቀኛዝማች ወርቁ በጥይት ተመትተው ወደቁ። ጦርነቱ ዓላማውን ሳይመታ ቀረ።

በዚህ በህዳር ወር 1933 ዓ.ም በፊታውራሪ አስፋው ኃይለ ማርያም የሚመራው የጠላት ጦር ቅዱስ ያሬድ ተፈራ ላይ በተደረገ ጦርነት ተሸንፎ



ወደ መጣበት ተመለሰ። ብዙ አርበኞች ሞቱ፣ ቆሰሉ። ሆኖም ከጠላት ወገን ያለቀው ይበዛ ነበር። በመሽሐ በኩል ሲካሄድ የቆየው ጦርነት በዚህ አከተመ።

መሽሐና ሰቆጣ የነበረው የጠላት ጦር ምሽጉን እየለቀቀ አዲአርቃይ ገባ። አዲአርቃይንም ለቅቆ ወደ ደረስጌ፣ ከዚያም ወደ ጐንደር ሄደ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ እግር በእግር እየተከታተለ ጣልያን የለቀቀውን ቦታ በመያዝ ሕዝቡን አረጋጋ።

አርበኛው ደረስጌ የነበረውን ጣልያን ለመውጋት ሲዘጋጅ፣ ጣልያንን የገዛ ባንዳው ከድቶ ውሃ አላስቀዳ፣ እህል አላስገባ ብሎ ከበበው። በስፍራው የነበረው የጦሩ መሪ መቶ አለቃ ሽከቶ እጁን እንዲሰጥ ከአለቃው መመሪያ ቢሰጠውም፣ እሞታለሁ እንጂ ለገዛ አሽከሬ እጄን አልሰጥም ብሎ እምቢ አለ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ ሲደርስ፣ ጌታውን ማርኮ ሊፎክር ተዘጋጅቶ የነበረው ባንዳ ቦታ ለቀቀ። ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ጣልያን ውሃ እንዲቀዳ ፈቀዱለት፤ አሥር ሰንጋ ላኩለት። ያንን በልቶ እና ውሀ ጠጥቶ ከጠገበ በኋላ፦ ሥጋ የላክሁልህ፣ ውሃም የፈቀድኩልህ አስርቦ፣ አስጠምቶ ያዘኝ እንዳትል እንጂ ልለቅህ አይደለምና እጅህን ስጥ አሉት። መቶ አለቃ ሽከቶም ጀግናን የሚማርከው ጀግና መሆኑን ገልፆ፣ በሰላም እጁን ሰጠ። ስድሣ ስድስት መትረየስና ብዙ ጠመንጃ፣ እጅግ ብዙ ጥይትና የእጅ ቦምብ አስረከበ። ከሦስት ቀን እረፍት በኋላ አዲአርቃይ ለነበረው እንግሊዝ አስረከቡት።

ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጡአቸውን የሥራ ባልደረቦች ይዘው፣ ሻለቃ ሪንግሮስ ከካርቱም በገዳሪፍ፣ በቆብቲያ፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ ቆላ ወገራ፣ አጅሬ ከተባለው ቦታ ጥር 11 ቀን 1933 ዓ.ም ደረሱ። አርበኛውም በሰላም፣ በደስታ ተቀበላቸው። ሻለቃ ሪንግሮስ ከኬንያ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባ ሊገባ መቃረቡን፣ እሳቸው የተሰለፉበት የነበረው ጦር ቀድሞ ጐንደር ከተማ እንደሚገባ ያላቸውን ተስፋ ገለፁ።

የዳባትን ከተማ ለመያዝ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ጠላትን ከድቶ ከአርበኛው ጐን እንዲሰለፍ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑ ታወቀ። እሱም ንጉሠ ነገሥቱን በቅርብ፣ በመልክ የሚያውቃቸውን ልጅ ገሠሠን፣ ሄዶ አይቶ እንዲመጣና ለእሱ እንዲነግረው ላከው። በዚህ ምክንያት ጦርነቱ መካሄዱ ቀርቶ ወደ ካርቱም ጉዞ ተደረገ። ሻለቃ ሪንግሮስ ራሳቸው ልጅ ገሠሠን ይዘው ከቆላ ወገራ ወልቃይት በከብት፣ ከወልቃይት በካሚዮን ተሰነይ ድረስ፤ ከተሰነይ በአይሮፕላን ካርቱም ገቡ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከካርቱም ወደ ጐጃም ሄደው ስለነበር፣ ልጅ ገሠሠ ንጉሠ ነገሥቱን በዓይን ለማየት ሳይችል ቀረ። ቢሆንም የሚያውቁአቸውን መኳንንት በማነጋገር የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት እውነተኛነት አረጋግጦ ተመለሰ። ደጃዝማች አያሌው ብሩ የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት የሠማ ዕለት፣ ሌሊቱን ከጠላት ተለይቶ ወደ መረባ ወረደ።

በፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል የሚመራው ጦር ጐንደር ክፍለ ሀገር ገባ። ጐርጐራ የነበሩ ጣልያኖች ጠቃሚ ዕቃዎችንና የጦር መሣሪያዎችን፣ ዲናሚቶችን ጭምር ከጣና ባህር ጨምረው፣ አንጋራ ከሚባለው ደሴት ተጠግተው የነበሩ ጀልባዎቻቸውን አስጥመው፣ እጃቸውን ለእንግሊዝ ሰጡ። ለጐጃምና ለበጌምድር መገናኛ እንዲሆን አፄ ፋሲል ያሠሩትን ደልድይ፣ ፊታውራሪ ታምራት ቀደም ብሎ ሰብሮት እንደነበር መግለጼ የሚታወስ ነው።

ከደሴ ወደ ጐንደር የሚጓዘው ጣልያን መጣ። ፊታውራሪ ብሩ እስቴ ላይ ሠፈር አድርገው ስለነበር፣ አንድ ቡድን ጦር ላኩ። የጠላት ኃይል ስለአየለ፣ አሸንፎት ደብረ ታቦር ገባ። ቢሆንም አንድ መቶ ሠላሳ ጠመንጃና ሰባት ካሚዮኖች ተማረኩ።

ደጃዝማች አያሌው ብሩን በተገለፀው መንገድ ከጠላት ማስከዳት እንደተቻለ፣ የዳባትን ምሽግ የማጥቃት ዕቅድ ተሠራ። ሠራዊቱ በምሥጢር ከምሽጉ እንዲጠጋ ከተደረገ በኋላ፣ ሚያዝያ 5 ቀን 1933 ከጥዋቱ በ12 ሰዓት ጦርነት ተከፈተ። በምሽጉ ውስጥ ድብልቅልቅ ሆነ። ባንዶቹም እየተታኮሱ ወጡ። በመሀሉ የጣልያኑ የጦር አዛዥ ዕርዳታ በሬዲዮ ጠይቆ ኖሮ ከደባርቅ አዲስ ጦር መጣ። እሱን ደግሞ ምሥጢሩን አውቀው ከመንገድ ላይ አንጥፈው ይጠብቁ የነበሩ አርበኞች፣ ወቅን ከተባለው ቦታ ገጠሙት። አዛዥ ኮሎኔል በኒሊን ገድለው፣ ጭና ያመጣውን መትረየስና ጥይት ቀሙት። ጦርነቱ ተጋግሞበት በመከላከል ላይ እንዳለ፣ በረዶ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናም ጣለ። ቢራራ ገላ የተባለው አርበኛ በየተራራው እየዞረ ጥሩምባ በኃይል ስለነፋ፤ ብዙ አርበኛ የተሰበሰበ መስሎት ጠላት ደነገጠ። ሰሜን ደርሰዊ ላይ የተከበበውን እንዲያስለቅቅ የተላከው ጦር እንዲመለስ ስለታዘዘ፤ በለገዝ ከተባለው ወንዝ ላይ ከደረሰ በኋላ ተመለሰ። ከጭልጋ፣ ከደንቢያና ከጐንደር ሌላ አዲስ ጦር ለዕርዳታ ደረሰ።

ከዛ በኋላ ጣልያን ስለበረታ፣ አርበኞችን በጥይት እየደበደበ አረቡር እስከሚባለው ወንዝ ድረስ አባረራቸው። በዚያ ውጊያ (ግራዝማች) አሥማረ ዘረፉ የተባለ ባንዳ ለጣልያን ረድቶ የመጣውን ረዳት የአርበኛ ጦር አላሳልፍም ባይል ኖሮ፣ ድል የአርበኞች በሆነ ነበር።

በዚያ ሰሞን አርበኞች ፈንጠዝያ አብዝተው ነበርና፣ የአማራ አገር የምዕራብ ጦር አዛዥ የነበረው ኩሎኔል አስፖዳ ለትንሣኤ በዓል እንደተሰበሰቡ አደጋ ጥሎ ለመፍጀትና ለመማረክ አሰበ። ደጃዝማች በዛብህ ግብር እንደሚያበሉ በሰላዮች አማካኝነት አጠና። እንደአሰበውም ሚያዝያ 13 ቀን 1933 ዓ.ም (የማዕዶት ዕለት)፣ ተንከል ከተባለው ቦታ ላይ በማለዳ፣ በተንኮል አደጋ ጣለባቸው። ተሳክቶለት ቢሆን፣ እንግሊዞችንም ይማርክ ነበር። ደግነቱ ግን እንደዚያ አልሆነም። አደጋ ሲጣልበት አርበኛው በቅፅበት ተበተነ። ጉጣጉጡን ተጠግቶ በጥይት ጠዘጠዘው። አዲስ በሆነ ብልሀት፣ በጠመንጃው



አፈሙዝ ላይ የእጅ ቦምብ እያሠረ በመተኮስ ቦምቡን ከጥይት ኃይል ጋር እየወነጨፈ ደበደበው። ጦርነቱ ከጥዋቱ 1 እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ቆይቶ፣ በአርበኞች ድል አድራጊነት ተፈፀመ።

የዳባትን ምሽግ ለማስለቀቅ ከሚያዝያ 17 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ቀን ጦርነት ተካሄደ። ብዙ አርበኞች ቢወደቁም፣ ባንዳውን ጨምሮ ከጠላት ወገን ያለቀው ይበልጣል። በመጨረሻው ጠላት ተሸንፎ ከፊሉ ደባርቅ፣ ከፊሉ ደግሞ አምባ ጊዮርጊስ ገባ።

በሌሎች ምሽጐች የነበረው ጣልያን ሁሉ ምሽጉን እየለቀቀ ሲሄድ፣ ጥላዩ በተባለው ቦታ የነበረው ዝም ብሎ ተቀመጠ። እጅህን ስጥ ተብሎ ቢጠየቅ አልሰጥም አለ። አርበኛው ተሰብስቦ በዚሁ በሚያዝያ ወር 1933 ዓ.ም በምሽጉ ላይ ጦርነት ከፈተ። ጣልያንም ዕርዳታ ስለጠየቀ በኮሎኔል ቶሬሊ የሚመራ አዲስ ጦር መጣለት። እኩሉ አርበኛ የጥላዬን ምሽግ ከብቦ ሲያስጨንቅ፣ ሌላው ቡድን ከጐንደር የመጣውን የጠላት ጦር ሣንቅ ጥቅም ከተባለው ቦታ ገጠመው። ታላቅ ውጊያ ተካሄደ፣ ደጃዝማች ጫኔ መሸሻ ሞቱ። የጥላዬ ምሽግ ጦርነት ቀጥሎ፣ ከጠላት ጦር ብዙው አልቆ፣ የተረፈው ለአርበኞች እጁን መስጠት ጀመረ። ኰሎኔል ቶሬሊ በበኩሉ ሣንቃ ጥቅም ላይ በአገኘው ድል ተደፋፍሮ ወደ ጥላዬ ገሰገሰ። ጦርነቱ ቀጥሎ ብዙ ከተቀጠቀጠ በኋላ፣ ጣልያን ተሸንፎ ሽሽቱን ያዘ።

የጐንደር አርበኞች ጦርነቱን በዚህ ዓይነት እንደያዙ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከካርቱም በአሜድላ፣ በቢላያ፣ በደብረ ማርቆስ አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ አዲስ አበባ ገቡ። የጦርነቱ ሥርዓት ተለወጠ። ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ቆመች፤ የጣልያን የቅኝ ግዛት ኃይሎች በተራቸው እንደ ሽፍታ፣ የግል ሕይወታቸውን ለማትረፍ ይሳደዱ ገቡ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 164-165።
2. Greenfield, pp.162-163.
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 126-128።
4. ገሪማ ታፈረ፣ *ጎንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 15-49፣145-168።
5. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 66-80፣145-158፣174-182።
6. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 76-82፣124-138፣143-156፣161-162፣183-198፣213-219።
7. ኀይወት ኀዳሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 170-171።
8. ዝኒ ከማሁ፣ 197-203።
9. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ137-162፣217-232።

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት
# የአዲስ አበባ የትግል አስተዋጽኦ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ እንደመሆንዋ መጠን እንደ ማንኛውም ሀገር ዋና ከተማ የዓለምን ትኩረት ትስባለች። በውስጥዋ የሚካሄደው እንቅስቃሴ ሁሉ ክብደት አለው። በኢትዮጵያና ጣልያን ጦርነት ጊዜ የተጣለባት ትኩረት ደግሞ ከምንጊዜውም የበለጠ ነበር። እውነትም ለጣልያን መግባትም፣ መባረርም ወሣኝ ሆነች። ስለዚህ አዲስ አበባንም እንደ ሌሎች ክፍላተ ሀገር ለይቶ መመልከት የታሪክ ግንዛቤ ያዳብራል።

በጦርነቱ ዋዜማ አዲስ አበባ ከተቆረቆረች 49 ዓመትዋ ነበር። የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችዋ መኖሪያ ነበረች። ከሕዝብ መኖሪያ ቤቶች አብዛኛው ክዳኑ ሰንበሌጥ ነበር። የከተማው አካባቢ ከፍልውሃና ከዑራኤል በስተሰሜን፣ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ በስተምሥራቅ ያለውን ቦታ ይዞአል። በዚሁ አካባቢ የነበሩት የመኪና መንገዶች፣ አሁን በ1986 ዓ.ም ከሚታዩት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ብቻ ነበሩ ያኔ የነበሩት። ስፋትም አልነበራቸውም። በከተማዋ የነበሩ፣ በጣት የሚቆጠሩ መኪናዎች ይንቀሳቀሱባቸው ነበር።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፡- አንድ ባንክ፣ ጥቂት ንግድ ቤቶች በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቁመዋል። የሕዝቡ ብዛት አንድ መቶ ሺህ ቢሆን ነው። ቅርብ በወጣው የባሪያ አዋጅ፣ በተለምዶ ባሪያ ይባል የነበረው የከተማው ነዋሪ ቁጥር ብዙ ነበር። በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከነበረው ወደ 20,000 ያህሉ ቢሞትም፣ ነፃ በመውጣትም ቀንሶአል። ቢሆንም ከ15,000 ምንም ያህል አይቀንስም።[1] በዚህ ላይ ደግሞ አሽከሩ፣ ገረዱ አለ። በዚህ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ከሲሦ የማያንሰው የራሱ ንብረት የሌለው፣ ተገዥ ነበር ማለት ነው። ከእነሱ ውጪ የውጭ አገር ሰዎች በከተማዋ ነበሩ።

የከተማይቱ ውስጣዊ ገጽታ እንደዚህ ይሁን እንጂ፣ ባላት ኅብረተሰብ ዘንድ የነበረው አመለካከት ከቀድሞ ሁኔታዋ ሲመዛዘን ደህና ነበር። ሀገሩ ተረጋግቶ፣ ሰላም ሰፍኖ፣ ሕገ መንግሥት ወጥቶ፣ ምክር ቤት ቆሞ ነበር። ባርነት ባይወገድም፣ የባሪያ ንግድ ቀርቶአል። ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተው፣ የብዙ አገሮች ዲፕሎማቶች ተገኝተው፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ተከፍተዋል። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተቋቁመው ዘመናዊ አስተዳደር ተመሥርቶባት ነበርና፣ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ የነበራት ግምት ዝቅተኛ አልነበረም። ስለዚህ የአዲስ አበባ መያዝ ለጣልያኖች አንድ ዋና ጉዳይ ነበር።

በማይጨው ጦርነት የኢትዮጵያ ድል መሆን በዓለም ሬዲዮ ጣቢያዎች ዕለቱን ተስፋፍቶ ስለተነገረ፣ አዲስ አበባም ሰማች። በከተማይቱ ላይ ታላቅ ድንጋጤ ወደቀባት። ደጃዝማች ወልደጻድቅ የከተማይቱን ጸጥታ በማስከበር ረገድ ጠንካራ አቅዋም ያዙ። የከተማው ሹማምንትና ሕዝቡም



ተባበራቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የነበሩበት ጠፉ። ቢሆንም ከተማይቱ አልተናወጠችም። ንጉሠ ነገሥቱ ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ስደት እስኪሄዱ ደግሞ፣ የበለጠ መረጋጋት ሆነ። ከአዲስ አበባ እንደወጡ ግን ዝርፊያ ተካሄደ፤ ቤትም ተቃጠለ። ቢሆንም ከባድ ጉዳት አልደረሰም።

ማርሻል ባዶሊዮ 13,000 በሚሆን የጦር ሠራዊት ታጅቦ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። መግባቱንም በቴሌግራም ለሞሶሎኒ አስታወቀ። ለእሱ ክብርና ሞገስ ለማስገኘት የሚረዱ ዝግጅቶችም ተደርገዋል። ለባዶሊዮና ለመኳንንቶቹ መቀመጫ 193 ምርጥ ፈረሶች ከሮማ በመርከብና በመኪና ተጓጉዘው ቀርበዋል። ወደ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ልዩ ልዩ መኪናዎች ተሰናድተዋል። ማርሻሉ አዲስ አበባ በሚገባበት ጊዜ በሰማይ ላይ አይሮፕላኖች እንዲያንዣብቡ ተደርጓል። በርካታ ጋዜጠኞች ወሬውን ለዓለም ኅብረተሰብ ለማብሠር ተዘጋጅተዋል።

በዚህ ሁሉ በአዲስ አበባ ላይ ሐዘን አጥልቶባታል። በዚያው ማርሻሉ በሚገባበት ሰዓት ከባድ ዝናም ጥሎ፣ አካባቢው በጭቃ ተጨማልቆ፣ ወንዞች እስከገደፋቸው ሞልተዋል። እንባዉም የሰውን ፊት አጥቦታል። ሀገር ወዳድ ጀግኖች በየቦታው ጥግ እየያዙ የጠላትን ወታደር በጥይት መምታት ጀመሩ። ይህንን ለመከላከል የጣልያን ወታደሮች ያዩትን ሁሉ መግደል ያዙ። እለቱን ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ያላነሱ ኢትዮጵያውያን ሞቱ።[2] ጣልያኖች በመኪናም፣ በፈረስም፣ በእግርም እየተንቀሳቀሱ ማምሻቸውን የከተማይቱን ቁልፍ ቦታዎች ያዙ፤ የቀረውን ደግሞ በማግስቱ ያዙ።

የኢትዮጵያ መያዝ ሮም ሌሊት ላይ ተሰማ። ሕዝቡ በማግሥቱ ጥዋት ተነቅንቆ ወጣ። ሞሶሎኒም፣ ፒያሣ ቪንሲያ በተባለው አደባባይ ከተለመደው ሰገነቱ ላይ ብቅ ባለ ጊዜ፣ ምድር እስክትቀልጥ ጫጫታ ሆነ። ሞሶሎኒ እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ፡- "...ባለፈው 3000 ዓመታት ታሪካችን ውስጥ ኢጣልያ አኩሪና ታሪካዊ ሥራዎችን ሠርታለች። ይህ የዛሬው ግን...ከሁሉ የበለጠ ታሪካዊ ሥራ ነው... የሰላም መሠረት ዛሬ ተጣለ..." አለ።[3] እሱ ያን ይበል እንጂ፣ የዓለም ሕዝብ ከዚያ በፊት አይቶት ወደ ማያውቅ አዲስ ጦርነት እንገባ መሆኑን አልጠረጠረም።

የጣልያን ጦር በገባ ጊዜ አዲስ አበባ በድን ሆነች። የንጉሣውያን ቤተሰብ እና መኳንንቱ በተከታታይ በመርከብ እየተሳፈሩ ወደ አውሮፓ ተጉዞአል። ንብረትና ገንዘብ የነበራቸው ድርጅቶች ተዘርፈዋል። ጀግኖች መሣሪያዎቻቸውን ይዘው በከተማይቱ አካባቢ ባሉ ተራሮች ለፍልሚያ ተዘጋጅተዋል። ሕዝቡም በስጋት ከከተማው ዙሪያ ተጠልሎአል። ከሦስት ቀን በኂላ ሰላማዊው የከተማይቱ ነዋሪ ወደየቤቱ መመለስ ጀመረ። ሬሣው እየተጠረገ የጽዳት ሥራ ተካሄደ።

በአርበኞች ዘንድ የሃሳብ መለዋወጥ ተደረገ። ዋናው ሃሳብ አዲስ አበባ የገባውን የጣልያን ጦር ሳይደራጅ ደምስሴ ከተማይቱን ከጠላት ይዞታ

ለማስለቀቅ ነበር። ጣልያንን ኢትዮጵያን ያዝኩ ብሎ በዓለም ለነዛው ወሬ ማስተባበያ ስለሚሆን፣ የዚህ ጉዳይ ጠቀሜታ ትልቅ ሆኖ ተገኘ። "የኢትዮጵያ መሬትና በውስጡ የሚገኙ ሕዝቦች በሙሉ የኢጣልያ መንግሥት ተገዥዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ለኢጣልያ ንጉሥና ለዘሮቹ ዞሮአል..." ብሎ ሞሶሎኒ ያወጣውን አዋጅም የሚያፈርስ ይሆናል፤ በሀገር ውስጥም ጠንካራ ጦርነት (ተቃውሞ) ይቀሰቅሳል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ገቤኔቭ፣ በዓለም ማኅበር ጉባዔ የሚኖራቸውን ተደማጭነት ያጠናክራል። ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ ያገኘችውን ይዞታ ለማወቅ መንግሥታት የያዙትን እሽቅድድም ይገታል። የጣልያንን ጦር ያዳክማል።

ነገር ግን ይህንን የመሰለው ታላቅ ሥራ በተናጠል፣ በአንድ ቡድን ለማከናወን የሚቻል አይደለም። ስለዚህ በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ ኃይሎችን በኅብረት፣ በአንድ ጊዜ ለማንቀሳቀስ ተሞከረ። አዲስ አበባ የሚገባበት ጊዜ ለሐምሌ ማርያም፣ ማለትም በሐምሌ 21 ቀን 1927 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ። የቡልጋ ጦር፣ በደጃዝማች ፍቅረማርያም አስተባባሪነት በሾላ በር፤ የመርሐ ቤቴ ጦር፣ በደጃዝማች አበራ ካሣ አዛዥነት በእንጦጦ በር፤ የገነት ጦር መኰንኖች፣ በአዛዦቻቸው መሪነት በጉለሌ በር፤ የደጃዝማች ባልቻ ጦር በሰበታ እንዲገቡ ተመደቡ። የእነዚህ ኃይሎች መገናኛ ታላቁ ቤተ መንግሥት ላይ እንዲሆን ተወሰነ። መልዕክተኞች በያለበት ተላኩ።

አዲስ አበባን መልሶ ለመያዝ የወጣውን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ታላቅ ሙከራ ተደረገ። በደጃዝማች ፍቅረ ማርያም የተመራው ጦር ከሸንኮራ ተንቀሳቅሶ፣ የረርን ወደ ደቡብ በመተው ተጠጋ። አሁን ገርጂ በሚባለው አካባቢ አድርጐ በአብዋሬ በኩል በመግባት፣ በታላቁ ቤተመንግሥት የነበረውን የጠላት ጦር አጠቃ። የአንድ ሌሊትና የሁለት መዓልት ውጊያ አካሄደ።[4]

በደጃዝማች አበራ ካሣ የተመራው ጦር እንደተጠበቀው በእንጦጦ ገብቶ እስከ ሽሮ ሜዳ ድረስ ተጠጋ። ሆኖም ወደ ከተማ ሳይገባ ተመለሰ። በደጃዝማች አበራ አመራር ልልነት ሳይሆን አልቀረም። አቡነ ጴጥሮስ በዚህ ሁኔታ ማዋጋታቸውን ትተው ፍኖተ መስቀላቸውን ተሸክመው አዲስ አበባ ገቡ።

በገፈርሣ የመጣው ጦር እስከ ራስ ደስታ ሆስፒታል ድረስ አጥቅቶ ብዙም ሳይቆይ ተመለሰ። በደጃዝማች ባልቻ የተመራው ጦር እስከ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ ተጠጋ። በዚያ የነበሩ የጠላት አውሮፕላኖችን የማውደም ዕድሉ መልካም ነበር፤ ጦሩ ግን ዕድሉን ሳይጠቀምበት ቀረ። በሥልት መጓደል ሳይሆን አልቀረም። ከአዲስ አበባ ዙሪያ የመጣው አርበኛ ይህንን ሁሉ ሙከራ ሲያደርግ፣ የከተማው ነዋሪ አንዳች እንቅስቃሴ አላሳየም። እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ 11,353 ጠመንጃ፣ 53 መድፍ፣ 191 መትረየስ፣ 169 ሽጉጥ ለጣልያን አስረክቦ ስለነበር፣ እጁን አጣጥፎ በመቀመጥ ተመልካች ሆነ።[5]



አዲስ አበባን መልሶ ለመያዝ በተደረገው ሙከራ የተሰለፈው አርበኛ ብዛት በትክክል አልታወቀም። ግራዚያኒ 100,000 እንደነበረ በበኩሉ ገምቶአል። ከፍርሃት ጭምር የተደረገ ግምት ሳይሆን አልቀረም። አውሮፓውያን ከ10,000 እንደማያልፍ ግምት ሰጥተዋል። ይህም አነስተኛ ይመስላል። በዳጃዝማች ፍቅረማርያም መሪነት 10,000፣ በደጃዝማች ባልቻ 3,000፣ በደጃዝማች አበራ 5,000፣ በጉለሌ በኩል 2,000፤ በድምሩ 20,000 አርበኛ እንደተሰለፈ መገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም። በአንፃሩ በጣልያኖች በኩል የነበረው ተከላካይ ኃይል 26,163 ነበር። እሱም በ2,060 የጦር መኰንኖች የሚመራና በ38 ጠንካራ ምሽጎች ውስጥ የተጠለለ ነበር።[6]

በዚህ ሁኔታ አርበኞች አዲስ አበባን መልሰው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ከሸፈ። ለሙከራው መክሸፍ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩት። በመጀመሪያ የማስተባበሩ ሂደት የተዋጣለት አልነበረም። ለተዋጊዎች መልእክት የደረሱት እየዘገዩ ነበር። በዚህ ላይ ጊዜው ክረምት በመሆኑ የሠራዊቱን እንቅስቃሴ የውሃ ሙላትና ጭቃ ጎተተው። እንደገናም የደጃዝማች አበራ ካሣ አመጣጥ በአንድ ልብ አልነበረም። በጉለሌ የመጣው ሠራዊትም እውቅ መሪ አልነበረውም። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከነጭራሹም በሙከራው አልተሳተፉም። በእለቱም ከባድ ዝናም ስለዘነበ ሠራዊቱ ከመንቀሳቀሱም በተረፈ፤ ከነጭ ቃታ መውዜር በስተቀር ሌሎች መሣሪያዎች በዝናሙ ምክንያት መተኮስ አልቻሉም። ከላይ እንደተጠቀሰው የከተማው ሕዝብ አልተፈናፈነም።

ምንም ግቡን ሙሉ በሙሉ ባይመታም፤ ሙከራው መልካም ውጤት አስገኘ። አዲስ ጦርነት መቀስቀሱን ለዓለም ኅብረተሰብ አበሰረ። በሀገር ውስጥም አርበኞችን አስተባበረ።

የአቡነ ጴጥሮስ መያዝ በጣልያኖች ላይ ሌላ ጭንቅ ፈጠረ። የጣልያንን መንግሥት እንዲደግፉ በብዙ ተለማመጡአቸው። ልምምጡም ውጤት ባላስገኘላቸው ጊዜ አስፈራሩአቸው። ቆራጡ ሊቀ ጳጳስ አልተበገሩም። ሕዝቡም፣ ምድሪቱም ለጣልያን መንግሥት እንዳይገዙ ገዘቱ። ጣልያን ምንም ሌላ ምርጫ ስለአጣ፣ ከአንድ ሣምንት ልምምጥና ማስፈራራት በኋላ፣ ሐምሌ 29 ቀን ለሞት አቀረባቸው። አሁን ሐውልታቸው ከሚገኝበት በስተደቡብ ምሥራቅ፣ ከቀድሞው ማስታወቂያ ሚኒስቴር አጥር ጋ አስጠግቶ አቆማቸው። እርሳቸውም ዓይናቸው እንዲሸፈን የተደረገውን ሙከራ ተከላከሉ፤ ፊታቸውን ወደ ግድግዳው እንዲያዞሩ የቀረበላቸውን ጥያቄም አልተቀበሉም። ቀጥ ብለው ቆሙ። በመትረየስ ጥይት አስደበደባቸው። በዚያም ሳይሞቱ ስለቀሩ፣ አስገዳዩ መኰንን በሽጉጥ ራስ ቅላቸውን በታተነው።

ንጉሠ ነገሥቱ አብረዋቸው ወደ አውሮፓ እንዲሄዱ ቢጋብዙአቸው "በጐቼን ለማን ጥዬ?" ያሉት፤ በእንጦጦ በኩል የመጣው አርበኛ የተንቀሳቀሰበትን ዓላማ ትቶ ወደ ኋላ በተመለሰ ጊዜ፣ ተለይተው አዲስ አበባ

የገቡት እኚህ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ፤ የጨረሱትን የሥጋ ጉዳይ፣ በግብር ፈጸሙት። በዚህ ድርጊቱ የጣልያን መንግሥት የቆመበትን የጭካኔ መሠረት ለመላው ዓለም በግብር አሳየ። የኢትዮጵያም ሕዝብ ቁርጡን አወቀው።

ጣልያንን በሙሉ ኃይላቸው ለመቋቋም ከቆረጡት ጀግኖች አንዱ ደጃዝማች ባልቻ ነበሩ። ከጌታቸው ከአጼ ምኒልክ እረፍት በኋላ በተካሄደው የሥልጣን ሽኩቻ ወድቀው ብዙ መንገላታት የደረሰባቸው እኚህ አርበኛ፣ በወቅቱ የሰማንያ ዓመት አካባቢ ሽማግሌ ነበሩ። ሆኖም የደረሰባቸውን መንገላታት ከቁም ነገር ባለመቁጠር፣ የዕድሜአቸውንም መሸምገል ባለማሰብ፣ ትግል ጀመሩ። መካር ቢቀርባቸው፦ "ጌታዬ ምኒልክ አልጋዬን ለማ ጥለህ መጣህ ቢለኝስ?" በሚል ጥያቄ ዘጉት። ጣልያንም በበኩሉ ሊያግባባቸው ሞከረ። ሚስዮናዊ መስሎ ገብቶ፣ የአማርኛ ቋንቋ አጥንቶ፣ አገር ያምታታ የነበረ አንድ ጣልያናዊ ላከባቸው። እሱንም ደብቀው በያዘዋት አንዲት መሣሪያ፣ በጥይት ገደሉ። በዚህን ጊዜ የጣልያን መንግሥት አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ከበባቸው። ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ጣልያንን ብዙ ካስጨነቁት በኋላ በነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ተገደሉ።



የሁለት ትውልድ አርበኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ።

ምንም ግቡን ባይመታ፣ አርበኞች አዲስ አበባን ነጥቀው፣ መልሰው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ጣልያንን አስደነገጠው። ከተማይቱን ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኘውን የባቡር ሐዲድና፤ ከአሰብና ከአሥመራ ጋር የሚያገናኙትን የሰሜኑን የመኪና መንገዶች ለመቁረጥ የሚደረገው ርብርቦሽ ማለቂያ የሌለው ሆነ። ስለዚህ የከተማይቱን ጥበቃ ማጠናከር ግድ ሆነ። ጣልያን ብዙ ወታደር አስገባ፤ የከተማይቱን ዙሪያ በእሾህማ ሽቦ አጠረ። ሽቦው ርስበርሳቸው አራትና አምስት ሜትር ተራርቀው በተተከሉ፣ ጠምዛዛ አንጓ ባላቸው ብረቶች



ላይ ተተብትቦ የታሠረ ነበር። ወደ ከተማይቱ ለመግባትና ለመውጣት የሚቻለው በአሥር በሮች ብቻ ሆነ። ከእነዚህም ዋነኞቹ የእንጦጦ፣ የየካ፣ የገፈርሣ፣ የሰበታና የአቃቂ በሮች ሆኑ። በበሮቹም ላይ ከባድ ቁጥጥር ተደረገ። ያለይለፍ የፈቃድ ወረቀት ሰው መውጣት፣ መግባት ቀረ።



የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ሓውልት

በማሕል አገር የነበረው አርበኛ አዲስ አበባን ለመያዝ ያደረገው ሙከራ እንደ አልተቃና በታወቀ ጊዜ፣ በወቅቱ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ሆነው በጐሬ ከተማ የነበሩት ራስ እምሩ ተንቀሳቀሱ። በራስ እምሩ የሚመራው ጦር ዓላማ በጐሬ፣ በወለጋና በአምቦ በኩል ተወርውሮ አዲስ አበባን ለማጥቃት ነበር። እሱም ሳይቻል ቀረ። ደጃዝማች ፍቅረ ማርያምም ሸንኮራ ወደቁ። አዲስ አበባን መልሶ የመያዝ ጉዳይ ሕልም ሆኖ ቀረ።

ከተማይቱን ከውጭ አገር ያላትን ግንኙነት ለማስቀረት በሰሜኑ የመኪና መንገድና በምሥራቁ የባቡር ሐዲድ ላይ ይካሄድ የነበረው ትግል በተካረረ መልኩ ቀጠለ። በተለይ በባቡሩ ላይ በቀከታታይ የተጣለው አደጋ



የሁለት ትውልድ አርበኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ።



የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ሓውልት

ብዙ የጣልያን ወታደሮች ጨረሰ። የጦር ሹማምንቱንም ግራ አጋባ። የጣልያን መንግሥት ለዚህ ችግር ማቃለያ መስለው የታዩትን እርምጃዎች ወሰደ።

ማርሻል ባዶሊዮ ወደ ሀገሩ እንዲመለስና በቦታው ጄነራል ግራዚያኒ እንዲተካ ግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 1 ቀን 1936/ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተግባራዊ ሆነ። እንደሚታወቀው ግራዚያኒ በሊቢያ ሕዝብ ላይ ታላቅ ጭፍጨፋ በማካሄድ፣ በዚያ ሀገር ይካሄድ የነበረውን የነፃነት ንቅናቄ በማጥፋቱ፣ በጣልያን መንግሥት ዘንድ አመኔታን ያገኘ ጨካኝ ሰው ነበር። በወቅቱ፣ ለፍላጐቱ ማሳኪያ እንዲረዳው መሣፍንቱንና መኳንንቱን፣ የተማሩ ወጣቶችን ጭምር እንዲጨርስ ከሞሶሎኒ መመሪያ ተሰጠው። እሱም መሣፍንቱን፣ መኳንንቱን፣ ሊቃውንቱን በየአደባባይ እያንገዋለለ፣ ለጣልያን መንግሥት ያላቸውን ታማኝነት በሕዝብ ፊት እንዲገልጹ አስገደዳቸው። ከጥንት ቄሳራዊት ሮም ጀምሮ ሲሠራበት የኖረው፣ በጡንቻ በሰላም እንዲኖር የማድረግ ግብር /ፓክስ ሮማና/ በሥራ ላይ አዋለ።[7]

ጣልያኖች ደማቸውን ያፈሰሱበትን፣ የራሳቸውን ጥቅም የመገንባት ሥራ፣ በአዲስ አበባም ያዙ። ባሣር በመከራ የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ተዘጉ። የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፣ የጣልያን አየር ኃይል ሠፈር በመሆን ተገጣጣሚ ቤቶች በተጨማሪ ተሠሩለት። አሮጌው ትምህርት ቤት የወታደርና የቁስለኛ መታከሚያ ሆነ። የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የጣልያን ልጆች እንዲማሩበት ተደረገ። ከኢትዮጵያውያን፣ ስድስት የሚሆኑ የታላላቅ መኳንንት ልጆች ብቻ ጉለሌ፣ ደጃዝማች ይገዙ ሠፈር ለፋሽስት ልጆች ማስተማሪያ ከተሠራው ትምህርት ቤት ገቡ። ከእነሱም ውስጥ የራብ ጌታቸውና የራስ ሥዩም ልጆች ነበሩባቸው። ለሌላው ኢትዮጵያዊ የትምህርት ዕድል የለም።

የጣልያን መንግሥት ካተኮረባቸው ተቋማት ዋነኛይቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የነበሩት አማራጮች ሁለት ሆኑ። አንድም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ተገዥነት ተላቅቃ፣ ራስዋን ችላ እንደምትተዳደር ሆኖ፤ አቡነ ቄርሎስ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ። አለበለዚያ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ መርጣ ራስዋን እንድትችል ማድረግ ሆነ። ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ቄርሎስ ሮም ድረስ ሄደው ከተነጋገሩ በኋላ፣ ወደ እስክንድርያ ሄዱ። በአቡነ ዮሐንስ 10ኛ የተመራው የእስክንድርያ ሲኖዶስ ከሁለቱ ሃሳቦች አንዱንም ሳይቀበል ስለቀረ፣ ከቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ፣ አቡነ አብረሃም የሊቀ ጵጵስናውን ሥራ በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲይዙ፣ ታህሣሥ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ተደረገ።[8]

ከተማይቱ መረጋጋት ስትጀምር፣ በወጣቶቹ ዘንድ ቁጭት እየበረከተ ሄደ። ካህናት አቋዋማቸውን በማጠንከር፣ ከላይ የሚንቆረቀረውን ስብከት እንዲሁም በተግባር እንዲውል የሚፈስውን ትዕዛዝ፣ መቀበላቸው ቀረ።



ሁኔታዎች እየተካረሩ ሄዱ። ጣልያኖች ይህንን የተካረረ ስሜት ለማብረድ ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት፣ የጣልያን ንጉሥ አልጋ ወራሽ ሚስት ስለወለደች ጥሩ አጋጣሚ ተገኘ። ግራዚያኒ ለድሆች ገንዘብ እሰጣለሁ በሚል ምክንያት ሕዝብ እንዲሰባሰብ አደረገ። መኳንንትና መሣፍንቱም የችሮታውን ሥራ እንዲያደንቁ ተጠሩ። በዚህ ምክንያት የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም፣ አሁን በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት በሆነው፣ የበፊተኛው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት፣ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ተደረገ። 3,000 ያህል ድሆችና እጅግ ብዙ ሰው በተገኘበት በዚህ ስብሰባ ላይ፣ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስግዶም፣ ሰባት የእጅ ቦምቦች በመወርወር፤ ማርሻል ግራዚያኒን ጨምሮ ሠላሣ የጣልያን ሹማምንትና የጦር አለቆች አቆሰሉ።

በዚህ ጊዜ ግራዝያኒ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በከተማይቱ የነበሩ የጣልያን የጦር ኃይሎች በሙሉ ኃይላቸው ተንቀሳቀሱ። በወቅቱ በከተማይቱ ላይ ሠፍረው የነበሩት ወታደሮች ከ85,000 አያንሱም። ከእነሱም 42% ጣልያናውያን ወታደሮች፣ ከእነሱም 47% ጥቁር ለባሾች የሆኑት፣ የታጠቁ ጣልያናውያን የፋሽስት ካድሬዎች ነበሩ፤ የተቀሩት ከኤርትራ፣ ከሊቢያና ከሶማሊያ የተመለመሉ የቅኝ ግዛት ወታደሮች ነበሩ። እነዚህም ሕዝቡን እንደአገኙ ጨፈጨፉት። ቤት እየዘጉ አቃጠሉት፤ እጁን ወይም እግሩን በሽቦ ከመኪና ጋር እያሠሩ፣ በመንገድ ላይ ጐተቱት። እልቂቱ፣ ዓርብ ዕለት የካቲት 12 እኩለ ቀን አካባቢ የጀመረ እስከ የካቲት 14 ቀን እሁድ ከቀትር በኋላ፣ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ ቆየ። ሠላሳ ሺህ ሰው አለቀ፤ አራት ሺህ ቤት ተቃጠለ።[9]

ጣልያኖች አብረሃ ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶምን ማደን ጀመሩ። መሣሪያ ደብቃችሁአል፤ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶምን አብልታችኋል፣ አጠጥታችኋል እያሉ በከተማዋ ላይ ጭፍጨፋ አነገሱ። ከደብረ ሊባኖስ፣ ከዝቋላና ከዜና ማርቆስ ገዳማት ከአንድ ሺህ ያላነሱ መነኮሳትና መነኮሳስት ገደሉ። ጐንደር ማኅበረ ሥላሴንም አቃጠሉ። ሰባት ሺህ እሥረኞች ወደ ኤርትራ፣ ሶማሌና ኢጣልያ ተወሰዱ።[10]

አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም እነማን ነበሩ? አብርሃ ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም እና ስብሐት ኤርትራውያን ነበሩ። በአሥመራ ትምህርት ቤቶች የጣልያን ቋንቋ ከተማሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሥራ የያዙ ናቸው። በሕዝብ ዘንድ የነበረባቸው ጥርጣሬ ከባድ እንደ መሆኑ፣ አመጣጣቸው ለስለላ ሥራ በጣልያኖች ተልከው ሳይሆን አልቀረም። አብርሃ ደቦጭ የሚሠራው በጣልያን ለጋሲዮን ሲሆን፤ ስብሐት ደግሞ የጣልያን ወዳጅ በነበረችው በጀርመን ለጋሲዮን ነበር። እነዚህ ወጣቶች በጣልያኖች እየመረራቸው ሲሄድ ለወገኖቻቸው መቆርቆርና እርስበርሳቸው መመካከር

ጀመሩ። ከዚህም የተነሣ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የየካቲት 12 ቀኑን አደጋ ለመጣል በቁ።

ይህ እልቂት ሌላ አዲስ ሁኔታ ፈጠረ። የጣልያን ባለሥልጣኖች ስለሰላም የሚለፈልፉት ጉዳይ ሁሉ ከንቱ መሆኑ ተረጋገጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእልቂትና ለባርነት መዳረጉን አወቀ። በመሆኑም፣ ልብ ያለው ከጫካ ገባ። ይህም፣ መዳከም ጀምሮ የነበረውን አርበኝነት እንደገና መልሶ አጠናከረ። በየካቲት 12 ቀን ጉዳይ የአዲስ አበባ ካህናት አልነበሩበትም። ነገር ግን ጣልያኖች የአራዳ ጊዮርጊስን ለማቃጠል ሞከሩ። ይህ ባልተሳካላቸው ጊዜ ከዚሁ ከአራዳ ጊዮርጊስ፣ ከየካ ሚካኤል፣ ከኡራኤልና ከሌሎችም አድባራት ሊቃውንትን እያሠሩ ወደ ውጭ አገር ላኩአቸው። ይህም ካህናት ከአርበኞች ጋር እንዲያብሩ አደረገ። በጣልያን ላይ ክንዳቸውን ያነሱ ካህናትም ነበሩ። አለቃ መርሻ ከየካ ሚካኤል ወደ ቀበና ሄደው በገዛ ቤታቸው ውስጥ ሸፈቱ። አራት ጣልያን ገድለው ሞቱ። መምሬ በየነ የአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዘው ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ ጋር ተቀላቀሉ። በአዲስ አበባ ከነበረውም ሕዝብ፣ ነፃነት ፈላጊው አርበኝነት ገባ።

የኢትዮጵያውያንና የጣልያውያን በአንድ ከተማ ውስጥ መኖር፣ ጉርብትና እና መቀራረብን ፈጥሮ አስቸገረ። የፋሽስት አስተዳዳሪዎች ከኢትዮጵያ ሴቶች ተጠጉ። በመሆኑም ከየሴትኛ አዳሪው ጭን የሚፈላው ክልስ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ታላቅ ቅልቅሎሽ እንደሚፈጥር ታወቃቸው። ከዚህ ቅልቅሎሽ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም አልታያቸውም። የዘር ርክሰት እንደሚደርስ፣ ከእሱም ጋር መናቅ እና መዋረድ እንደሚመጣ ሆኖ ተሰማቸው። የየካቲት 12 ቀን አደጋ መከሰቱ፣ ለዚህ ችግር መፍቻ መስሎ የታያቸውን እርምጃ እንዲወስዱ ምክንያት ሆናቸው። ጥቁርና ነጭ የሚኖርበት ቦታ እንዲለይ አደረጉ። ቀድሞ ኢንዲጂኖ እየተባለ በአካባቢው ኅብረተሰብ ይጠራ የነበረው ሰፈር፣ ለጥቁር ዜጋ መኖሪያ እንዲሆን ተመደበ። በመሐንዲስ ተሸንሽኖ ለኢትዮጵያውያን መሥፈሪያ ሆነ። ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ድልድይ በስተምዕራብ ያለው የጥቁር፤ ከወንዙ በስተምሥራቅ ያለው የጣልያኖች መኖሪያ ሆነ። በእነሱም በራሳቸው መካከል ልዩነት ነበረ። ከገብርኤል በታች ያለውን ቦታ፣ ኢንቺስ የተባለው ድርጅት ቤት እንዲሠራበትና ለሹማምንት መኖሪያ እንዲሆን፣ ከሜክሲኮ አደባባይ በታች ያለው ቦታ ፎቶ እየተሠራበት የሕዝብ መኖሪያ እንዲሆን ተመረጠ።

ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም እልቂት በኋላ በሹማምንቱና በግራዚያኒ ላይ የሕዝብ ጥላቻ ተፈጠረ። በጣልያኖችም ዘንድ ሞገሱ ቀነሰ። ሊሶና የተባለው የጣልያን የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ግራዚያኒ ከሹመቱ እንዲሻር ሞሶሎኒን ወተወተ። ቀድሞውንም ግራዚያኒ የተሾመው ሊሶና ሳይጠየቅ ስለነበረ፤ ጥያቄውን አልቀበልም ለማለት አስቸገረው። ግራዚያኒ ከደረሰበት የግድያ ሙከራ ቢድንም፣ ድንጋጤው የማይለቀው ሆነ። ቢሆንም



ራሱን ከውርደት ለማዳን፣ ጥፋቱ የሊሶና እንደሆነ አድርጐ ማሳየት ያዘ። አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ ካራቢኒየር የሚባሉት የደህንነት ኃይሎች ግራዚያኒን ደገፉ። ነገር ግን ግራዚያኒ ከሦስት መቶ ሃምሣ ቦታ ቆስያለሁ የሚል ዝማሬ ይዞ፣ አንዳች ማሻሻያ ማድረግ አቃተው። በጭካኔ ሥራው ገፋበት። ሁኔታው የማያስኬድ እየሆነ ስለቀጠለ፣ ግራዚያኒ ተሻረ። ቁስሉ እንዳይቆጠቁጠው የነጋሌ ጦር ሜዳ ማርሻል ተብሎ 500,000 ሊሬ የጡረታ አበል ተቆረጠለት። የግራዚያኒ ደጋፊዎች ተቃውሞአቸውን ስለአጠናከሩ፣ ሊሶናም 100,000 ሊሬ ካሣ ከሞሶሎኒ ተፈቅዶለት በሮም ዩኒቨርስቲ የቅኝ ግዛት ታሪክ ሊቅ ሆነ።[11]

ባላምባራስ /ጄነራል/ ተድላ መኰንን ከአዲስ አበባ ከተማ አምስት ጣልያኖች አፍነው ወስደው ለገጣፎ ወንዝ አጠገብ ገደሉአቸው። ጣልያኖቹን የወሰዱአቸው፣ የአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው አካባቢ መሆኑ ነው። በዋሻው ምድር ቤት ውስጥ ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ቀብረውት የነበረውን በርካታ ጠመንጃና ጥይት ወሰዱ። ደጃዝማች መኰንንን ግን ጣልያን ቀደም ብሎ ወደ አገሩ ወስዶአቸው ስለነበረ፤ አርበኝነት እንዲገቡ ለማድረግ የተዘጋጀው ዕቅድ ከሸፈ። ሥራው የተቀነባበረው ኮተቤ በነበሩት በግራዝማች እንደሻው ነበር።[12]

በግራዚያኒ ምትክ፣ ዱክ አሜዲዮ ደ አምስታ፤ በሊሶና ምትክ ፓውሎ ቴሩዚ ተሾሙ። ዱካ ደ አምስታ ታህሣሥ 16 ቀን 1930 ዓ.ም /ዲሴምበር 26 ቀን 1937/ አዲስ አበባ ገባ። ወዲያውም የአስተዳደሩን አረመኔነት ለመቀነስ ሙከራ አደረገ። ሞኝ አበሻ፣ የተሻለ ነገር የተገኘ መሰለው። ነገር ግን የዱክ ደ አምስታ ዓላማ በለዘብተኛ አያያዝ ኢትዮጵያን ከዘላቂ መሥገርት ውስጥ ለማስገባት ነበር። የዚህ መሥፍን መሾም ደጋፊም ተቃዋሚም ነበረው። ኢትዮጵያን ከፋሽስቶች ፈልቅቆ ወደ ኢጣሊያ ንጉሣውያን ቤተሰቦች የሚያገባ መሆኑ የማይቀር ሆነ። ፋሽስቶች ለሥልጣናቸው እንደ መሠስታቸው፣ የንጉሣውያን ቤተሰቦች ደግሞ የኢጣልያ ዘውድ ከኢትዮጵያ ጣጣ ውስጥ እንዳይዘፈቅ ፈርተው ነበር።

የዱክ ደ አምስታ ሃሳብ ለጣልያን በርካታ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ተጠብቆ ነበረው። በኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋት ይፈጥራል፤ በአውሮፓ የነበረውን ጫጫታ ይቀንሣል፤ ለጦርነት የሚደረገውን ወጭ ወደ ልማት ሥራዎች ይመልሳል። አለመጠን የገነነውን የፋሽስት ፓርቲ ኃይል፣ በተለይም የሞሶሎኒን ሥልጣን ያቀዘቅዛል። ስለዚህ ዱካ ደ አምስታ ቀደም ብሎ ግራዚያኒ ያጨመላለቀውን አስተዳደር ለማሻሻል ሞከረ። የአዲስ አበባን ከተማ በ14,000 ስኴር ኪሎሜትር ውስጥ ለመከለልና ከሸዋ ለመነጠል ኅዳር 20 ቀን 1929 ዓ.ም /ኖቬምበር 11 ቀን 1936/ የወጣውን አዋጅ ሻረ። የሸዋን አንድነት መልሶ አጸና። ቢሆንም በወታደራዊ ሥራ ረገድ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ምሥራቅ ተብሎ በሦስት እንደ ተከፈለ ቆየ።

ጣልያኖች ከመግባታቸው በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ሦስት ሲኒማ ቤቶች ነበሩ። እነሱም፦ ደጎል አደባባይ ከሚባለው አካባቢ አንዱ፣ አሁን የመብራት ኃይል ባለሥልጣን ከአለበት፤ ሁለተኛው ሲኒማ አምፒር ከአለበት፤ ሦስተኛው ደግሞ ከማዘጋጃ ቤቱ ፊት ለፊት ከሚታየው ባዶ ቦታ ላይ ነበሩ። ሶስቱም ጣልያኖች በገቡ ጊዜ ተቃጠሉ። በምትካቸው ዛሬ ሲኒማ ኢትዮጵያ የሚባለው ሲኒማ፣ ሮማ ተብሎ፤ ከነፃነት በኋላ ሲኒማ አድዋ ተብሎ የነበረው፣ ሲኒማ ማርኮኒ ተብሎ፤ አራት ኪሎ አሁን የሣይንስ ፋክልቲ ከአለበት ጠርዝ ላይ ሲኒማ አዲዮን ተብለው ለጣልያናውያን ተከፈቱ። ለአበሾች ደግሞ መርካቶ፣ ራስ ኃይሉ፣ አሁን ራስ የሚባለው ሲኒማ ቤት ተከፈተ።[13]

የወጣቱን ሃሳብ ለማረጋጋትና ጊዜውን የሚያሳልፍበት ዕድል ለመስጠት፣ ስፖርት ተስፋፋ። አራዳ፣ ስድስት ኪሎ፣ ቀበናና እንጦጦ የሚባሉ የእግር ኳስ ቡደኖች ተቋቋሙ። እነ አቶ ይድነቃቸው እሸቴ የስፖርት ሰው መሆን የጀመሩት፣ በዚያን ዘመን ነው። የብስክሌት ውድድርም ነበር።[14] በየአደባባዩ የወሬ ማድመጫ ሬዲዮ ተተከለ። የሮም ብርሃን የተባለ ወርሐዊ መጽሔት፤ እንደዚሁም ተሐደስት ኢትዮጵያ የሚል ሳምንታዊ ጋዜጣ ይታተሙ ጀመር። እንደ ቀድሞው ሁሉ፣ የመንግሥቱ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነበር።

የከተማዋ ሴቶች በበኩላቸው የራሳቸውን ሥራ አካሄዱ። አልጋቸውን እየዘረጉ፣ ፍራሻቸውን እያመቻቹ፣ መጨጊያ ያለው ወንበር እያዘጋጁ ተቀመጡ። ቤተሰቦቻቸውን ሳይዙ ነጠላቸውን የመጡ ጣልያኖች ከዚያ የተፈጥሮ ወጥመድ ገቡ። ይህ ሁኔታ ችግር ፈጠረ። እንደገለፅኩት፣ ነጭና ጥቁር እንዳይቀላቀል የሚያግደው ሕግ ተጣሰ፤ ክልሶች በረከቱ። ጣልያናውያን ሚስቶች ተቆጡ። ከጣልያን ሠራዊት የሚበዛው በቂጥኝና ጨብጥ ተበከለ፤ ከአበሻውም እንደዚሁ። የጣልያኖች ምሥጢር ከከተማ እያፈተለከ ለአርበኞች ይደርሳል። በጠቅላላው ምሥጢር የመጠበቅ፣ የማሰብና የመሥራት አቅም ተቀነሰ።[15]

ሞሶሎኒ የገመተው ኢትዮጵያ ስትያዝ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ጣልያናውያን ተሽቀዳድመው ይገባሉ ብሎ ነበር። ነገር ግን እንደተጠበቀው አልሆነም። ጦርነቱ በመቀጠሉ ምክንያት፣ ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አልፈለጉም። ከፍተኛ ባለሙያዎች እንዲመደቡባቸው ከተፈቀዱት 2700 ሥራዎች ላይ የተገኙት ባለሙያዎች፣ 1,350 (50%) ብቻ ነበር።

በአቀጣጠርም ረገድ እንዲሁ ችግር አጋጠመ። የሚፈልጋቸውን እየመረጠ የመቅጠር ሥልጣን ኅዳር 5 ቀን 1930 ዓ.ም ቢሰጥም፣ የቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስትር መቅጠሩን ስለ ቀጠለ አዋጁ ሳይከበር ቀረ። ይህንን የባለሙያ እጦትና የአቀጣጠር ችግር ለማቃለል፣ ከጦሩ እየመረጡ መቅጠር ግድ ሆነ። ይህ ደግሞ የተዋጊውን ኃይል ቀነሰ። ለቁጥጥር ባለመመቸቱ ስንት



ሠራተኞች እንደተመደቡ ለማወቅ እንኳን አዳገተ። ቴሩዚ 6,943 ቢልም፣ ከ10,000 የሚያንሱ አልነበሩም። በዚህ ላይ ደግሞ ከተቀጠሩት ሠራተኞቹ ውስጥ 50%ቱ በቂ እውቀትና የሥራ ልምድ አልነበራቸውም።

በዛ ላይ ደግሞ አብዛኞቹ ቤተሰብ ስለሌላቸው ጠጭዎች፣ ሴሰኞች፣ ፍቅረ ንዋይ የተጠናወታቸው ሆኑ።[16] የጦር መኮንን ተብሎ የተመደበው ኢጣሊያዊ፣ በአርበኝነት ወንድምዋ የሞተባትን ኢትዮጵያዊት እቁባቱን ከማስተዛዘን የማይገታ ሆነ። እንዲህ መሰሎቹ ሁኔታዎች ሁሉ የዱካ ደ አምስታን አስተዳደር ከማጥ ውስጥ ከተቱት።

ሁኔታዎች በእንዲህ እንደአሉ፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ፤ እናም ነገሮች በፍጥነት ተለዋወጡ። ሞሶሎኒ ከሂትለር ጐን መቆሙን አስታወቀ። እሱም ወዲያው በሣልሣዊ ኢማኑኤል ትዕዛዝ ተይዞ ታሠረ። ሂትለር የአየር ወለድ ኃይል ልኮ አስፈታው። ወደ ጀርመን አገር አስወስዶ ከአነጋገረው በኋላ ወደ ጣልያን ሊመልሰው ሞከረ። ነገር ግን በጣልያን አገር ውስጥ የርስበርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ጃፓን በፈናዋ ፐርል ሃርበር የተባለውን የአሜሪካን ወደብ በአይሮፕላን ደብድባ፣ በአምስት የአሜሪካን የጦር መርከቦች ላይ ጉዳት አደረሰች። ከዚያን ጊዜ አንስቶ አሜሪካን ከዳር ሆኖ ተመልካችነቷን ትታ፣ ከጦርነቱ ገባች።

ሁኔታዎች እየተለወጡ ስለሄዱ፣ ሞሶሎኒም በግልፅ ከሂትለር ጐን መቆሙን ስለ አስታወቀ፣ እንግሊዝ ጦርነቱን ወደ አፍሪቃ አዞረችው። በዛው መሠረት በምሥራቅ አፍሪካ አዲስ የጦር ግንባር ተከፈተ። ሊቢያ የጦር ሜዳ ሆነች። ስዊዝ ካናል ለጣልያን መርከቦች ዝግ ሆነ። ምሥራቅ አፍሪካ ላይ የፈሰሰው የጣልያን ሠራዊት ብቻዉን ሆነ፤ ከአገሩ ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ። በመቀጠል እንግሊዝ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከለንደን አንቀሳቅሳ ካርቱም አስገባች፤ በደቡብ፣ ከኬንያ፤ ከምሥራቅ፣ በበርበራ· ጦርዋን አንቀሳቀሰች። ከካርቱም በኦሜድላ በኩል ንጉሡ ነገሥቱን ይዞ ጐጃም የሚገባ፤ በከሰላ በኩል ገብቶ አሥመራን የሚይዝና የቀይ ባሕርን የሚቆጣጠር፣ በእንግሊዝ የሚታዘዝ ጦር፣ ከዓለም ማዕዘናት አቀረበች። በምሥራቅ አፍሪካ የነበረው የኢጣልያን ሠራዊት፣ ከጠላቶቹ ጋር ተፋጠጠ፤ ለእልቂት ተጋለጠ። ዱካ ደ አምስታ የሚይዝ፣ የሚጥለውን አጣ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ወሬውን ከዓለም ሬዲዮ ዕለት፣ በዕለት ይሠማ ነበር። የሰማው ላልሰማው እያሰማ፣ ሃሳብ ለሃሳብ ተዋወቀ። በጣልያኖች ላይ የነበረው አመለካከት ተለወጠ፤ እነሱም የከተማው አጠቃላይ ልቦና በጣልያኖች ላይ መለወጡ ታወቃቸው። የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ታወቀ። የነፃነት እንቅስቃሴ ጠነከረ፤ ባንዳ ከአርበኛ ጋር አበረ። ዱክ ደ አምስታ ገንዘብ በመርጨት፣ ሹመት በመስጠት፣ ወሬ በመንዛት፣ ሁኔታውን ለመቋቋም ሞከረ፤ ግን አልተቻለም። በምሥራቅ የመጣው የኢትዮጵያ ነፃ

አውጭ ጦር ከሐረር አልፎ አዋሽን ተሻገረ። ንጉሠ ነገሥቱ ከቢልያ አልፈው ቡሬ ገቡ። አዲስ አበባ ተጨነቀች።

ዱካ ደ አዎስታ ውሣኔ ማድረግ ግድ ሆነበት። ምርጫው፡- አንድም መዋጋት፣ አለዚያም እጅ መስጠት ሆነ። መዋጋት ማለት፣ ሞት፤ በቅኝ ግዛት አገር ላይ እጅ መስጠት ደግሞ፣ የሞት ሞት ሆነበት። መዋጋት መረጠ። ለመዋጋት ደግሞ የኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ማግኘት ግድ ሆነ። ራሱ መጠየቅ ውርደት ነበርና፣ የታማኞቹን ምክር አስጠየቀ። ተጠያቂዎች የታያቸውን፣ የሚጥመው የመሰላቸውን ነገሩ። የቀጨኔ መድኃኒ ዓለም አለቃ፣ አባ ገብረ መስቀል /አቡነ ዮሐንስ ዘትግራይ/ የተለየ ሃሳብ ነበራቸው። እሳቸውም "በአዲስ አበባ ከተማ ሕፃን፣ ሴት፣ ሽማግሌ ሕመምተኛ አለ። በከተማው ላይ ጦርነት ሲከፈት ኢትዮጵያውያኑ አገራቸው ነውና ወደየወገናቸው ይሄዳሉ። የእናንተ ሰዎች፣ ጣልያኖች ወዴት ይሄዳሉ? ስለዚህ ከበረሃ ላይ እንጂ፣ ከከተማ ላይ ልትሞቱ አይገባችሁም" አሉአቸው። ጉባዔው በዚሁ አበቃ።[17]

ዱክ ደ አዎስታ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ለመዋጋት የነበረውን ሃሳብ ተወ። ከከተማይቱ ወጥቶ ለመዋጋት ዝግጅት አልተደረገም። አዲስ አበባ ላይ ለመዋጋት በነበረው ዕቅድ ምክንያት ተላቅቆ በሩ ክፍት ነው። እንግሊዞች ከንጉሠ ነገሥቱ በፊት ለመግባት አዋሽን ተሻግረው ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ ናቸው። ስለዚህ የዱካ ደ አዎስታ ዕድል ወደ ሰሜን መሸሽ ብቻ ሆነ። ከተማይቱን ለእንግሊዝ እንዲያስረክብ ለከንቲባው ሥልጣን ሰጥቶ ወደ ደሴ፣ ከዚያም ወደ አምባላጌ ሸሸ። የጠላውን ውርደት አምባላጌ ላይ፣ የፈራውን ሞት ደግሞ ኬንያ አገር የሚቀበለበትን፣ የተቀበለበትን የመከራ ጉዞ ቀጠለ።

በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታዎች ሌላ ቅርጽ ነበራቸው። የሸዋ አርበኞች አዲስ አበባን ለመያዝ አቆብቁበዋል። ነገር ግን አንድነት የላቸውም። ስደታቸውን እንደ ሽሽት የቆጠረባቸውና መልሶ ለመቀበል ቅሬታ የነበረው አርበኛ ቀድሞአቸው አዲስ አበባ መግባቱን ንጉሠ ነገሥቱ አልወደዱትም። በዚህ ላይ ደግሞ አርበኛው በከተማው ውስጥ ያሉትን ጣልያናውያን በቁጭት ይጨርሳቸዋል የሚል ስጋት ተፈጠረ። ከየአለበት ተጠረቃቅሞ በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ የቆመው ስደተኛ፤ የቢልያን በረሃ አቋርጦ በመኪናና በባቡር ወደ አዲስ አበባ የሚገሰግሰውን የእንግሊዝ ጦር ቀድሞ አዲስ አበባ ለመግባት አቅም አላገኘም። የጠላትን ጦር ጠራርጎ ከሀገር የማስወጣቱ ሥራ ወደ ኋላ ተትቶ፤ በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው ጦር የጠላትን ጦር እየቆራረጠ በመገስገስ ቀድሞ አዲስ አበባ እንዲገቡ፤ በቀና ልቡና ኢትዮጵያን ይረዱ ከነበሩት፣ ከኰሎኔል /ጄነራል/ ዊንጌት በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ በኩል በምሥጢር ቀርቦ የነበረው ሃሳብ ተቀባይነት በማጣት፣ ቀርቶአል።[18] በእነዚህ ምክንያቶች አዲስ አበባን የመያዝ ዕድል፣ የኢትዮጵያውያን ሳይሆን ቀረ።



በከተማው ውስጥ ፈንጠዝያ በዛ፤ ጣልያኖችን መፍራት ቀረ። ፈንጠዝያ ይካሄድባቸው ከነበሩ መጠጥ ቤቶች አንዱ መርካቶ ራስ ትያትር አካባቢ የነበረው የወይዘሮ እልፍነሽ ዘውዴ ቤት ነበር። ከዚያ የተሰበሰበውን ሰው ብዛት በማየት ራስ ጌታቸውና አቶ ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝ ገቡ። ንግግር ለማድረግ በመሞከራቸው ጠብ ተነሣ። ሁለቱ የጣልያን ባለሥልጣኖች ወጥተው እንደሄዱ ጣልያናውያን የከተማ ዘበኞች መጡ። ተኩስ ተከፈተ። ሰባት ኢትዮጵያውያን ሞተው ሌሎች አሥራ አምስት ቆሰሉ።[19]

ከመንግሥቱ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም እሑድ ጥዋት አዲስ አበባን ያዘ። አሁን ዩኒቨርሲቲ ከሆነው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት ገብቶ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ። የእንግሊዝ ሰንደቅ ዓላማ መተከሉ ደግሞ በሕዝብ ዘንድ ቁጣ አስነሣ። በዚያው ቀን ከቀትር በኋላ በ11 ሰዓት ጄነራል ዊዛራል በታላቁ የአፄ ምኒልክ ጊቢ ተገኝተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማም ተከሉ። በአቶ /ብላታ/ ዳዊት እቁበ እግዚእ አስተርጓሚነት ባደረጉት ንግግር "ይህ ቀን አዲስ አበባን ለእናንተ /ለሕዝቡ/ እንደገና መልሼ የያዝኩበት ቀን በመሆኑ የምኮራበት ነው። የያዝኩትም በምንም ዓይነት አዲስ የቅኝ ግዛት ጥርጣሬ በማያስከትል ሁኔታ ነው" በማለት ሕዝቡን አረጋጉ። የንጉሠ ነገሥቱም አዋጅ በዚያው በአደባባዩ ላይ ተነበበ።[20] ነዋሪውም በሰላምና በደስታ ወደየቤቱ ተመለሰ።

የእንግሊዝ ጦር የአዲስ አበባን ከተማ ከንጉሠ ነገሥቱም ከአርበኞችም አስቀድሞ መያዝ፤ ለእንግሊዞች የሚያስገኝላቸው ተደራራቢ ጥቅም ነበረው። አንደኛው ጥቅም በሰሜን አፍሪካ ለሚደረገው ጦርነት ለሚያንቀሳቅሱት ጦር መንገድ መክፈቱና ለማቀነባበር የሚረዳ ምቹ ቦታ መገኘቱ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ምንግዜም በእንግሊዞች ዘንድ ዋጋ የሚሰጠውን የክብር አጠባበቁን ጉዳይ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስተካክላል። ሦስተኛው ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሥልጣን ሊመለሱ ይችላሉ ለሚለው ጥያቄ ጊዜ ይሰጣል። በጦርነቱ ወቅት እጃቸው የገባውን ነገር ከኢትዮጵያ ለማውጣት ይቻላል። በአዲስ አበባ የነበሩትን ጣልያናውያንና ሌሎችም የውጭ አገር ሰዎች ሕይወት አዳንን በማለት፤ የዓለም ኅብረተሰብን አመኔታ ለማግኘት ይረዳል። እንደዚሁም ሆነ።


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ላፒሶ ጌ.ዴሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም*፣ ገጽ 39።
2. Richard Greenfield, *Ethiopia*, pp.228
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*, ገጽ 146-147።
4. ከቀኛዝማች ምሥካየ ሥዩም በወቅቱ የተነገረ።
5. ጳውሎስ ኞኞ ።
6. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini*, pp.183

7. *Ibid.*,pp, 35-48.
8. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው፣* ገጽ 83-103።
9. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 158-161።
10. Sabacchi, p.189-194.
11. *Ibid.*, pp. 52-53.
12. ከቄስ ኃይለ ሚካኤል የተነገረኝ።
13. የራስ ትያትር *መጽሔት*፣ 1976 ዓ.ም ፣ገጽ 45።
14. የሮማ ብርሃን *መጽሔት*፣ የየካቲት 1932 ዓ.ም እትም።
15. Sabacchi, pp.167-174.
16. *Ibid.*, pp. 78-93.
17. ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በ1958 ዓ.ም የተነገረኝ።
18. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 373።
19. ከጄነራል መኰንን ደነቀ የተነገረኝ።
20. Greenfield, p.262



# ምዕራፍ ሠላሣ ስድስት
# የሴቶችና የልጆች ሚና

በኢትዮጵያና ጣልያን ጦርነት፣ የኢትዮጵያ ሴቶችና ልጆች ጥሩ ሚና ተጫውተዋል። የታሪኩን ሂደት ለመገንዘብ በዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ሥራዎችን እጠቅሳለሁ።

ለዘማች ሥንቅ የመሰነቅና ፈትሎ ልብስ የማዘጋጀት ሥራ፣ የሴቶች ሥራ ነበር። በሰሜኑም ሆነ በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባር ጠላት ሠብሮ እስከገባበት ጊዜ ድረስ ሴቶች የጎላ ተሳትፎ አላደረጉም፤ ከባሎቻቸው ጋር የዘመቱ እጅግ ጥቂት ነበሩ። ከቤተ መንግሥት ወገን የዘመቱ ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይለሥላሴ ብቻ ነበሩ። እቴጌ መነንም እንኳን ቢሆኑ ባላቸውን ጐትተው ወደ ውጭ አገር ከመውሰድ በስተቀር ሌላ ሥራ ለመሥራታቸው ተጨባጭ ማስረጃ የለም። ነገር ግን ጣልያን ድል አድርጐ ኢትዮጵያ ሲገባ ይህ ሥዕል ተለወጠ። ሴቶች የዜግነት ድርሻቸውን መወጣት ያዙ።

ሴቶች በአርበኝነት ጊዜ ምግብ የማዘጋጀት ኃላፊነት ነበረባቸው። እህል በታጣ ጊዜ ፍራፍሬ በመልቀም፣ ሥራ ሥር በመማስ ምግብ ያዘጋጃሉ። ትንሽ ዕረፍት በተገኘ ጊዜ ጫብሌ ቆፍረው፣ የቀጋ ፍሬ ለቅመው ብርዝ ያዘጋጃሉ።[1] ጠጅ ይጠምቃሉ። እህል ከተገኝም ጠላ ጠምቀው ያቀርባሉ። ቁስለኛውን ሕመምተኛውን ማስታመም የእነሱ ሥራ ነበር። በተለይ የሕፃናትና የሽማግሌዎች ሕይወት በእነሱ እጅ ወደቀ። ይህም እጅግ ከባድ ነበር።

የጠላትን ሁኔታ ለመሰለል፣ ምሥጢራዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ፣ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ችሎታ አሳይተዋል። ለምሣሌ በውስጥ አርበኝነት ረገድ የአዲስ ዓለምዋን ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌን መጥቀስ ይቻላል። እኚህ ሴት በአዲስ ዓለም አካባቢ ይንቀሳቀስ ለነበረው አርበኛ ምሥጢር ማቀበል ሥራ አድርገው ያዙ። ተከስሰው ከጦር ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ፦ "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ የኢጣልያ ባንዲራ ሲሰቀል አልቅሰሻል" ቢባሉ፣ "አዎን አልቅሻለሁ" አሉ። በዚህ ብቻ አላበቁም "የእናንተ አገር ሴቶች በሰው አገር ቀንተው የጣታቸውን ቀለበት፣ የአንገታቸውን ሐብል እያወለቁ ኢትዮጵያን ለመውረር ለመጡት ሽፍቶች ሲያበረክቱ፤ እኔ አገሬ በባዕድ ሕዝብ ስትወረር፣ መንግሥት ጠፍቶ የአገሩ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ ሌላ ሲሰቀል...ማልቀስ ይነስብኝ?" የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ከተግሣጽ ጋር አሰናበቱአቸው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ "ለአርበኞች ስንቅ ታቀብያለሽ፣ ቀይ መስቀልን ትረዳለሽ" ተብለው ተከሰሱ። እሳቸው "ስለነፃነት... ከአገሬ አርበኞች ጐን ተሰልፌ ጠላቴን መውጋት ቀርቶ፤ የረሐብና የጥም መድኃኒት እያዘጋጀሁ መላኩ ቁም ነገር ሆኖ ነው የተጠየቅኩት?" ብለው ጠየቁ። በዚህም አልበቃቸውም። "ይህንን ባላደርግ... እንኳን እነሱ እናንተም ትታዘቡኛላችሁ..." አሉአቸው። ጣልያኑም "እንግዲያ እኛን አትወጂንማ?" ቢላቸው፤ እሳቸው ደግሞ "አዎን አልወዳችሁም። ማነው ጠላቱን የሚወድ?" ብለው አረጋገጡለት። ከትንሽ ቀን እሥራት በስተቀር ምንም አላገኛቸውም።[2] አርበኞች የአዲስ ዓለምን ምሽግ ደጋግመው ለማጥቃትና ለመጨረሻም ለማስለቀቅ የቻሉት በቆፍጣናይቷ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ድጋፍ ጭምር ነው።

በሕክምና ሥራም የረዱ ብዙ ናቸው። ሰው በቆሰለ ጊዜ ደሙን አጥበው፣ መግሉን አጥበው፤ የተገኘውን የሀገር ባሕል መድኃኒት አድርገው፣ መግበው፣ ውሃ አጠጥተው ያድናሉ። የሞተባቸውም እንደሆነ ለማያውቁት ሰው ጭምር እርር ብለው አልቅሰው ቀባሪ ለምነው ያስቀብራሉ። በዚህ ያየሁትን ሁሉ ለመዘርዘር ከብዛቱ የተነሣ ይሳነኛል።

ሕክምናን በተመለከተ ወይዘሪት /ወይዘሮ/ ስንዱ ገብሩና ወይዘሪት /ወይዘሮ/ ጽጌ መንገሻ ሊጠቀሱ ይገባል። ወይዘሪት ስንዱ ከአዲስ አበባ ከአባታቸው ከከንቲባ ገብሩ ጋር ጐሬ ከተማ ገቡ። ወይዘሪት ጽጌ መንገሻ ደግሞ ከወንድማቸው ከአቶ ይልማ መንገሻ ጋር አምቦ ከተማ፣ ከጥቁር አንበሳ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። እነዚህ ሁለት ወጣቶች ጐሬ ከአለው ሀኪም ቤት ያገኙትን ያህል መድኃኒት ወስደው ጦሩ በየሄደበት ቦታ ሁሉ የህክምና አገልግሎት እስከ መጨረሻው፣ ማለትም ጦሩ እጁን እስከሰጠበት ቀን ድረስ በመርዳት አገልግለዋል። ደንበኛውን የቀይ መስቀል መለዮ አድርገው፣ እንደ ወንድ ኮትና ሡሪ ለብሰው፣ ቡሽ ባርኔጣ አድርገው በጦርነት ጊዜ የቆሰለውንና የታመመውን በማከም ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።[3]

በጦር ሜዳም እንደ ወንድ ታጥቀው የተዋጉ ብዙዎች ናቸው። ከቡልጋ ወይዘሮ ልክየለሽ በያን፣ ከመርሐቤቴ ወይዘሮ አሰለፈች ክብረ ሥላሴ፣ በወለጋ በኩል ወደ ሱዳን ከወጣው አርበኛ ወይዘሮ ከበደች ሥዩም እንዲሁም ወይዘሮ ወርቅነሽ ሲሣይ ሊጠቀሱ ይገባል።

ሴቶች በጦር ሜዳ ጀብዱ ለመሥራታቸው ማስረጃ ከአስፈለገ አንዲት ወይዘሮ የፈፀሙትን ማየት ይቻላል። ዊልያም ሚኪን የተባለ ታሪክ ፀሐፊ እንደተረከው የደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ሚስት ዶሎ በተባለው ቦታ የጠላት ጦር መምጣቱን ይረዳሉ። ሰው ተጉድቶ ነበርና



ባልየው ጦርነት ለመግጠም አመነቱ። ሴቲቱ የወንድ ልብስ ለብሰው፣ 150 ወታደሮች ይዘው በበቅሎ ገሥግሠው በጠላት ላይ አደጋ በመጣል ውጊያ ገጠሙ። የጠላት ወታደሮች በብርታት ስለተዋጉ፣ ሴቲቱ የጀግንነት ሥራ ሠርተው ከዚያው ከጦር ሜዳው ሞተዋል።[4] ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች ጦር ሲመጣ ቁቁ ይላሉ፤ ውጊያ ሲካሄድ እልል እያሉ ያበረታታሉ። እመስክርብሀለሁ እያሉ በማሳቀቅ ወንዱን ከሽሽት እየተመለሰ ከጦር ሜዳ ገብቶ እንዲዋጋ ያደርጋሉ። ናዳና መርግ እየለቀቁ ጠላትን ያጠቃሉ። የጦር ሠፈር እንዳይደፈር ይጠባበቃሉ።

ምክራቸውም ቀላል አልነበረም። ደጃዝማች አበራ ካሣ ከውርደትና ከሞት የደረሱት የባለቤታቸውን የወይዘሮ ከበደች ሥዩምን ቃል ባለመቀበል ነው። ደጃዝማች ተሾመ ሸንቁጥ በአርበኝነት ጸንተው በመቆየት ሊከበሩ የቻሉት የባለቤታቸውን የወይዘሮ አሰለፈች ክብረሥላሴን ምክር በመስማት ነው። የሴቶችን ብርታት ንጉሠ ነገሥቱም መስክረዋል። በትግራይ በተካሄደው ጦርነት አንዲት ሴት ጠላት አስገድዶ ሊያረክሳት ሲሞክር፤ በገዛ ጩቤው ልቡን ብላ ገድላ፣ መሣሪያውን ገፍፋ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጐን መሰለፍዋን ገልጸዋል።[5]

ጠላት የሴቱን ኃይል አልናቀም። በአገዳደል ረገድ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት አላሳየም። ሴቶቹን ረሽኖአል። በእሥራትም እንደዚሁ ሴቶች በሀገር ውስጥም፣ በውጭ አገርም ከወንዶች እኩል ታሥረዋል። በጠቅላላው ሲታይ በሴቶች ላይ የደረሰው ግፍ በወንዶች ላይ ከደረሰው የከፋ ነበር። በጦርነቱ የሞቱት እጅግ ብዙ ናቸው። የቆሰሉትም እንደዚሁ። በምርኮ ከጠላት እጅ የወደቁ እንደሆነ የሚደርስባቸው የአካል ጉዳትና የሚሰማቸው የመንፈስ ርክሰት አሰቃቂ ነበር። ክብረ ንጽሕናቸውን ያጡም አሉ። አንዳንድ ሴቶች የወር አበባቸው ይከብድና ይፈጥንባቸዋል፤ ውርጃ ያጋጥማቸዋል። ለመውለድ የታደሉም አሉ። በምርኮም በእሥራትም ጊዜ ከአቅማቸው በላይ የሆነ የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ ተገድደዋል። የዕድሜ ልክ ህመምተኛ የሆኑም ጥቂት አይደሉም።[6]

ልጆች የሠሩትም ቀላል አልነበረም። በተለይ በዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በላይ የነበሩት ይላላካሉ፣ የሚችሉትን ያህል መሣሪያ ይሸከማሉ፣ ዕቃ ያጓጉዛሉ። እንጨት ይሠብራሉ፣ ውሃ ይቀዳሉ፣ መኝታ ያዘጋጃሉ፣ ስንቅ ያቀብላሉ። ሴቶች በሌሉ ጊዜ ምግብ ያበስላሉ። ቀን ቀን ቃፊር በመሆን ሠራዊቱ እንዲያርፍ ያደርጋሉ። አንዳንዶችም መሣሪያ ጨብጠው ይዋጋሉ።

በአንፃሩ ደግሞ የአርበኝነትን ሥራ ካከበዱት ነገሮች አንዱ የጓዝ መብዛት ነው። ሕፃኑ፣ ሴቱ፣ ሽማግሌው፣ አሮጊቱ፣ ቁስለኛው፣

ሕመምተኛው፣ ከተዋጊው ሠራዊት መለየት አይችልም። ከተለየ፣ ከጠላት እጅ ይወድቃል። በጣልያኖች ዘንድ ሕፃን፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ቄስ፣ መነኩሴ ብሎ ነገር የለም። ነፍስ ያለው ፍጡር ከተያዘ፣ ምርኮኛ ነው። ምርኮኛ በሥርዓት እንዲያዝ በጄኔቫ ውል የተፈረመው ነጭ ነጭን ሲማርክ ብቻ ነው። ነጭ ጥቁርን ሲማርክ አይጸናም። ጥቁር ነጭን መውጋት በነጭ ዘንድ ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የተማረከው ሁሉ መገደል አለበት። በዚህ ምክንያት አርበኛው የሚንቀሳቀሰው ከተዋጊው ኃይል ሁለትም ሦስትም አጠፌታ የሚሆን ጓዝ ተሸክሞ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የምግብና የልብስ እጥረት ፈጠረ። የሠራዊቱንም የውጊያ ኃይል ቀነሰ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 191።
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 503-507።
3. *ታደሰ ሜጫ፣ ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 102።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 129-130።
5. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፡ 1ኛ መጽሐፍ*፣ገጽ 217።
6. ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 283።



# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት
# የውስጥ አርበኞች ተጋድሎ

በጦርነት ላይ የመረጃ ሠራተኞች ቁልፈ ሚና ይጫወታሉ። አፄ ምኒልክ ዐድዋ ላይ ያሸነፉት፤[1] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማይጨው የተሸነፉት፤[2] በመረጃ ጉዳይ እንደሆነ በታሪክ አንብበናል። አሁን ደግሞ አርበኞች በዚህ ረገድ የነበራቸውን አቅዋም እንመለከታለን።

ጣልያኖች ኢትዮጵያን ሲይዙ ምሥጢር የማግኘት አቅማቸው በሚያስገርም ሁኔታ ተቀነሰ። በጦርነቱ ጊዜ ተበታትኖ የነበረው የሕዝቡ ሥነ ልቡና ተመለሰ። ስለ ሀገር ጉዳይ ማሰብ፣ መቆርቆር ጀመረ። የአርበኝነት እንቅስቃሴን መደገፍ ጀመረ። ጣልያንን ጎትተው ያመጡት እነማን እንደሆኑ አወቀ፤ ምሥጢሩን ከእነሱ ደበቀ። ከነፃነት ታጋዮች ጋር ያለውን ወገናዊነት አጠበቀ።

ይህ ሁኔታ የውስጥ አርበኝነትን ሥራ ፈጠረ። ብዙዎች ሀገራቸውን ኢትዮጵያን በውስጥ አርበኝነት እንዲረዱ አደረጋቸው። እነዚህ ወገኖች ለአርበኝነት ሥራ መቃናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ሥራቸውን የሚያካሂዱት በማኅበርም በቡድንም፣ በተናጠልም በግለሰብም ሆኖ፤ የሚንቀሳቀሱትም ባመቻቸው ጊዜና ቦታ ነበር።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደገባ 12 ወጣቶች ተሰብስበው ስለሀገራቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተማከሩ። ጊዜ ካመጣው መንግሥት ጋር መስማማት የሚሻል የመሰለውም ነበር። ነገር ግን ተቀባይነት አላገኘም። የሀገር ፍቅር ያላቸው ወገኖች ተባብረው አንድ የምሥጢር ማኅበር አቋቋሙ።[3] ምንም የንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር በልጠባቸው ከእነሱ ጋር በማይስማሙ፤ እንዲሁም ሰዎች ላይ አንዳንድ ከሀገር ፍቅር የራቀ ሥራ ቢሠሩም፤ ጠላትን ድል ለመምታት በተካሄደው ትግል መልካም አስተዋፅኦ አድርገዋል። አባላቱ ተስማምተው መጋቢት 27 ቀን 1930 ዓ.ም አንድ መተዳደሪያ ደንብ አወጡ። ደንቡ 12 አንቀፆች ያሉት ሲሆን፤ ዓላማው አገርህን ውደድ፣ ንጉሥህን አክብር፣ ወገንህን ጠብቅ የሚል ነበር። ማኅበሩ ፕሬዚደንት፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ፣ አማካሪዎችና ተመልካቾች እንዲኖሩት ተወሰነ። አባል የሚሆኑ ሰዎች ማኅደራቸው ተመርምሮ ለኢትዮጵያ የመታመን ሥራ የሠሩ፣ ባይሠሩም ያልተቃወሙ ይሁኑ ተባለ (አንቀጽ 3)። ማኅበሩ ለኢትዮጵያ ሕይወታቸውን ላሳለፉ ሰዎች ልጆችና ቤተሰብ እንዲረዳ ተወሰነ (አንቀጽ 5)። የራስን ሀብትና ጥቅም ማደላደል ተከለከለ (አንቀጽ 9)፣ ምሥጢር ያወጣ እንዲጠፋ ተደነገገ (አንቀጽ 11)። ደንቡ እያደር ተሻሽሎ የውስጥ አርበኛው በደፈጣ አደጋ እየጣለ በጠላት ላይ የማይናቅ ጉዳት አደረሰ። የፖለቲካ እሥረኞችን፣ አቅም በፈቀደ መጠን ረዳ።

በተናጠል አርበኞችን ከሚረዱ ግለሰቦች ዋነኛዋ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሉ ነበሩ። ጣልያኖች ሲገቡ ቤታቸውን ለቀይ መስቀል አስረክበው ትግል ጀመሩ። የጠላት ማስፈራራትና እሥራት አልበገራቸውም። አርበኞች የአዲስ ዓለምን ምሽግ ለመሥበር የቻሉት በእሳቸው ምሥጢር ሥራ ነበር።[4]

የውስጥ አርበኞች እርዳታ ያደረጉባቸው መንገዶች ብዙ ነበሩ። ለአርበኞች መድኃኒት በማቀበል፣ የታመሙትን በማስታመም፣ የቆሰሉትን ደብቆ በማሳከም ረድተዋል። ነገር ግን ዋናው ዕርዳታ ይህ አልነበረም። ዋናው እርዳታ የጠላትን ሐሳብና የእንቅስቃሴ ዕቅድ ለአርበኞች አስቀድሞ ማስታወቅ፤ ጠላትን በምክር፣ በማስረጃ አቀራረብ፣ በጥቆማም ማሳሳት ነበር። በዚህ አደራረግ የውስጥ አርበኞች በጠላት ያደረሱት ጉዳት ቀላል አልነበረም። በአንድ ወቅት ጄነራል ናዚ፦ "ወዳጅ መስላችሁ ከምትጐዱን ከእናንተ ይልቅ ጠላቶቻችንን እናመሰግናቸዋለን። ጠላትነታቸውን በግልጽ አስታውቀውናልና" በማለት አስተርጓሚዎቹን እስከ መውቀስ መድረሱ በታሪክ ተመዝግቦአል። ተይዘውና ተከሰው የሚቀርቡ ሰዎችን ወንጀል ማቅለል፣ ማስረጃውን ማጥፋት፣ እሥረኞችን መርዳት፣ ሲቻልም እንዲያመልጡ ማድረግ፣ የሚፈቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ በድብቅ የታሠሩ ሰዎች ያሉበትን ለዘመዶቻቸው ማስታወቅና ዋስ ሆኖ ማስፈታት ዋና ዋናዎቹ ሥልቶች ነበሩ።

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳንገባ በሸዋ የነበሩ አርበኞች ከአዲስ አበባና ከሌሎችም ከተሞች ትኩስ ወሬ ይደርሳቸው እንደነበረና በዚያም ጥሩ ውጤት እንደተገኘበት እንገነዘባለን።

አርበኞች ንጉሥ አንግሠው በአዲስ ኃይል ሲንቀሳቀሱ፤ የጣልያን የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ሊሶና አዲሲቱን የቅኝ ግዛት ኢትዮጵያን በመጐብኘት በሀገሪቱ ላይ ሰላም መስራቱን ለዓለም የሚያስረዳ ጉብኝት እንዲያደርግ መወሰኑ ይታወሳል። የጉብኝቱም ጉዞ በአይሮፕላን ሳይሆን በባቡር እንዲሆን ተደረገ። ጉዞው በሦስት ተከታታይ ባቡሮች ነበር። የመጀመሪያው ባቡር መስከረም 30 ቀን 1930 ዓ.ም ዱከም ደረሰ። ባቡሩ ከከተማይቱ 4 ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ እንዳለ አርበኞች አደጋ ጥለው ብዙ ጣልያን ገደሉ። ሆኖም ሚኒስትሩ ከዚያ ባቡር ውስጥ አለመሆኑ እንደ ታወቀ፣ አቃቂ ከመድረሱ በፊት በሌላኛው ባቡር ላይ አደጋ ጥለው ብዙ ጣልያን ጨረሱ። ሚኒስትሩ ከዚያም ውስጥ አልነበረም።[5] ምናልባት በድሬዳዋና በናዝሬት መካከል ባቡር ሳይለወጥ አልቀረም። ምክንያቱም በወቅቱ የመጀመሪያውን አደጋ የጣሉት፣ አርበኞች በመጀመሪያው ውስጥ ስለመሆኑ ትክክለኛ ማስረጃ ደርሶአቸው ነበር።

እራሳቸው ከከተማ እየገቡ ምሥጢር የመሰብሰብ ሥራ ያካሄዱ ብዙ አርበኞች ነበሩ። በዚህ ዘዴ ሥሉጥ የነበሩት ዲማ ሰንበቱ ነበሩ። የእንቁላልና የዶሮ ነጋዴ እየመሰሉ እንደ ሸኖና ሰንዳፋ፣ አንዳንድ ጊዜም አዲስ አበባ



እየገቡ ምሥጢር በማግኘት አርበኞችን እያስተባበሩ በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።

ከጣልያኖች ከራሳቸው ጋር ግንኙነት መሥርተው መረጃ ማግኘት የቻሉ አርበኞችም ነበሩ። ለማስረጃም ያህል ቱኒቲ ኮሪያ የተባለ በጊና አገር ምሽግ የፖለቲካ ሹም የነበረ ጣልያናዊ እንዴት እንደተጠቀሙበት እጠቅሳለሁ። ይህ ሰው ዕርቅን ምክንያት በማድረግ በሙገሬ ዛላ አካባቢ ሲዘዋወር፣ ከጦር አዛዡና ከሠራዊቱ ጋር በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ተማረከ። ሳይገድሉትና ሳያጉላሉት በሰላም፣ ከነመሣሪያውና ከነሠራዊቱ ስለለቀቁት፣ ባለውለታ ሆኖ ምሥጢርም፣ መድኃኒትም ይልክላቸው ነበር። ዕርቅ በፈረሰ ጊዜ «ወልደፃድቅ ቪያ» በሚል አነጋገር፣ ያለአስተርጓሚ መልእክት በዘበኛው በኩል ስለላከባቸው፤ ምሥጢሩን በቅድሚያ አውቀው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረጋቸው ዕርቅ እንደፈረሰ ከደረሰው አደጋ ዳኑ።

ሙሴ ቀስተኛ አስታራቂ መስሎ ወደ ኦሮሞ አርበኞች ዘንድ በቀረበ ጊዜ፣ ስለአርበኞቹ ልዩ ጥናት አካሄዶ ነበር። የሚደልልበትንም ዘዴ አዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን አርበኞቹ ስለእሱ ማንነትና ምንነት፣ ስለዓላማውና ስለአስተሳሰቡ ጭምር ያውቁ ነበር። እሱ ስዊስ ነኝ ቢልም፣ በአድዋ ጦርነት ተማርኮ አዲስ አበባ የኖረ ኢጣልያዊ መሆኑን፤ እነ ራስ ደስታ የነበሩበትን አካባቢና ሁኔታ በአስታራቂነት ቀርቦ ማስፈጀቱን፤ ባላምባራስ አበበ የራስነት ማዕረግ በተሾሙ በአንድ ሣምንት ውስጥ ከምንጃር እስከ ጌልጌላ ሄዶ በማነጋገር ሁኔታቸውን ሰልሎ ለጣልያኖች መረጃና ምክር በመስጠት እንዳስደበደባቸው፣ የኦሮሞው አርበኛ ያውቅ ነበር።[6] በመሆኑም አርበኛው ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ፣ እሱ ከተሰለፈበት ሤራና ከሚያስከትልባቸው ጉዳት ራሱን አዳነ።

በጐንደር በኩል የነበረው የውስጥ አርበኝነት ሥራ ዩተጠናከረና የውጭ አገር ሰውንም ያካተተ ነበር። ኪጃ ኃይሉ የተባሉ በሱዳን ሀገር፣ ዱካ በተባለው ቦታ የሚኖሩ የወላይታ ባላባትና ባለቤታቸው ወይዘሮ ደስታ አበባየሁ ያደረጉት ዕርዳታ ከሁሉም የላቀ ነበር። ጦርነት ሰልችቶት ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን የሚሰደደውን፣ ሱዳን በመግባት አገግሞ ትግሉን ለመቀጠል ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሰውን ሁሉ ረድተዋል። ለድካሙ ማረፊያ፣ ለረሐቡ ምግብ፣ ለጥሙ መጠጥ፣ ለእርቃን ሥጋው ልብስ ሆነውታል። መንገድ መሪ፣ ሽኚ እየሰጡ አስተላልፈውታል። ለዚህ ሥራ ያዋሉት ገንዘብ ከ44 ሺህ ብር በላይ ተገምቶአል። ራሳቸው ከመርዳታቸውም በላይ የሱዳን ተወላጅ የሆኑ ወዳጆቻቸውን በማኀበራዊ ኑሮና በፍቅር እየጐተቱ፣ የኢትዮጵያን ጥቃትና የኢትዮጵያውንን ተጋድሎ እያስረዱ፣ አርበኞችን እንዲረዱ አድርገዋል።

ከዚህም በስተቀር በጋላባት፣ በገዳሪፍ፣ በከሰላና በካርቱም የነበሩ ኢትዮጵያውን በውስጥ አርበኝነት ሠርተዋል። ሥራቸው በጣልያኖች ዘንድ

እየታወቀ በብዙዎቹ ላይ ተደጋጋሚ ክስ ቀርቦባቸዋል፤ ወቀሳም፣ ቅጣትም ደርሶባቸዋል። ነገር ግን የተሠነዘረባቸውን ጥቃት እርስ በርስ በመረዳዳት ተወጥተውታል። ግዛው ውቤ የተባለ ሰው ስድስት አልቤን ጠመንጃ ከጠላት ወስዶ ቤቱ ሲፈተሽ ሳይገኝበት ቀርቶአል። ሳይገኝበት የቀረውም አንዱ ሀገር ወዳድ ጊዜ የለኝም በማለት ፍተሻውን ለማግስቱ በማሳደሩ ነው፤ ሌላው ደግሞ ምሥጢሩን በመንገሩና በአካባቢው የሚኖሩ ሴቶች ጠመንጃዎቹን ተከፋፍለው በመደበቃቸው ነበር።

በውስጥ አርበኝነት ከረዱ ቡድኖች ጠንካራው የኤርትራ ልጆች ነበሩ። እንደዛ ሊሆን የቻለበት ምክንያት፣ በአስተርጓሚነትና በልዩ ልዩ የጽሕፈት ቤት ሥራ በመመደባቸው ምሥጢር ለማግኘት መቻላቸው እና በኢጣልያኖች ዘንድ የመደመጥ ዕድል ስለነበራቸው ነው። ስለዚህ ብዙ ሥራ ለመሥራት ችለዋል። ከጠላት ጐን የተሠለፉትን ወገኖቻቸውን በምሥጢር እየተጻጻፉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዞሩ አድርገዋል። ምሥጢር ወደ ውጭ አገር በማስተላለፍና ከውጭ አገር የሚያገኙትን ወሬ ወደ አርበኞች እንዲደርስ በማድረግ ረድተዋል። በአስተርጓሚነት የሚሠሩ ደግሞ በዘዴ በመሥራት ብዙ ሰው ከሞት አድነዋል። ለማስረጃም ያህል ፊታውራሪ ብጡል ሊሰቀሉ በቀረቡ ጊዜ፤ የቀበሩት መሣሪያ ሊኖር ስለሚችል መሰቀላቸው ቢቆይ ይሻላል ብለው ለጣልያናዊው መኰንን በማማከር አድነዋቸዋል። አቶ አስናቀ ፈለቀ የወሬ መቀበያና ማስተላለፊያ መሣሪያ ቀብረዋል ተብሎ በቀረበባቸው ክስ ሊገደሉ ሲፈለጉ፤ ምሥጢሩ ስለተነገራቸው ሸሽተው ለማምለጥ ችለዋል። አቶ ተገኝ ዮሴፍ እንግሊዝኛ በማወቃቸው ሊገደሉ ታስቦ ዝግጅት እየተደረገ ሳለ ምክር ተሰጥቶአቸው በመሸሽ ነፍሳቸውን ድነዋል። በዚህ ዓይነቱ ሥራ የእነ ቀኛዝማች ኪዳኔ መሰለ፣ ስብሐት አጽብሃ፣ ምህረተ አብቀልቲ፣ ደጃዝማች ሮዛሪዮ፣ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ ስም በክብር ይጠቀሳል።[7]

የጐጃም አርበኞችም እንዲሁ የውስጥ አርበኝነት ሥራ አልተለያቸውም። በተለይም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ። እሳቸውም በሚያገኙት ምሥጢር የመጠቀም ችሎታ ነበራቸው። ታህሣሥ 4 ቀን 1930 ዓ.ም አርበኞችን ለማፈን ጠላት ወደ በከና የሚንቀሳቀስበትን ሁኔታ ሰላዮቻቸው ስለነገሩአቸው፣ ገስግሰው ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ባሳሰበው ቦታ አደጋ ጥለው ሊያጠፉት ችለዋል። እንደዚሁም ጠላት ታህሣሥ 9 ቀን አደጋ ሊጥልባቸው በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ስለሰሙ፣ አስቀድመው ታህሣሥ 7 ቀን 1930 ዓ.ም ሙጋ በተባለው ምሽግ ላይ አደጋ ጥለው ምሽጉን አቃጥለዋል። ግንቦት 2 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ወሎ ተሻግረው አንድ ቀንደኛ ባንዳ ቤት ተሰብስቦ ይዶልት የነበረውን የጠላት ጦር አውደመውታል። ለመታረቂያ ይዞአት የነበረችውን የሻሸወርቅ የተባለች ልጃቸውንም ከደብረ ማርቆስ ወህኒ አስርቀው ለመውሰድ ችለዋል።[8]



ብዙ ጀግኖች ከውስጥ አርበኞች ተመሣሣይ ደጋፍ ያግኙ እንጂ፣ ሂደቱ ሌላም መጥፎ ገጽታ ነበረው። ምክንያቱም በአርበኞች ውስጥ ተሰግስገው ጐጂ ሥራ የሚያካሂዱ አልታጡም። በዚህ ረገድ በጉራጌ አገር መንገድ እንመራለን ብለው፣ ገንዘብ ተቀብለው ራስ ደስታንና ሠራዊታቸውን ያስፈጁት፤ በቡልጋ ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴና ባልደረቦቻቸውን አስይዘው ያስጨረሱት፤ ተመሳጥረው ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን በመርዝ የገደሉት፤ ጄነራል ናዚን ጠልፎ በማገቻነት በመያዝ፣ ለእርቀ ድርድር መነጋገሪያ ለማድረግ የታሰበውን ዓላማ አስቀድመው ምሥጢሩን በመንገር ያከሸፉት፤ መንገድ እንመራለን በማለት ከተቃጠለ ግንብ ውስጥ አስገብተው ለጣልያን ባለሥልጣኖች ምሥጢሩን በመንገር ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህንን ከነሰዎቻቸው ያስፈጁ ከሀድያን ይጠቀሳሉ።[9]

## <u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ጆርጅ ኦፍ ኤች በርክሌይ፣ *የዐድዋ ዘመቻና የአፄ ምኒልክ አነሣሥ*፣ ትርጉም ዳኘው ወልደሥላሴ፣ ገጽ 93።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 116።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባሳሽኝ ዘመን*፣ ገጽ 60-79።
4. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 503-515።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 176።
6. *ታቦር ዋሚ፣ አባ በራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎች አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 58-61።
7. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 154-156፣ 58-61፣ 173-174 እና 212-213።
8. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር፣ የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 13-15 እና 22።
9. ድርጊቶቹን ከታሪካቸው ይመልከቱአል።

# ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት
# የስደተኛው ትግል

ትክክለኛ ኢትዮጵያዊ ሽሽትን ከውርደት፣ ውርደትን ደግሞ ከሞት በላይ አድርጐ ይመለከታል። በአለበት ቆሞ የመጣበትን መቀበልን ይመርጣል። አገሩን ለቅቆ የመሰደድ ልማድ ግን ፈጽሞ አልነበረበትም። አሁን ግን የተለመደ ሆኖአል።

ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ አውሮፓ ሄዱ። ዝርዝሩ በሌላ ምዕራፍ ስለተገለፀ አልመለስበትም። ይህ ምዕራፍ የሚገልፀው የሠራዊቱን የስደት እንቅስቃሴ ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ለቅቀው መሄዳቸው በመሣፍንቱና በመኳንንቱ ዘንድ ወዲያው ታወቀ። እንዲያውም አብዛኛው አስቀድሞ አውቆ እና አቀብቁቦ ይጠባበቅ ስለነበር፣ አዲስ ነገር አልሆነበትም። የተወሰኑት ንጉሠ ነገሥቱን ተከትለው ጥዋት በባቡር ወደ ጅቡቲ ወጣ። የኦጋዴን ጦር አዛገርች፣ በጅጅጋ አድርገው በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ወደ በርበራ ሄዱ። በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በባሌና በሲዳሞ የነበሩት ደግሞ የሞተው ሞቶ የቀረው በወላይታ፣ በባኮጋዘር አድርገው ወደ ኬንያ ገቡ። በከፋና በጋሞ ጎፋ የነበረውም እንደዚሁ ሽሽቱን ቀጠለ። ከአዲስ አበባ በመርሐ ቤቴና በግንደ በረት ወደ ጐጃም የተሻገረው ደግሞ፣ በወንበራ በኩል አድርጐ ቡሬ ሳይገባ ሱዳን ጠረፍ ደረሰ። ሌላ አንድ ቡድን በራስ እምሩ ታዝዞ ልብስና መድኃኒት ገዝቶ ሊያመጣ ከደባርቅ በመተማ በኩል ሱዳን ገብቷል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ባልለመደው ዓይነት ተበታትኖ ወደ ውጪ አገር በስደት መሄዱ አሳዛኝ ነበር። ጉዞው አድካሚ ከመሆኑ ጋር ብዙ ሰው በመንገድ ላይ አለቀ። ያጋጠመው ሌላው ችግር፣ አብዛኛው ወደ ተሰደደበት አገር ከገባ በኋላ፣ ሀገሩንና ምግቡን ባለመልመድ በልዩ ልዩ በሽታ ሞተ።

ስደት በዚያን ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰው እንግዳ ነገር ነበር። ለተሰደደ ሰው መራብ፣ መጠማት፣ መታረዝ፣ መጠለያ ማጣት ያለ ነገር ነው። መታመምና መሞትም አለ። ሥራ አይገኝም፤ ቢገኝም አሠራሩ አይታወቅም። የሚገኘው ደግሞ እንደ ጽዳት፣ ዘበኝነት ያለ ነው። እሱም በፈረንጅ ፈቃደኛነት እና በእሱ ቁጥጥር ስለሆነ፣ ይከብዳል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን አልረሱም፤ ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር ጠነከረ እንጂ፣ አልተቀነሰም። ሁሉም በየአለበት ሀገሩን ለመደገፍና ወገኑን ለመርዳት፣ ጣልያንን ለማዋረድና ለመጉዳት የሚቻለውን አደረገ።

ዋናው የስደተኛ ቡድን እንግሊዝ አገር የገባው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ስለነበር፣ ቁጥሩም አነስተኛ ቢሆን ብርታት አገኘ። የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም ማኅበር ለማቅረብና ድምፅዋን ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሰማት ጥረት አደረገ። አንዳንድ እንግሊዞችም ደገፉት። ከዚህ ላይ ስማቸው መጠቀስ ያለበት



ሚስስ ሲልቪያ ፓንክረስት ናቸው። እኚህ ወይዘሮ አቅማቸውን አጠንፍፈው ለኢትዮጵያ ጉዳይ አዋሉ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በስደት ሳሉ።

እየሩሳሌም የገባው ሰው ብዙ አልነበረም። ሦስት መቶ ቢሆን ነው። የሀገሩ ፍቅር እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተመስጦም ነበረው። በገዳሙ ከነበሩት መነኮሳት አብዛኞቹ ተባበሩ። ገዳሙን ለመያዝ ጣልያኖች ያደረጉትን ሙከራ አከሸፈ። በገዳሙ ተሰቅሎ ይውለበለብ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለማስወረድ ያደረጉትን ጥረት ተናንቆ አሸነፈ። በገዳሙ ውስጥ የነበሩትን መዛግብት ለመውሰድ ያደረጉትን ሙከራ አከሸፈ። በወቅቱ በዛ ባለሥልጣን የነበረው የእንግሊዙ አገረ ገዥ፣ በገዳሙ ውስጥ እጁን ለማስገባትና እሱ የወደደውን ለማድረግ ያደረገውን ሙከራ አስቀረ። እየተከራዩ፣ ለኢትዮጵያ ስደተኞች የሚረዱባቸው ቤቶች ወደ ጣልያን እንዲዛወሩ እንግሊዝና ጣልያን የሠሩትን ሤራ በፍርድ ቤት ተከራክሮ አፈረሰ። ተስፋ የተባለውን ማኅበር አቋቁሞ የኢትዮጵያን ስደተኛ ወጣቶች ረዳ። ከአርበኞች ወደ አውሮፓ፣ ከአውሮፓ ወደ አርበኞች መልእክት በማስተላለፍ ተጋድሎውን አጠናከረ።[1]

ሸሽቶ ከሄደው፣ በርከት ያለው ስደተኛ የገባው ወደ ሱዳን ነው። ምናልባት አሥራ አምስት ሺህ ሳይሆን አልቀረም። ቀደም ብለው በዚያ የነበሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያንም ብዙ አስተዋጽኦ አደረጉ። በጋምቤላና በመተማ በኩል መልእክትም፣ ዕርዳታም አስገቡ። አንድ ቡድን ከካርቱም ልብስና መድኃኒት ገዝቶ በጋምቤላ በኩል እስከ ጐሬ አምጥቶ በራስ እምሩ



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በስደት ሳሉ።

ለሚመራው አርበኛ አስረክቦአል::[2] የኢትዮጵያን አርበኞች እንቅስቃሴ ወደ አውሮፓ በማሰማት እና ከአውሮፓ የሚገኘውን ወሬ ለአርበኞች በማድረስ ለጦርነቱ እገዛ አድርጓል:: በሱዳን የነበሩ ስደተኞች በፈቃዳቸው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ የተዋጉበትም ጊዜ ነበር:: ንጉሠ ነገሥቱም በዚያ በኩል ለመምጣትና ወደ ሀገራቸው ለመግባት ያገዛቸው፣ በሱዳን በርካታ የኢትዮጵያ ስደተኞች መኖራቸው ነው:: ንጉሠ ነገሥቱ ካርቱም ገብተው አዲስ ጦር ለማዘጋጀት በጀመሩ ጊዜም ስደተኛው አገዟል::[3] ስደተኛው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ከገባ በኋላ፣ ምድር ሰቅስቆ ተዋጋ::

ሌላው ቡድን ወደ ኬንያ የተሰደደው ነው:: ብዛቱ እስከ አሥር ሺህ ይገመታል:: በኬንያ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያውያንን እና ኤርትራውያንን ለያዩአቸው:: ኢትዮጵያውያኑን ከሀሮ ወደ ኢሲሎሎ፤ ከዚያም ወደ ታቤታ አዛወሩአቸው:: ታቤታ የተባለችው መንደር በኬንያና በታንዛንያ ድንበር ላይ የምትገኝ መንደር ናት:: በዚች መንደር የአይጥ መንጋ ገብቶ ችግር ፈጥሮ እንደነበረ ብዙዎች ያስታውሳሉ:: ንጉሠ ነገሥቱ ካርቱም እንደገቡ በኬንያ ካለው የኢትዮጵያ ስደተኛ፣ ለጦር የሚያገለግለው ወደ ሱዳን መጣ::[4]

ሌላው ስደተኛ ቡድን ከኦጋዴን የጦር ግንባር፣ ከጣልያን ጥቃት አምልጦ በጅጅጋ በኩል በርበራ የገባው ነበር:: ይህ ቡድን በቁጥር አነስተኛ ነው፤ የቡድኑ ዋና ዋና ሹማምንቶች ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ፣ አብዛኛው ከዚያው ቆይቶ ነበር:: አንዳንዱም ወደ የመን ተሻግሮ ከቆየ በኋላ፣ የነፃነት ጦርነት ሲጀመር ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተቀላቅሎ እየተዋጋ ሐረር ገባ::[5]

የኢትዮጵያ ስደተኛ በየትኛውም በር ቢወጣ፣ የገባው ከእንግሊዞች እጅ ነበር:: በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን የሱዳንን፣ የኬንያን፣ የሰሜን ሱማልያን፣ የፍልስጤምና የየመንን አገር በቅኝ ገዥነት የያዙ እነሱ ነበሩ:: እንግሊዞች የጊዜው ሁኔታ በሚፈቅድላቸው መጠን የኢትዮጵያን ስደተኛ ረድተዋል:: አንቀበልም ወይም አናስገባም አላሉትም፤ እየመለሱ ለጣልያን አልሰጡትም:: ሞሶሎኒ ያካሂድባቸው ከነበረው ተፅዕኖ አንፃር ሲታይ፣ የሚያስመሰግናቸው ነው:: የየሀገሩም ተወላጆች ስደተኛውን አቅማቸው በፈቀደላቸው መጠን ደግፈውታል:: ለታሪክ ጭምር፣ ይህንን መመስከር ይገባል::

ቀደም ብለው አሜሪካ ሄደው የነበሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁ የተቻላቸውን ያህል ተፍጨርጭረዋል:: ለምሳሌ ወላጆቻቸው ሄደው ከዚያ የተወለዱ ክልሶች፣ እነ ሻለቃ ካሣ ሊጠቀሱ ይገባቸዋል:: ዶክተር መልእኩ በያን ታላቅ ሥራ ሠርተዋል:: በዚያ የነበረው ቡድን መስከረም 2 ቀን 1929 ዓ.ም "…ሀገራችንን የምንለቅ ሰዎች አይደለንም:: ጠላቶቻችን የያዙብንን መሬት ለቅቀው እስኪወጡ ድረስ ተኩስ አይቆምም…" በማለት በይፋ አስታወቀ:: "ምኒልክ" የተባለ ክበብ ተቋቋመ:: ክበቡ ሃያ ሁለት ቅርንጫፎች



ነበሩት:: የኢትዮጵያ ድምፅ የተሰኘ ጋዜጣም ተቋቋመ:: በዚህ ጋዜጣ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን የአርበኝነት ሥራ ለአሜሪካን ሕዝብ ለማስታወቅ ተቻለ::[6] ይኸ በመሳካቱ ደግሞ፣ አሜሪካ ለጣልያን የምትሰጠውን ድጋፍ ቀነሰ::

በፈረንሣይ አገርም ጥቂት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ነበሩ:: የኢትዮጵያ አምባሳደር የጣልያንን ጥሪ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ ወጣት አክሊሉ ሀብተወልድ ግን በዛ የጉዳይ ፈፃሚነቱን ሥራ ቀጠሉ:: ከባድ የፖለቲካ ተፅዕኖና ብዙ የገንዘብ ችግር ቢደርስባቸውም፣ ፈረንሣይ ራስዋ በጀርመን እስከ ተወረረችበት ጊዜ ድረስ፣ ኤምባሲው ሳይዘጋና ኢትዮጵያ በፈረንሣይ መንግሥት ዘንድ የነበራት ዕውቅና ሳይሠረዝ እንዲቀጥል አደረጉ:: ኤምባሲውም፣ በዓለም መንግሥታት ማኅበርና ለንደን በነበሩት በንጉሠ ነገሥቱ መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ አገለገለ::[7]

በሌሎች አገሮች የነበሩ ኢትዮጵያውያንም የየአቅማቸውን ያህል ተፍጨርጭረዋል:: በጂቡቲ በኩል የነበሩት መልእክት በማስተላለፍ ረድተዋል:: ግብጾች ከኢትዮጵያ ይልቅ ወደ ጣልያን ስለአደሉ፣ በዚያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች አስተዋጽኦ የማድረግ አቅማቸው ውስን ነበር::

በውጭ አገር በተካሄዱት ትግሎች አስገራሚው በጣልያን፣ በራስዋ አገር ውስጥ የተካሄደው ነበር:: በዛ የማበሳጨቱም ሥራ አንዱ የትግል መሥመር ነበር:: በእሱ ደግሞ እሥረኞችም እንኳን አልተመለሱም:: ለምሣሌ ራስ እምሩ በፖይዛ ደሴትበቁም እሥር ላይ በነበሩበት ጊዜ፤ ከሞሶሎኒ ተልከው ለመጡ ሁለት የኢጣልያ ከፍተኛ ሹማምንት ወንበር እንዳይቀርብላቸው በማገድ፣ እሳቸው ተቀምጠው እነሱ ቆመው እንዲያነጋግሩአቸው አስገድደዋቸዋል:: አዲስ አበባ የሚገኘው ቤት ንብረታቸው እንዲመለስላቸው ሞሶሊኒ መወሰኑን ሹማምንቱ እንደ ቆሙ ቢነግሩአቸው "…የእኔ የነበረው ሁሉ የኢትዮጵያ ነፃነት ሲጠፋ አብሮ ጠፍቶአል:: የጣልያን መንግሥት ለወደደው ይስጠው" በማለት አናደዱአቸው:: ሌፖሪ ወደምትባል የእሥራታቸው ደሴት ሲጓዙ ደግሞ፣ ሻንጣቸውን ላለማስፈተሽ ቁልፉን አልሰጥም አሉ:: በልመና ሲሰጡ ከሻንጣቸው ውስጥ ቀድሞ የተሸለሙት ከፍተኛ የጣልያን ኒሻን አላግባብ ተጥሎ ተገኘ:: በሥርዓት እንዲያስቀምጡ ቢጠየቁ ለእሳቸው ኒሻኑ ከአፈር አንድ እንደሆነ ገልጸው፣ ቢፈልጉ እንዲወስዱት ለፈታሾቹ ፈቀዱላቸው:: ፈታሾቹ ተናድደው መፈተሻቸውን ተዉ::[8]

ጣልያኖችን ከማበሳጨት፣ ራስ ኃይሉም እንኳ አልበዙኑም:: ሮም ከተማ በቆዩበት ጊዜ ማንኛቸው ሽንታቸውን እንደሚችሉ ለማየት ከራስ ሥዩም ጋር ተወራርደው፣ አንድ እሁድ ከጥዋት ጀምረው ከተማዋን ሲዞሩ ከዋሉ በኋላ፣ ውሃ ከሚንፎለፎልበት ፒያሣ ቬነሲያ ከሚባለው አደባባይ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ደረሱ::—ክአደባባዩ ላይ ሽንታቸውን ሸኑ:: በዚህ

ምክንያት ተይዘው ሃያ ሁለት ሊሬ ተቀጡ። ሆኖም ያላቸው ገንዘብ ባለ አንዳንድ ሺህ ሊሬ ብቻ ስለሆነና ፖሊሱም መመንዘር ስላልተቻለው፣ ራስ ሥዩም አንዱን ሺህ ሊሬ ከፍለው፣ ሸንተው ሄዱ ይባላል። ራስ ኃይሉ አዲስ አበባ በነበሩት ጊዜ የጣልያኖች አያያዝ እያስቀየማቸው ሲሄድ ፊታቸው ሲያኮሳትሩ፣ አለቅዬው «ፊትህ የዝንጀሮ ይመስላል።» ቢላቸው «የአንተ ደግሞ ቂጥዋን ይመስላል።» ብለውት እንደነበር ጠቅሻለሁ።

በግዞት ላይ የነበሩ ሌሎች እሥረኞችም ጣልያኖችን በነገር ለመጉንተል ቸል አላሉም። እነዚህ ፈሊጦች ግን ኢትዮጵያውያን በጣልያናውያን ያላቸውን ጥላቻና ንቀት ከመግለጽ በስተቀር ሌላ ፋይዳ አልነበራቸውም። ቢሆንም በታሪክ መጠቀስ ስለሚገባቸው፣ እጠቅሳለሁ።

ከእነኛ፣ ኢትዮጵያውያን በጣልያኖችና በኢጣልያ በራስዋ ላይ ከፈፀሙት ሁሉ ግን የበቁ ሥራዎች አሉ። እነሱም፦ ዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋ የፈፀሙትን የሚያህል እና የሚመስል፣ እንዲሁም የሚስተካከል የለም። ዝርዝሩን መመርመር ይገባል።

ዘርዓይ ደረስ ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁን 14 ቀን 1938 እ.ኤ.አ/ በሮም ከተማ፣ በአንድ የመንግሥት አደባባይ ላይ በጐራዴ ብዙ ጣልያኖች ጨፈጨፈ። የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ነገሩ ውርደት ስለሆነባቸውና በምሥጢር ስለያዙት ስንት ሰው እንደሞተ በውል አልታወቀም። እጅግ ቢያንስ አምስት ሬሣ ከአደባባዩ መለቀሙ እርግጥ ነው።[9] ቁጥሩን እስከ አሥራ ስምንት የሚያደርሱም አሉ። በትርምሱ ጭምር ብዙዎች መቁሰላቸው እውነት ነው።

ዘርዓይ ደረስ የኤርትራ ተወላጅ የሆነ፣ በወቅቱ የ24 ዓመት ወጣት ነበር። በዚህ ከላይ በተጠቀሰው ታሪካዊ ቀን በመንግሥት አደባባይ ህዝብ የተጠራው በዶጋሊ ያለቁትን አምስት መቶ ጣልያናውያን ለማሰብ ነበር። በስብሰባው ላይ ሣልሣዊ ኢማኑኤልና ሙሶሊኒም ይገኙ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ ከአደባባዩ እንዲገኝ የተደረገው የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ የወግ ዕቃዎች ይዞ ፒያሣ ዲ ፒያሞንቴ በተባለው አደባባይ ለማላገጫነት እንዲቆም ነበር። ከያዛቸው ዕቃዎች አንዱ በዶጋሊ ጦርነት በጥር ወር 1871 ዓ.ም /1879 እ.ኤ.አ / ራስ አሉላ አባ ነጋ ጀብዱ የሠሩበት ጐራዴ ነበር። ዕቃዎቹን ይዞ እንዲሄድ ከመታዘዙ በስተቀር፣ ለመሳለቂያነት መቆም እንደ አለበት ለዘርዓይ ደረስ አልተገለጸለትም ነበር።

ዘርዓይ ከአደባባዩ ሲደርስ እንግዳ ነገር አጋጠመው። ቀድሞ አዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ መግቢያ አደባባይ ተተክሎ የነበረውና፤ አሁን ተመልሶ በቀድሞ ቦታው (በለገሃር) የሚገኘው የይሁዳ አንበሳ ሀውልት፣ የሮም ከተማ ሕዝብ በዓል ሊያከብር በተሰበሰበበት አደባባይ ላይ ቆሞ አየው። በዛ ግን ከሃውልቱ ላይ ሁለት ግልገሎች የምታጠባ ተኩላ ተቀምጣበታለች፤ በአንበሳው መስቀል ላይ ደግሞ የጣልያን ባንዲራ ተሰቅሎአል። የኢትዮጵያ



ሰንደቅ ዓላማ ከመሬት ላይ ተጥሎአል። በዙሪያው ከተጻፉ መፈክሮች መካከል "...የይሁዳ አንበሳን ልጆችሽ.. እንደ ፍየል ጭራውን ጠምዝዘው አምጥተው ከእግርሽ ሥር ያሰግዱታል" የሚል ጥቅስ ከብዙ ነውረኛ መፈክሮች መካከል ይታያል። ሕዝቡ እያስካካ ምራቁን በአንበሳው ላይ በመትፋት ያፌዛል።

ዘርዓይ ደረስ ሁኔታውን በመገረም ሲመለከት ማርሻል ማሪዮ ኢሶን የተባለ የዘበኞች አለቃ ወደ እሱ ቀርቦ መመልከት እንደማይችል ነገረው። መናደዱን አይቶ ሳይሆን አልቀረም፣ ከዚያ አካባቢ ሊያባርረው ሞከረ። ዘርዓይ "...እናንተ የምታዩትን እኔ የማላይበት ምን ምክንያት አለ" ሲል ጠየቀ። የዘበኞቹ አለቃ ጥያቄውን ከድፍረት በመቁጠር "ከእንግዲህ አንበሳ የለም። ...ለተኩላዋ ልትሰግድና ልታመልካት ይገባሀል" አለው። ዘርዓይም ይህ አይደረግም አለ። ክርክሩ ከረረ። ማሪዮ "ከእንግዲህ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ልነግርህ እወዳለሁ።...ያውም ንጽሕናውን ያሻሸል እንደሆነ......" አለ። ዘርዓይም በእልህ ተከራከረ። አንበሳው ከአንድም ሁለት ጊዜ ሰብሮ ድራሻቸውን እንደ አጠፋው ገለጸለት። ማሪዮ ደግሞ "...ከጀርባው ላይ ወጥታችው አሳዩት፣ የአንበሳውን ቁርጥ ይወቀው..." የሚል ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ሰጠ። ሕዝቡ ጭምር ከአንበሳው ላይ ለመውጣት ተተረማመሰ።

ዘርዓይ ደረስ ሥራውን የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። በያዘው ጐራዴ ጣልያኖችን ጨፈጨፋቸው። የዘበኞች አለቃ ማረሻል ማሪዮ ኢሶን በአንበሳው ዙሪያ እንደከብት አንከራትቶና እንደ ሕፃን አስለቅሶ፣ በአንበሳው እግር ሥር አሰግዶ፣ እጅና እግሩን ቆራርጦ ከመሬት ጣለለት። የሌሎችንም ሬሣ እየተጐተቱ በአንበሳው ሀውልት ሥር ረፈረፈው። እሱም ራሱ ከዚያች ንቅንቅ ሳይል ቁጭ አለ።

በከተማው ሽብር ተነሣ። "ኢትዮጵያ ሰብራ ገብታ ሕዝቡን በጐራዴ ፈጀችው።...ጠላትህን ቶሎ ታጥቀህ ራስህን ተከላከል..." ተብሎ ታወጀ። በያለበት ተኩስ ተከፈተ። በአደባባዩ ላይ በመተረማመስ ከአለቀው በተጨማሪ፤ በከተማይቱ ውስጥ እርስበርሱ ተላለቀ።

ዘርዓይ ደረስ ጭፍጨፋ የጀመረበት ትክክለኛው ሰዓት አልተመዘገበም። ከጥዋቱ ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ሳይሆን አልቀረም። ሽብሩ ቀኑን ሙሉ ውሎ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ተኩል ላይ አገርዋ ሰላም መሆንዋ፤ ሽብር የተነሣው አንድ ዕብድ በሽታው ተነስቶበት እንደሆነ የሚገልጽ አዋጅ ተለፈፈ። የአዋጁ ቃል ይህ ብቻ አልነበረም። "... ወደ ፒያሣ ኢዝድራ ሄዳችሁ እጁን ያዙ..." የሚል ትዕዛዝም ነበረበት። በዚህ ትዕዛዝ ምክንያት የከተማው ሕዝብ እንደገና ተነቅንቆ ወጣ።

ዘርዓይ ደረስ ሰውነቱ እንደ ነብር ተነፋ። በተኩላዋ ሀውልት ላይ ቁሞ በመጮህ ሕዝቡን ዝም አሰኘው። "...በየቤታችሁ እየዞርኩ ብዙ ሰው አርድ ነበር። ግን እኔን አሥሮ የያዘኝና አኮራምቶኝ የዋለው የአንበሳው ፍቅር ነው። ደግሞም አሟሟቴ ከአንበሳው ሥር እንዲሆንልኝ ፈልጌ ነው።...ወንድ

ይምጣና ይማርከኝ" አላቸው። ከተኩላዋ ላይ ወርዶ አንበሳውን እየዳሰሰ ቆመ።

አውቶማቲክ መሣሪያ የያዙ ወታደሮች በሞተር ሳይክል፣ በሁለት አቅጣጫ በመምጣት ተኩሰው መቱት። ጉራዴውን መዝዞ እንደገና ወደ ሕዝቡ ገሠገሠ። ከተማይቱ በተኩሱና በሽሽቱ ምክንያት እንደገና ተሸበረች። ዘርዓይ ተመልሶ ቢወድቅም ሊቀርበው የደፈረ የለም። ለአዲስ ሥራ እንደገና ተንቀሳቀሰ። ከወደቀበት ጉራዴውን ይዞ ተነሣ። ከመሬት ወድቆ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማንሳት በደሙ ለውሶ ከአንበሳው ላይ ሰቀለው። ከተኩላዋ ላይ የነበረውን የጣልያንን ባንዲራ ሕዝቡ እያየ አወረደው። ቀድዶ ከመሬት ጣለና በእግሩ ረገጠው። ሊያስጥለው የሞከረ አልነበረም። አንበሳውን እየሳመ አነጋገረው። ምን እንደሚለው የሰማ የለም። ወታደሮቹ እንደገና በሮምታ ተኮሱ፤ እሱም ወደቀ። በዘርዓይ ደረስ ጀግንነት የተካሄደው የሮም አደባባይ ትርእይት በዚህ አለቀ። ከተማይቱ ምትሐት የመታትን ያህል ጭው አለች። ዘርዓይ ደረስ ታላቅ የጀግንነት ሥራ ሠራ። ሁኔታዎች አልገጠሙለትም እንጂ፣ የዲፕሎማቲክ ቡድን እስኪሰበሰብ፣ ሣልሣዊ ኢማኑኤል እና ሞሶሊኒ እስኪደርሱ ታግሦ ቢሆን ኖሮ ምንኛ ደግ ይሆንለት ነበር!

የዘርዓይ ደረስ ታሪክ በዓለም ተሰማ። የጣልያን ጋዜጦች ዕብድ ነው፣ የተጐዳው ሰው ትንሽ ነው እያሉ ቢዋሹ፣ አድማጭ አላገኙም። ሲልቭያ ፖንክረስት የዘርዓይ ደረስን አድራጐት ለዓለም አስረድተው፣ አያይዘውም "ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ...ጥንታዊ ክብርዋን እንደምትመልስ አልጠረጥርም..." የሚል ትንቢት አበሰሩ።[10] ወዳጆቹ በሥራው ኮሩ፣ ስለመከራው አዘኑለት። ጠላቶቹ የተገላገሉት መሰላቸው። በገዛ ሀገሩና ወገኑ መካከል ጀብዱ ይሰሯል፤ ግን በሰው አገር እና በቅኝ ገዥ ሕዝብ አደባባይ ላይ ይህንን ለሠራ ምን ስም ይሰጠዋል?

ዘርዓይ ይህንን ሁሉ ሠርቶ፣ በስድስት ጥይት ተመትቶ መትረፉ ለጣልያኖች ራስ ምታት ሆነባቸው። በሮም ከተማ ከነበሩት ሀኪም ቤቶች ሁሉ ብልጫ ከነበረው ሀኪም ቤት አስገቡት። እየዳነ ሄደ። ሐምሌ 15 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁላይ 22 ቀን 1938/ ሞሶሊኒ በጭፍጨፋው የቆሰሉትን ለመጠየቅ ከሀኪም ቤቱ ሲደርስ፣ ማሪዮ ኢሶን ሞቶ ሲገነዝ ደረሰ። እጀግ ተቆጥቶ ያመጣለትን ኒሻን ሰጥቶ ዘርዓይ ወደተኛበት ክፍል ሄደ። ድኖ ስለአገኘውም ይበልጥ ተናደደ። "አንተ ነህ ሮምን የደፈርካት?" ብሎ ጠየቀው። በሚገባ ታክሞ እንዲድን ለሀኪሞቹ አደራውን ሰጠ። እሱን በሞት መቅጣት፣ የጣልያንን ስም በመላው ዓለም አየር ላይ መበተን መሆኑን ገልጾ፤ በዳነ ጊዜ በቃልም፣ በጽሑፍም ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ የአእምሮ ሕመምተኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ዘረዓይ ራሱ እንዲያምን እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጠ።



ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የተባለው ዋና ሀኪም የሞሶሊኒን ትዕዛዝ በሥራ ላይ ለማዋል በብርቱ ተጣጣረ። ብዙ ቀን አባበለው፤ በመጨረሻው አንድ ወረቀት እንዲፈርም አቀረበለት። ደብዳቤው ስለተደረገለት ሕክምና አመስግኖ "በአምስት መቶ ወታደሮች አደባባይ ላይ በድንገት ታምሜ በሰዎች ሕይወት ላይ ስለ አደረስኩት በደል... ይቅርታ እጠይቃለሁ። ...በስድስት ጥይት የተበሳሳው ሰውነቴና አንጐሌም ድኖ በቅርብ ቀን ለመውጣት ተስፋ ሰጥቶኛል /ሀኪሙ ማለቱ ነው/..." የሚሉ አዋራጅ ቃላትን ያዘለ ነበር። ዘርዓይ ደረስ ደብዳቤውን ከሀኪሙ ነጥቆ ቀድዶ መልሶ ከፊቱ ላይ በተነበት። ቀደም ብሎ ስለዚሁ ጉዳይ በተደረገ በአንድ ክርክር ላይ "በእናንተ አፍ እውነት የሚነገርበት መቼ ይሆን?" በሚል ቃል ቢገስጸው እንኳን ያልታገሰለት ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የሀፍረት ማቅ ለብሶ ወጣ። ዳግመኛ አልተመለሰበትም።

ራሱ በመተናነቅ ፈንታ ፕሮፌሰሩ ሁለት ኢትዮጵያውያን ላከበት። አንዱ ስሙ ያልተጠቀሰ /ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ ሳይሆን አልቀረም/ አንዱ ደግሞ ወልደ ሚካኤል የተሰኘ መነኩሴ ነበር። ሁለቱ ሰዎች የዘርዓይ ደረስን አቋም ለማስለወጥ የሚቻላቸውን ያህል ደከሙ። የጣልያንን መንግሥት ኃያልነትና የእሱን ወጣትነት እያገናዘቡ ብዙ አባበሉት። እሱ ግን አልተቀበላቸውም። ከመኝታው ተነስቶ ቁጭ በማለት መጀመሪያ ለደጃዝማቹ መልስ ሰጠ። "..እንደርስዎ ያለ...ለማንም ጭነት ማጓጓዣ፤ አንበሳ መሆን የለበትም ነበር" አላቸው። "ለእነሱ ክብር፣ ለእነሱ መስፋፋት ከቶ የእናንተ አጠንጣኝነት ምንድነው?" ሲል ጠየቃቸው። እሳቸው ግን መልስ የላቸውም። ቀጥሎም "...እንሰሶች እንኳን ጌቶቻቸውን ይወዳሉ። ...እናንተ ግን...ቅሌታችሁን ተሸክማችሁ ትዞራላችሁ" ብሎአቸው ወደ መነኩሴው ዞረ። "...የእግዚአብሔር እንደራሴ መስለው በጥቁር ጨርቅ ይምነሸነሻሉ።" "...የሰውን የእኩልነት ኑሮ ለማጥፋት ከላይ ተልካችሁ የመጣችሁ መቅሰፍቶች ናችሁ" አላቸው። "ቅስናዎን ይተውት። ..ተራ መሐይምን መስለው እንደ ሌሎች ባንዶች ቢያገለግሉ ይበልጣል" ብሎ መከራቸው። በመጨረሻም "...ከአጠገቤ ውጡ" አላቸው። እነሱም ቀለል፣ ቀለል እያሉ ወጡ። ዳግመኛ ይህንን ዓይነት ጥያቄ ለዘርዓይ ደረስ አልቀረበለትም።

ጉዳዩ ወደ መደበኛ ፍርድ፣ መስከረም 3 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 14 ቀን 1938/ ቀረበ። መደበኛ ፍርድ ቤቱ ወደ ጦር ፍርድ ቤት መራው። በጦር ፍርድ ቤቱ መስከረም 12 ቀን 1931 ዓ.ም /ስፕቴምበር 23 ቀን 1938/ ቀረበ። ዳኞች በጭካኔአቸው የታወቁ ሦስት ኰሎኔሎች ነበሩ። ስማቸው አልተገለጸም። ነገር ግን ሳንታሪክስ፣ ዲማንደቶርና ኢንሣራ ሳይሆኑ እንደ አልቀሩ ተገምቶአል። ሕዝብ እጅግ በብዛት ተሰብስቦአል። ዓቃቤ ሕጉ አስቶፖኒ ነው። ዘርዓይ ደረስ ብቻውን ቀረበ። ሥርዓቱ፣ ዕለቱን ፍርድ ሳይሰጥ፣ ፍርዱም ሳይፈጸም እንዳያድር የሚያስገድድ ነበር።

ዓቃቤ ሕጉ አሥራ አንድ ወንጀሎች በእሱ እንደተፈጸመ ገልጸ፤ ዘርዓይ ደረሰ "በቤንዚን ተቃጥሎ እንዲሞት ወይም እጁ ታሥሮ በሠረገላ እየተጐተተ በከተማው እየዞረ ለሕዝብ እንዲታይ" ተብለው በተለይ ለቅኝ ግዛት ዜጎች ከወጡት ሁለት አንቀጾች በአንዱ እንዲቀጣ ሃሳብ አቀረበበት። እነዚህን ሁለት አንቀጾች የጠቀሰው ሌላ የባሠ ባለመኖሩ እንጂ፣ ለዘርዓይ በደል በቂ ናቸው በማለት አለመሆኑን አስረዳ። የክሱ አቀራረብ ኢጣልያ ተደፍራለች፤ አንድ ማርሻልና ብዙ ወታደሮች ሞተዋል፣ በዚሁ ምክንያት ከተማ ተረብሾ እንደ ነበርና የሞተና የቆሰለው እንዳልታወቀ የሚገልጽ ነበር።

የቀረቡበት ክሶች ፍሬ ነገር ከቤኒቶ ሞሶሊኒ የተፈቀደ የይለፍ ፊርማ ይዞ ወታደሮች በማዘናጋት የጦር መሣሪያ /ጐራዴ/ ይዞ አደባባይ ገብቶአል። ከፍተኛ ረብሻ በማስነሳት ወታደሮቹንና ሰላማዊ ሰዎችን ፈጅቶአል። የጣልያንን ክብር ደፍሮአል፤ በተፈጥሮ አሥር ሺህ ጊዜ የሚበልጡትን የጣልያኖችን ታሪክ አደፍርሶአል። የጣልያንን ፖለቲካ ለማጣረስ አስቦ ተነሳስቶአል። ከመንግሥታችን የተጣለበትን ኃላፊነት አንኳሶ ጥሎአል፤ የመንግሥት ምሥጢር አባክኖአል። ጣልያኖችን የጨፈጨፈበትን ጐራዴ የወሰደው እስኩድሪን አታልሎ ነው። የጣልያንን ባንዲራ ከራሱ ቀለበት አውርዶ ረጋግጦ ከመጣሉም በላይ፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በራሱ ደም ቀብቶ ሰቅሎአል። ተፈሪ ለዘለዓለም ይኑር፣ የኢጣልያ ፋሽስት መንግሥት ይውደም በማለት የኢጣልያ መንግሥት ላይ ጥላቻ አሳይቶአል የሚሉ ነበሩ። ክሶቹ፣ እውነታቸው በሁሉም ዘንድ የታወቀ በመሆኑ፣ ማስረጃ የሚጠየቅበት አልነበረም።

ሰብሳቢው ዳኛ ሌሎቹን ሳያማክር አስተያየቱን ሠነዘረ። "...ኢጣልያ እንዳችም ጉዳት አልደረሰባትም። ...ኢጣልያ...ልጆችዋን ወደ ሜዳ ልካ የጦርም የትምህርትም ሐዋርያ ሆነው ይገኛሉ" አለ። የሕዝቡ ጫጫታ ተነሣ። እሱ ግን "ዝሆንን በቁንጢጥ...ባንድ ጥፍር በማይሞላ ሰው ሕመም የተነሣ ይህንን ያህል ልንተችበት አይገባም" አለ። ቀደም ብሎ ጆሮውን ሳይኮረኩር አልቀረም። ጫጫታውን፣ ፉጨቱን፣ ውሽቱን ከምንም ሳይቆጥር "አንድ ዕብድ የምንቀጣበት አንቀጽ በዚያው በአንጐል ሕመምተኞች ቦታ ተቀላቅሎ እንዲኖር ብቻ ነው" በማለት ፍርዱን ደመደመ። ሌሎች ሁለት ዳኞች በዚህ ፍርድ ሳይስማሙ ቀሩ። "...እኛ ዕብድ መሆኑን አናምንም። ...በተጠቀሰው አንቀጽ ይፈረድበትና አሟሟቱን እንመልከት" አሉ። ዓቃቤ ሕጉ በሁለቱ ዳኞች ሃሳብ ልቡን አደንድኖ "እሱን ዕብድ ሰው ነው የሚል ራሱ ያበደ ነው" አለ። ችሎቱን ከመድፈር አልተቆጠረበትም። የሕዝቡ ጭብጨባ ከዳር እስከዳር አስተጋባ።

ዳኞች ፊት ሊያደርጉት ይገባ የነበረውን ሥራ ጀመሩ። እርስበርሳቸው ተመካክረው የወንጀሉን መነሻ ለመመርመር ተስማሙ። ዘርዓይ ቃሉን እንዲሰጥ ተፈቀደለት። የጣልያንኛ ቋንቋ አጥርቶ ማወቁ፣ ጉዳዩን እንደ ልቡ



ለማስረዳት ጠቀመው። ኀሊና የሚሠረሥረውን ነገሩን ቀጠለ። "ምን እንድል ነው የምትሹት? እብድ ነኝ እንድል ነው ጤነኛ?" ብሎ ዳኞቹን ጠየቃቸው። መልስ የለም። ሲደነፉ ነፍሥና ሥጋን ለመለያየት የተመረጡ በሚመስል አቀራረብ ወደ ዓቃቤ ሕጉ ዞሮ፦"...አንተ እንደምትለውና እንደምታስወራው መሆኑን ላረጋግጥልህ እደስታለሁ። በእውነቱ የእኔ ዶክተር አንተ ብቻ ነህ" አለው። ሐኪሙ ከሞሶሊኒ ተሻርኮ ዕብድ ነው ማለቱን፤ ሰብሳቢውም ዳኛ ይህንኑ ማስተጋባቱን አጋለጠ። ሞሶሊኒ የጣልያንን ዕድል በር ሊከፍት የተፈጠረ አስመስሎ፣ በኋላ ግን ሮምን ጥቁር ታሪክ አልብሷት እንደሚሄድ ተነበየ።

ሕዝቡ ይገደል! ይሰቀል! ይቃጠል! አለ። እሱ ግን በድፍረት ንግግሩን ቀጠለ። ብዙ ከወቀሳቸው በኋላ "...እኔ ሙሉ ጤነኛ ነኝ" አላቸው። ከእነሱ በስተቀር ምንም ሕመም እንደሌለበት ገለጸላቸው። የግፍ ሥራቸው ቢበዛበት ጥቂት ሰዎች ማረዱን አምኖ፣ እርዱ እንዳላጠገበው፣ እንዲያውም በሽታ እንደሆነበት አረጋገጠላቸው። "...ያገርን መውደድ ቋንቋ ካወቃችሁ አገራችንን እንድንጠላ፣ እርስበርሳችን እንድንጣላ ...ለምን ታስገድዱናላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። አሁንም መልስ የለም። እሱ ላይ ለመፍረድ ከሺህ ሕዝብ በላይ መሰብሰቡን አሳይቶ፣ የፋሽስት ወሮበሎች በእሱ አገር በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ሲፈጁ ዳኛ እንደ ሌለባቸው ገለጸ። "ግን" አላቸው "የእነሱ /የኢትዮጵያውያን/ አጥንትና ደም ዋጋ ሲኖረው፤ የእናንተ ስም እየገማ መሄዱ ዛሬ አይታያችሁም። ...ዘለዓለም በታሪካችሁ አቀርቅራችሁ ትኖራላችሁ" አላቸው። ከዚያም አመስግኖ በጣሊያን ሰው ላይ ይህንን ያህል ትዕግስት ሲያይ የመጀመሪያው መሆኑን ነገራቸው።

በመጨረሻም "የኢጣልያን ባንዲራ ይውደቅ! የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በክብር ትኑር! ንጉሥ ተፈሪ በድል አድራጊነት ይኑር! የይሁዳ አንበሳ ምንግዜም ድል ከሱ ይሁን!" ብሎ ንግግሩን ደመደመ። ችሎቱ እንደ ትያትር ሆነ። ሕዝቡ ከመጠን ያለፈ ጮኸ። ተተራመሰ። ዳኞቹ የሚሰማቸው ስለአጡ ተናደዱ። ዓቃቤ ሕጉ "...ሮማ ማልቀስና ማዘን የሚገባት ዛሬ ነው " አለ። ሰብሳቢው ዳኛ ተሸነፈ። በቤንዚን ተቃጥሎ ይሙት በሚለው ፍርድ ሦስቱም ዳኞች ተስማሙ። ንቀቱንና ድፍረቱን የሚያሳይበት፣ ስሜቱን የሚገልጽበት ዕድል ለዘርዓይ ደረስ በመስጠታቸው ሁሉም ተጸጸቱ። ኰሎኔል ሳንታሪክስ የተባለው ሰብሳቢ ዳኛ "አሞራ በራሳችን ላይ ተቀምጦ ረፈጡን እስከሚጥልብን ድረስ ተኝተናል" አለ። ዘርዓይ በፀጥታ ይመለከት ነበር።

ችሎቱ በዚህ ዓይነት ላይ እንዳለ አዲስ ነገር ተፈጠረ። ሁለት የፖሊስ መኰንኖች ችሎቱን ሰብረው ገቡ። ከሁለቱ አንዱ ወታደራዊ ሰላምታ አቀረበና አንዲት ጥቁር ፖስታ ለሰብሳቢው ዳኛ ሰጠ። ሰብሳቢው ዳኛ ፖስታውን ቀድዶ ሲመለከት የሞሶሊኒን ፊረማ ስለአየ በድንጋጤ ኩሽሽ አለ። ከሞሶሊኒ የተላከ ደብዳቤ መሆኑን በመግለጽ ደጋግሞ ለራሱ ከአነበበው በኋላ

ለሕዝቡ አሰማው። ሞሶሊኒ በዚህ ደብዳቤው የገለጸው ለአንድ እብድ ዋጋ በመስጠት በጭቅጭቅ መዋላቸውን እንደሰማ ከገለጸ በኋላ ብርቱ ወቀሳ ይወቅሳቸዋል። "...በአርባ ሚሊዮን ደንቆሮ መካከል ተፈጥሬ እናንተን ጥዋት ማታ ማስተማሩ ሰለቸኝ" የሚል ስሞታ ከአሰማ በኋላ፤ "...ለዕብድ ያቋቋምኩት ወንጀለኛ መቅጫ የለኝምና...ወደ አንኮል በሽተኞች ሐኪም ቤት ሄዶ እንዲቀመጥ ይሁን። ...በዕብደቱ እንጂ በሌላ መልክ ሮማንንና ሕዝብዋን እንደ አልደፈረ እንዲታወቅ" የሚል ውሣኔ የያዘ ነበር። ከዚህም በስተቀር ማንም ሰው ዘርዓይ ደረስ ያደረገውን ቢያነሣ በገመዱ እንደሚገባ ይገልጽና፣ ዳኞቹ ወደ ሞሶሊኒ በፍጥነት እንዲቀርቡ የሚያዝ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ የአርበኝነትና የፖለቲካ ሥራውን በጣልያን አገር፣ ከዚህ በላይ በተገለጸው አይነት አከናውኖ ወደ እሥራት ኑሮው ተሸጋገረ። ቀጣይ ታሪኩን ከድል በኋላ ትግል በሚለው ምዕራፍ ይመልከቱ።

ዘርዓይ ደረስ ግን ማን እንደነበረ ማወቅ ይገባል። ዘርዓይ በአዲ ሐይስ፣ ከተማ በተባለች ቦታ በ1908 ዓ.ም ተወልዶ ሐዘጋ ያደገ የኤርትራ ልጅ ነው። አሥመራ ከተማ ከገባ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ትምህርት ያስተማሩት ርዕሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ እንደሆኑ እሳቸው ራሳቸው ለእኔ ለዚህ ታሪክ ፀሐፊ ነግረውኛል። እሳቸውም በጐንደር፣ በትግራይ፣ በጐጃምና በላስታ እየተዘዋወሩ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ አቋቋም የተማሩ ስለነበሩ፤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ የኢትዮጵያን ታሪክና ሥርዓት በማስጠናት የሀገር ፍቅር ስሜት ሳያሳድሩበት አልቀሩም። እሱም ብልህ ተማሪ ስለነበር፣ በትምህርታቸው እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ሠራበት።

ከቤተ ክህነት ትምህርት በኋላ ዘርዓይ በሣልሣዊ ኢማኑኤል ስም በተከፈተ፣ አሥመራ ከተማ በነበረ ትምህርት ቤት እስከ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ያለውን ትምህርት ተከታተለ። ከዚያም አዲ ኡግሪ ተዛውሮ ጥቂት ከተማረ በኋላ፣ ኮረም በነበረ የሚሲዮን ትምህርት ቤት፣ ቤአስተማሪነት ሥራ በ1920 ዓ.ም ተሰጠው። የአስተማሪነት ሥራ የተሰጠው የኢትዮጵያ ፍቅር እያየለበት ስለሄደ፣ ሀሳቡን ወደ ሌሎች ወጣቶች ለማዞር እንጂ እሱን ለመጥቀም አልነበረም። በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር መቀሌ በሚደረግ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ስለታዘዘ ሄደ። በየመንገዱ ዳር በጦርነቱ የሞቱ ኢትዮጵያውያን ሬሣ በብዛት ማየቱ፣ የሀገር ፍቅር ስሜቱን አጋግሎ እንደ በሽታ ወደ ህመምነት ተለወጠበት። ወደ ሥራው በተመለሰ ጊዜ ስሜቱን ለተማሪዎቹ መግለጽና ስለሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ማስተማር፣ ከዚያም አልፎ መከራከር አመጣ። ይህ ይሁኔታ ለጣልያኖች ስለከበዳቸው ከሥራው ተባረረ።

ሁኔታው በቤተሰቡ ላይ ሥጋት ስለፈጠረ ተዳረ። ዓለማሽ የተባለች ልጅ ከሰገነይቲ አገባ። የደጃዝማች አዳል ወገን ነበር። ዘርዓይ እንደ በሽታ



ዘልቆት በገባው የሀገር ፍቅር ስሜት ምክንያት ከሁለት አጣብቂኝ ውስጥ ገባ። አንዱ ከወገኖቹ፣ ሌላው ደግሞ ከጌቶቹ ወገን የተሰነዘረ ነበር። ሁለቱም ከባድ ነበሩ። ኤርትራውያን የጣልያኖች ሰላይ አድርገው ቆጠሩት። እሱ የሚናገረው፣ እነሱን ለማውጣጣት መሰላቸው። ጣልያኖች ልቡ በሀገሩ ፍቅር እንደተቃጠለ አወቁ። የቅኝ ግዛት ዜጐቻቸውን እያነሳሳባቸው መሆኑን ተረዱ። እሱም በበኩሉ ኢትዮጵያን መደገፉን ቀጠለ። ለነጮች ዝቅተኛ ግምት ከመስጠቱም በላይ፣ የማንንም ማስጠንቀቂያ ከቁም ነገር ሳይቆጥር "ገብረ ሚካኤላውያን" የሚል ማኅበር አቋቋመ። የማኅበሩ ዓላማ ኢትዮጵያን በጠላትዋ እጅ ስለወደቀች በጸሎትም፣ በመንፈስም ከኢትዮጵያውያን ጐን መቆም ነበር። የማኅበሩ የስም አጠራር የተመረጠው፣ የበላይ ጠባቂ ከነበሩት ከአባ ገብረ ሚካኤል ስም በመያያዙ ሳይሆን አልቀረም። ከዚያም አልፎ ተቃውሞውን በጋዜጣ መግለጽ ጀመረ።

ደውዲያች ከተባለው የኤርትራ ገዥ ዘንድ ቀርቦ የቃል ጥያቄ ተደረገለት። የጣልያንን ለቅኝ ግዛት ዜጐች የሚሰጠውን ትምህርት ማጠናቀቁ፣ ባለትዳር መሆኑ ታወቀ። በቋንቋም ረገድ ኢጣልያንኛ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ዓረብኛ አጣርቶ ማወቁ፤ ከዚህም በስተቀር ኦሮምኛ፣ ሱማልኛና አገውኛ የሚያስጠናው ቢያገኝ ማወቅ እንደሚፈልግ ግልጽ ሆነ። ለጣልያኑ አገረ ገዥ ይህንን ዓይነቱን ሰው በአሥመራ ውስጥ ከማስቀመጥ ወደ ሮም መላክ የተሻለ ሆኖ ታየው። በአስተርጓሚነት ሥራ በጣልያን፣ በቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ እንዲሠራ ወደ ሮም ላከው። ዘርዓይ ወደሮም የተላከው፦ የደረጃ ዕድገት በመስጠት የጥላቻ ስሜቱን ለማቀዝቀዝ፤ ጉዳት ሊያደርስበት ከሚችል አካባቢ ከአሥመራ ለማራቅና በችሎታው ለመጠቀም ሳይሆን አልቀረም።

የዘርዓይ ወደ ሮም መሄድ ካባድ ነገር ሆነ። ከቤተሰብ መለየቱ አንዱ ሲሆን፣ የሚከተለው የፖለቲካ አቅጣጫ የፈጠረው ሥጋት ሌላው ነበር። ቢሆንም ጉዞውን ቀጥሎ በመስከረም 1929 ዓ.ም ሮም ገባ። ከበቂ ደመወዝ ጋር የተመረጠበትን የአስተርጓሚነት ሥራ በቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ ያዘ። ለአንድ ቅኝ ግዛት ዜጋ ሊያገኝ የሚቻለውን ከፍተኛ ደረጃ አገኘ።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሥጋዊ ፀጋ ለዘርዓይ ደረስ መንፈሳዊ እርካታ አልሰጠውም። ስለዚህ በዚያ ከነበሩ የጣልያን ደጃዝማቾች ጋር ክርክሩን ቀጠለ። በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም አሥመራ ለነበረ ገብረ ሕይወት ለተባለ ጓደኛው የጻፈው ደብዳቤ ከብዙ ማስረጃዎች አንዱ ይሆናል። ዘርዓይ በዚህ ደብዳቤው በኑሮው በኩል ምንም የተጓደለበት ነገር እንደሌለ ከአረጋገጠ በኋላ፦ "...አሥመራ ውስጥ አልፎ አልፎ ይዘጋ የነበረው ልሣኔ ተከፍቶአል። ዛሬ ሮምን እንደ ቅኝ ግዛቴ ነው የማያት ..." ብሎአል።

የጉራጌውንም ጉዳይ መመልከት ይገባል። ራስ አሉላ በጥር ወር 1871 ዓ.ም /ጃንዋሪ 1878 እ.ኤ.አ/ ዶጋሊ ጦርነት ላይ ታጥቀውት በዋሉት

ጐራጼ ነው ዘርዓይ ደረስ ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁን 14 ቀን 1938/ የጀብዱ ሥራ የሠራው፡፡ ጐራጼው ከእጁ የገባው እስኩድሪ የተባለ ጣልያናዊ ወዳጁ ከሮም ወደ ናፖሊ እንዲወስድለት ከሞሶሊኒ ስለተፈቀደለት ነው፡፡ የሞሶሊኒን ፈቃድያገኘው ደግሞ እስኩድሪ ራሱ እንዲያመለክት በዘዴ በማስማማት ነው፡፡ እስኩድሪ ጐራጼውን ወደ ሮም የወሰደው የመቀሌ ገዥ በነበረ ጊዜ ደጃዝማች በየነ የተባለ እወደድ ባይ ስለሰጠው ነው፡፡ ደጃዝማች በየነ ጐራጼውን ለእስኩድሪ የሸለመው በአፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት በወግ ዕቃነት ተጠብቆ ይኖር ከነበረበት ቦታ ወስዶ ነው፡፡[11]

ሌላው በጣልያን አገር አስደናቂ የጀግንነት ሥራ የሠሩት ሻምበል /ኰሎኔል/ አብዲሣ አጋ ናቸው፡፡ እሳቸው ደግሞ በኢጣልያ በረሃዎች ሸፍተው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ የአርበኝነት ሥራ አካሂደው በመጨረሻ ከድል አድራጊው የእንግሊዝና የአሜሪካን ጦር በክብር ተቀላቅለዋል፡፡ ሲቀላቀሉም በሻምበል አዛዥነት ጦራቸውን ነጭ ጥቁር ሳይባል ሁሉም በግራ ክንዱ ላይ የኢትዮጵያን፣ በቀኝ ክንዱ ላይ ደግሞ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማዎች እንዲያሥር አድርገው በማሰለፍ ነው፡፡ ከዚህም በስተቀር ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ አስረክበዋል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

| የዕቃው ዓይነት | ከጣልያን የተማረከ | ከእንግሊዝ የተላከ | ድምር |
|---|---|---|---|
| 1ኛ. ልዩ ልዩ መትረየስ | 254 | 40 | 294 |
| 2ኛ. የልዩ መሣሪያ ጥይት | 327,923 | 16,354 | 344,277 |
| 3ኛ. የእጅ ቦምብ | 9,080 | 400 | 9,280 |
| 4ኛ. ልዩ ልዩ ጠመንጃ | 253 | - | 253 |
| 5ኛ. አውቶማቲክ ሽጉጥ | 10 | - | 10 |
| 6ኛ. ካሜራ | 2 | - | 2 |
| 7ኛ. ኮምፓስ | 90 | - | 440 |
| 8ኛ. ጂፕ መኪና | 350 | - | 15 |
| 9ኛ. ብረት ለበስ መኪና | 15 | - | 2 |
| 10ኛ. ጩቤ | 2 | - | 104 |
| 11ኛ. የወታደር ሬዲዮ | 104 | - | 9 |
| 12ኛ. የቴሌግራም ሬዲዮ | 7 | 2 | 3 |
| 13ኛ. ከባድና ቀላል መኪናዎች | 3 | - | 103 |
| 14ኛ. የብረት ባርኔጣ | 103 | - | 17,731 |
| 15ኛ. ደናሚት | 17,731 | - | 350 |
| 16ኛ. የኢጣልያ ካርታ | - | - | 4 |
| 17ኛ. የጦር ሜዳ መነጽር | - | - | 20 |
| 18ኛ. ሞተር ሳይክል | - | - | 1 |



እንደዚሁም ብዙ ልብስና ልዩ ልዩ ዕቃ፡፡ የተቀበሉአቸውም የእንግሊዙ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ፊልድ ማርሻል ቫይካውንት ሞንትጐሞሪ ነበር፡፡ የምስክር ወረቀትና ሜዳልያም ተሸልመዋል፡፡ ከዚህ በላይ የተገለጸው ውጤቱ ሲሆን፣ የሻምበል /ኰሎኔል/ አብዲሣ አጋ የፈጸሙት ሥራ ከዚህ የሚከተለው ነው፡፡

በሆለታ የጦር ትምህርት ቤት የአጭር ጊዜ ትምህርት እንደ አገኙ ኢትዮጵያ ድል ሆነች፡፡ ኢትዮጵያ ድል ስትሆን አብዲሣ አጋ በ15 ዓመት ማርተጋሻ ወታደር ነበሩ፡፡ ስለዚህም የጥቁር አንበሳ ጦር አባል ሆነው ወደ ምዕራብ ኢትዮጳያ ተጓዙ፡፡ በወለጋ በኩል ኢሉባቡር ደርሰው፣ ከዚያም ተመልሰው በጐጅብ ጦርነት በጥይት ቆሰሉ፡፡ በዚያውም ላይ የራስ እምሩ ጦር እጁን ሲሰጥ እሳቸውም አብረው እጃቸውን ሰጡ፡፡

ጣልያን ከምርኮኞቹ ወታደሮች ጋር አብሮ አምጥቶ ጂማ እሥር ቤት ከተታቸው፡፡ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በእሥራት ከቆዩ በኋላ የቁም እሥረኛ ሆኑ፡፡ በቁም እሥረኛነት ጥቂት ጊዜ እንደ ቆዩ፣ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በግራዚያኒ ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት እንደገና ተይዘው ብዙ ድብደባ ከደረሰባቸው በኋላ፣ እሳቸውን በመኪና በማጓጓዝ ምፅዋ ወስደው ከመርከብ ላይ አስፈሩአቸው፡፡ ከምፅዋ ወደ ደናኔ ወሰዱአቸው፡፡ ደናኔ ሳሉ ኢጣሊያኖች እሥራ ስምንት የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት መኰንኖችን፣ የገዛ መቃብራቸውን አስቆፍረው በመትረየስ ከደበደቡአቸው በኋላ፣ የተረፉትን ሠላሳ በመርከብ አሳፈሩአቸው፡፡ ወታደር አብዲሣ አጋ ከእነዚህ እሥረኞች መካከል አንዱ ነበሩ፡፡

እሥረኞቹ ናፖሊ ሲደርሱ በአውቶቡስ አጓጉዘው አኞኖ ከተባለው የጦር ሠፈር አስገቡአቸው፡፡ በእዚያ እንደ አሉ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን ለመቆም ወሰነች፡፡ ጦርነቱ በጣልያን አገር ሲቀሰቀስ፣ በእንግሊዝ አይሮፕላኖች የተበተነ ጽሑፍ አግኝተው አነበቡ፡፡ በዚህ ደግሞ ሌላ ድብደባ ደረሰባቸው፡፡ በዚህ ተናደው ወሬውን የነገረባቸውን አሳባቂ ደበደቡ፡፡ በዚህ ደግሞ ከጦር ሠፈሩ ተወስደው ከናፖሊ፣ ባዱሊዮ ወህኒ ቤት ገቡ፡፡

የሰው ቅልጥም በሚመስለው የኢጣልያ አገር ላይ ጦርነት ከጫማው ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ አካል ወደ ሰሜን መንደድ ሲጀምር፣ ጣልያኖች በናፖሊ የነበሩትን እሥረኞች ወደ ሰሜን ኢጣልያ አጓዙ፡፡ ከእነዚህ እሥረኞች አንዱ ወታደር አብዲሣ አጋ ነበሩ፡፡ ሊቲ በተባለው ወረዳ ትሪያ ቀበሌ ከሚገኝ እሥር ቤት አገቡአቸው፡፡ የእግር ጉዞው ብዙ እሥረኞች የተሰቃዩበት ነበር፡፡ አስተሳሰባቸው አደገኛ መሆኑ በጣልያኖቹ ዘንድ ስለታወቀ፣ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን ተዘጋባቸው፡፡ ዕብድ

ብለው እጆቻቸውን በሰንሰለት አሠሩአቸው። በልመና እጆቻቸው ሲፈቱላቸው በአጠገባቸው የነበሩትን ጣልያኖች ደብድበው አንጀታቸውን ከማራስ ጋር ዕብደታቸውን በግብር አረጋገጡ። ከፖሊስ እሥር ቤት ሆነው ሀኪም ቤት እየተመላለሱ እንዲታከሙ ተደረገ። ከፊተኛው ሁኔታቸው ይህ የተሻለ ሆነ። ከዚያም ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ሌቺ ወህኒ ቤት ገቡ።

ከሌቺ ወህኒ ብዙ የዩጐዝላቭ፣ የእንግሊዝ፣ የመስኮብ፣ የአሜሪካ ዜጐችና አረቦች አገኙ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል የዩጐዝላቪያው ተወላጅ ጁሊዮ ኢታቺክ የሚባሉ ሰው ነበሩበት። እኝህ ወታደር አብዲሣ በአቀረቡት ሃሳብ መሠረት ከእሥር ቤቱ አምልጠው ለመውጣት ተስማሙ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ቦምብ በሚጥሉበት ጊዜ ከወህኒ ቤቱ አመለጡ። ያመለጡትም ያገኙትን ብርድ ልብስ ቀዳደው በመቀጣጠል አንዱን ጫፍ በመስኮት ላይ በማሰር ከነበሩበት ፎቅ ላይ ተንጠልጥለው በመውረድ ነው። ከእሥር ቤት ያመለጡት ሦስት ኢትዮጵያውያንና አምስት ዩጐዝላቫውያን ነበሩ። ሁለቱ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ካሣዬ አብጤና ከርሎ አቦ መጋል የሚባሉ ነበሩ።

ስምንቱ ሰዎች ከእሥር ቤት አምልጠው ጫካ ከገቡ በኋላ ከሁለት ከብት ጠባቂ ሰዎች ላይ ሁለት ረሽ ነጠቁ። ሁለቱን ረሽ ጠመንጃዎች ለመንጠቅ የቻሉት አንዱን ሰው ገድለው፣ ሁለተኛውን አቁስለው ነበር። ከዚያም ካዛቪንቺና ወደ ተባለው ተራራ ወጡ። ከዚያም በጣልያን መንግሥት ላይ ከሸፈቱ አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። በዚህ ጊዜ ቁጥራቸው ወደ ሠላሳ ከፍ አለ። ነገር ግን የነበሩአቸው መሣሪያዎች አንድ አልቤን ጠመንጀ ከአሥራ ሁለት ጥይት ጋር፣ ሁለት ረሽ፣ አንድ ፍሻሌ ሽጉጥ ከስድስት ጥይት ጋር፣ ሦስት የእጅ ቦምቦች ነበሩ። የጐደለው በዱላና በድንጋይ ማሟላት ነበረበት።

አንድ የአየር ኃይል መኰንን ከገደሉና አንድ ወህኒ ቤት ከአቃጠሉ በኋላ ከዛ ሎሬንስ ወደ ተባለው ተራራ ወጡ። ከለላ እየሰጠ የሚከተላቸውን የጣልያን መንግሥት ጦር ጋር ኡያሮ በተባለችው መንደር አካባቢ ተዋግተው ሃምሣ ሁለት ፋሽስት በመግደል ድል አድርገው አባረሩአቸው። ከእነሱም ወገን ሁለት ሰዎች ቆሰሉባቸው፣ አሥራ ሦስት ሰዎች ሞቱባቸው።

ቲቶ ነጩ /ቢያንካ/ የሚሉት ሰላያቸው ፍሩንታሌ በተባለው ሜዳ ላይ የጀርመን አይሮፕላን ማረፉን ነገራቸው። ወታደር /ኰሎኔል/ አብዲሣ አጋ ጁሊዮ አታቺክ ከተባለው ዩጐዝላቫዊ ጋር ሃያ ሦስት ወታደር ይዘው ወደተባለው ሜዳ ሄደው በጀርመኖቹ ላይ አደጋ ጣሉ። አይሮፕላን ነጅው



አይሮፕላንዋን ይዞ ሲያመልጥ በሌሎቹ ላይ ጉዳት አደረሱባቸው። ከጀርመኖቹ አንዱ መቶ አለቃና ሦስት ወታደሮች ተገደሉ፤ ሌሎቹ እጃቸውን ሰጡ። ከእነሱም ወገን ከርሎ አባመጋል የተባለው ኢትዮጵያዊ ሞተ። እነሱም የከርሎን ሬሣና እንደዚሁም የማረኩአቸውን የፋሽስት ወታደሮች ይዘው ኡያሮ ወደ ተባለው የጦር ሠፈራቸው ተመለሱ።

በምርኮኞቹ ላይ ፍርድ ተያዘ። ግብራቸው ከተመረመረ በኋላ በሞት እንዲቀጡ ተወሰነ። ውሣኔው ለምርኮኞቹ ሲገለጽላቸው፣ ጀርመናዊው ሻምበል ሃሳቡን ለመግለጽ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። በተፈቀደለት ጊዜ ፋሽስቶች በአርበኞቹ ቆራጥነት እንደተደናገጡ፤ ይልቁንም የወታደር /ኰሎኔል/ አብዲሣ ጀግንነት ገንኖ እንደሚነገር ከአስረዳ በኋላ፣ የደረሰባቸውን ሁኔታ ለአለቃው በሬዲዮ ለማስታወቅ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። ተፈቅዶለት ለአለቃው ከአስረዳ በኋላ ደግሞ እጆቻቸውን ሳይታሠሩና ዓይኖቻቸውን በጨርቅ ሳይሸፈኑ እንዲገደሉ ጠየቀ። ይህም በተፈቀደለት ጊዜ የወገቡን ሽጉጥ፣ የሱሪውን ቀበቶ፣ የእጁን ሰዓት ለወታደር /ኰሎኔል/ አብዲሣ አጋ ሸልሞ፣ ግንባሩን ሰጠ፡ በእሱና በወታደሮቹ ላይ የሞት ፍርድ ተፈጸመባቸው።

በሌላ ቀን ጠላት ሳንቢር በተባለው ተራራ ላይ አርበኞችን ለማጥቃት ሞከረ። የኢትዮጵያ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሣይ፣ የዮጐዛላቪያና የሌሎችም አገር ሰዎች ያሉበት የአርበኛ ቡድን በጥይት ቆላው። በሳንጃ እየቀደደ ገደል ለቀቀው።

አርበኞቹ ኃይላቸውን ከአጠናከሩ በኋላ የውጊያ ሥልታቸውን ከመከላከል ወደ ማጥቃት አዞሩ። ከዕለታት አንድ ቀን ከአንድ ቤተክርስቲያን የካህናት ልብስ ወስደው ለአሥር የራሳቸው ወታደሮች አልብሰው ሣንላ ባሪኖ፣ ደሌ ማርኬ ከተባለችው ከተማ አስገቡ። ከዚያ የነበሩትን የፀጥታ ጠባቂዎች ፈጅተው፣ በእጃቸው የነበረውን መሣሪያ ማረኩ። ምርኮውም አንድ መቶ አሥር ጠመንጃ፣ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዘጠኝ ጥይት፣ አንድ ካሚዮን፣ ሁለት ሬዲዮኖች እና አራት ሠራተኞቻቸውን ያጠቃልል ነበር።

ስንቅና ትጥቅ ለማግኘት ከገበያ እየገቡ መቅረጥ ያዙ። ፍሩንታሌና ትሪያ ከተባሉት ሁለት ገበያዎች፣ ከብዙ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ጋር 1761 ከባድና ቀላል መሣሪያ፣ 4 የእጅ ቦምብ፣ 3,836,231 ጥይትና 44,003,213 ሊሬ አገኙ። ከሽፍቶቹ ውስጥ ኢትዮጵያዊ መታየቱ እጅግ አስደንጋጭ ሆነ። ከገበያዎቹ የሚገቡት የስልክና የኤሌክትሪክ መሥመር እየበጠሱ ከመሆኑም በስተቀር፤ ለቅቀው ሲሄዱ ደግሞ ድልድዮችን በድናሚት ማፍረሳቸው በመንግሥት ላይ ችግር ፈጠረ።

በወታደር /ኩሎኔል/ አብዲሣ የሚመራ አንድ ቡድን ቢያኑራ ከተባለው መንገድ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ፣ ኰሎኔል ትሩንቢንቲ የተባለውን የጦር መኰንን ከአንድ ሹፌርና ከሁለት ወታደሮቹ ጋር ገድሎ 3 ቀላል አውቶማቲክ፣ 328 ጥይት፣ 3 የእጅ ቦምብና ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች ማረከ።

የኰሎኔል ትሩንቢንቲን መገደል ሲሰማ፣ ጣልያን ሌላ ጦር ላከ። እሱንም አርበኞች ሣንቢቲና ከተባለው ተራራ ላይ ገጥመው አራት ቀን ከወጉት በኋላ፣ ሌላ አዲስ የጀርመን ጦር ደረሰ። በብርታት ሲከላከሉ የእንግሊዝና የአሜሪካን ጦር ስለደረሰላቸው ድሉ የአርበኞች ሆነ። በዚህ ጦርነት በሻምበል ጁሊዮ ኢታቺክና በወታደር አብዲሣ አጋ የሚመራው ቡድን ጥሩ ውጤት ማሳየቱ ታውቋል።

በዚያ የጦር ሜዳ የተሠለፈው፣ በአራት ክፍል የተመደበ ነበር። በአንደኛው ቡድን 250 አሜሪካኖች፣ በሁለተኛው ቡድን 300 እንግሊዛውያን፣ በሦስተኛው ቡድን ከ400 ያላነሱ ዩጉዝላቫውያን ነበሩበት። ሦስቱም የሚታዘዙት የየራሳቸው ዜጋ በሆኑ መኰንኖች ነበር። አራተኛው ክፍለ ጦር የልዩ ልዩ አገር ዜጐችን ያካተተ ሲሆን 380 ወታደሮች ነበሩበት።

የአሜሪካኑ ጦር የሚመራው በአንድ አሜሪካዊ የመቶ አለቃ ነበር። የእንግሊዝ ጦር ደግሞ ሻለቃ ፋይ በተባለ ሲሆን፤ የዩጉዝላቫውያኑን የሚመሩት ሻምበል ጁሊዮ ኢታቺክ ነበር። አራተኛው ቡድን ብቻ የሚመራው በራሱ ዜጋ አልነበረም። በኢትዮጵያዊው በሻለቃ አብዲሣ አጋ ነበር። ሻለቅነቱንም ያገኙት ከዚያው ከጦር ሜዳው ላይ መሆኑ ነው። ጣልያንም እነዚህን መሪዎች ይዞ ላመጣ፣ ወይም ራሳቸውን ቆርጦ ላሳየ የወርቅ ኒሻንና አንድ መቶ ሺህ ሊሬ እንደሚሸልም በሕዝብ መገናኛ አስታውቆ ነበር። በዚህ ጊዜ ማርሻል ባሎምባሪኒ የተባለ ሰው አርበኞችን ማሳደድ ያዘ። በዚሁ ሥራው ላይ እንዳለ በሻለቃ አብዲሣ አጋ ቡድን ስለተያዘ፣ ለፍርድ ቀርቦ የመጣበትን ምክንያት አንድ በአንድ ዘርዝሮ ከአስረዳ በኋላ በጥይት ተደበደበ።

አሥራ ሁለት የጣልያን ጉረምሶች ፊታቸውን ሬንጅ ተቀብተው፤ ሌሎች 8 ደግሞ አውቶማቲክ መሣሪያ ይዘው በድምሩ 20 ሆነው አንድ ኮሚቴ ዘረፉ። ሻለቃ ድርጊቱን ሰምተው በመከታተል ሸጉጥ፣ ቀላል መትረየስ፣ የእጅ ቦምብና 7,240 ጥይት ማረኩ። ከዚህም በስተቀር 98,749 ሊሬ፣ 54 ጆንያ ምግብና 41 በቅሎዎች አገኙ። ይህም ለአርበኝነቱ ሥራ ጠቀመ፤ ወንጀለኞቹንም በሞት ቀጡ።



በዚህ ዓይነት ትንቅንቅ ውስጥ እንዳሉ ፋሽስቶች ድል ሆኑ። ሮም በነፃ አውጭው ጦር ተያዘች። ሻለቃ አብዲሣ አጋ በክብር ሮም ገቡ።

አብዲሣ አጋ ማን ነበር። አብዲሣ በ1916 ዓ.ም ወለጋ፣ በነጆ ቀበሌ ተወለደ። ዕድሜው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ከአንድ የሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብቶ የእንግሊዝኛ ትምህርት ጀመረ። አባቱ በእጃቸው የሰው ሕይወት ስለአለፈባቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ እሱም ወደ አዲስ አበባ መጣ። ወጣቱ አብዲሳ አባቱ በፍርድ ሲገደሉ መራር ሐዘን ደረሰበት።

ከዚያ በኋላ በገነተ አዲስ ከተቋቋመው የጦር ትምህርት ቤት ገባ። በዕድሜው ገና 14 ዓመቱ ስለነበረ ለጥቂት ጊዜ ከአዛገፍ ከኰሎኔል በላይ ጋር ቆይቶ፤ በቦይስካውት ክፍል ተመድቦ አማርኛ የማንበብና የመጻፍ፣ እንደዚሁም እንግሊዝኛና ሰልፍ ተማረ። ልዩ ሥልጠናው ከባድ መሣሪያ መፍታትና መግጠም ነበር። ይህንን ትምህርት እንደ አጠናቀቀ ጣልያን ኢትዮጵያን ወረረች። አብዲሣ አጋም የጥቁር አንበሳ ሠራዊት አባል ሆኖ የአርበኝነት ሥራውን ቀጠለ።[12]

ዘርዓይ ደረስና አብዲሣ አጋ ወደ ጣልያን አገር የሄዱት፣ ዘርዓይ በሹመት/በሥራ ቅጥር፣ አብዲሣ በእሥራት እንጂ በስደት አልነበረም። ታሪካቸውን በዚህ በስደተኞች ምዕራፍ ውስጥ ያስገባሁት፣ የፈፀሙት የጀብዱ ሥራ ከሹመኞችና ከእሥረኞች ይልቅ፣ ወደ ስደተኞች የተቃረበ ሆኖ ስለአገኘሁት ነው።

ሌላኛው፣ ሻለቃ በልሁ የሚባሉት ደግሞ የወሰዱት እርምጃ፣ ለየት ያለ ነው። ተሰድደው ካርቱም ገቡ። የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች የንጉሠ ነገሥቱ የእልፍኝ አስከልካይ መሆናቸውን በማወቅ ጭምር በክብር ተቀበሉአቸው፤ ቅር የሚያሰኝ ነገር አላሳዩአቸውም። ነገር ግን ክብሩና ምቾቱ ለእሳቸው አንዳች አልነበረም። በእውናቸውም፣ በሕልማቸውም የምትታያቸው ኢትዮጵያ ሆነች። ስለዚህ በጋምቤላ በኩል ተመልሰው ጉሬ በመግባት ከራስ እምሩ ጋር ተቀላቀሉ። ለምን ተመልሰው እንደመጡ ቢጠየቁ "...ሰው...መሞቱ አይቀርም። እኔም... በጸሎት ለመኖር ብችልም ...ሞት እንደማይቀርልኝ አውቃለሁ። በጠላት እጅ ብሞትም ደሜ ወደመነጨችበት አፈር ትመለሳለች። ሥጋዬንም...አሞሮች ቢካፈሉት...ተመልሰው የአገሬ አፈር ይሆኑ የለምን?" አሉ። እንደአሉትም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው በጀግንነት ሰጡ።[13]

በጠቅላላው ስደተኞች ለኢትዮጵያ ነፃነት በቂ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ቢሆንም አርበኛውን አይተካከልም። የአርበኛው አስተዋጽኦ ይልቃል። አርበኛው አንዳንድ ጊዜ ከመንዝ ወደ ተጉለት፣ ከዚያም ወደ

ቡልጋ ይዘዋወር፤ እንደዚሁም ከወሎ ወደ ጐንደር፣ ከጐንደር ወደ ጐጃም ይዘዋወር እንጂ፣ እግሩን ለቅቆ አልሄደም። ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወሩም የስደተኝነት ስሜት አልተሰማውም።

እውነታው ይኸ ሆኖ ሳለ፣ የጀግኖች ማኅበር ደንብ በመቅድሙ ላይ ግን የኢትዮጵያ ጀግኖች ለጠላት አንገዛም በማለት መላ ንብረታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው በዱር፣ በገደል እየተሰደዱ ስለ አገራቸው እና ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው ክብር መዋጋታቸውን ይገልጻል።[14] ይህ አባባል የአርበኛውንና የስደተኛውን ስሜት ለማስተሳሰር፣ እንዲሁም የስደተኛውን ገበና ሸፍኖ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሞገስ መልሶ ለመገንባት ሆን ተብሎ በጥበብ የተዘጋጀ ሳይሆን አልቀረም።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 172-201።
2. ሀዲስ አለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 100-139።
3. ሕይወት ኅደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 33-165።
4. ከአቶ አሸቴ ባዩ፣ የኬንያ ስደተኛ የተነገረኝ።
5. ከብርጋዴር ጄነራል ከበደ ዋጋዬ የተነገረኝ።
6. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 69።
7. አክሊሉ ሀብተወልድ ለደርግ የሰጡት ጽሑፍ።
8. ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ገጽ 215-229።
9. Greenfield p.242.
10. New Times and Ethiopian News.
11. ይልማ ማናዬ፣ *ዘርዓይ ደረሰ*፣ ገጽ 16-129።
12. መርሥዔ ኀዘን አበበ፣ *በኢጣልያ በረሃዎች*፣ ገጽ 5-62።
13. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 76-77።
14. ጥንታዊት ኢትዮጵያ አገራዊ የጀግኖች ማኅበር፣ *መሠረታዊ ደንብ* ገጽ 27።




# ምዕራፍ ሰላሣ ዘጠኝ
# የአርበኝነት ስልት

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ንጉሥ የነገሠው፣ ክርስቶስ ሊወለድ 2 ሺህ 482 ዓ.ም ሲቀረው ነው። የንጉሡም ስም ሰብታህ ነበር። ሌሎች ግኝቶች ደግሞ ክርስቶስ ሊወለድ 2800 ሲቀረው በዓባይ ሸለቆና በቀይ ባህር የንግድ ሥራ እንደነበር ይጠቁማሉ።[1] አንድ ሥርወ መንግሥት በአንድ ሀገር ላይ የሚመሠረተው፣ ኅብረተሰቡ ለበርካታ ምዕተ ዓመታት አብሮ ኖሮ በደንብ ከተዋወቀ በኋላ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች የሚጠቁሙት ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ከ5 ሺህ ዓመት ያላነሰ ዘመን እንደኖረች ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ የረጅም ጊዜ ታሪኩ ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሞታል። የዮዲትን /ጉዲትን/ ዘመን ዕልቂት ተቀብሎአል። በግራኝ መሐመድ መሣሪያነት የኦቶማን፤ ማለትም፦ የቱርክ ወረራ፤ ተካሂዶበታል። ነገር ግን በ1928 ዓ.ም እንደ ደረሰበት ዓይነት ጠቅላላ ሽንፈት ደርሶበት አያውቅም። ነገሥታቱም አብረውት ቆመው፣ አብረውት ይወድቃሉ እንጂ፤ አንድም ከዛ ቀደም ጥሎት የሄደ በታሪኩ አያውቅም። ስለዚሁ ሁለመናው እንግዳ ሆነበት። ራሱን እንደተመታ ሰው ዓይነት ጭውታ ደረሰበት። ብዙም ጊዜ ሳይወስድበት ነቃ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የሄዱት የጦርነት ባህል የማያውቁትን ኢትዮጵያውያንን ተራራና ጫካ ተገን አድርገው እየተከላከሉ እንዲቆዩ አዝዘው እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል። መንግሥቱ ወደ ጐሬ ተዛውሮ በአዣዥ ወልደጻድቅ መሪነት ጠላትን እንዲከላከል ተደር጖ ነበር። ኋላም ራስ ስዩም በእንደራሴነት እንዲሠሩ ተጽፎላቸዋል። ነገር ግን በውስጥ መመሪያ እንጂ በይፋ ለሕዝብ አዋጅ አልተነገረም። ስለዚህ የሆነውን ሁሉ ኢትዮጵያዊ በራሱ ጥረት እንደ አደረገው ከመቁጠር በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም። በኢትዮጵያ የተካሄደውን የሚመስል የአርበኝነት ሥራ ከዛ ቀደም በሌላ አገር ተካሄደ የሚያውቅም አይመስልም። ስለዚህ ሁሉም ነገር አዲስ ነበር።

የኢትዮጵያ ጀግኖች አዲስ የጦር መላ ፈጥረው፣ አዲስ የጦር ስልት ቀይሰው፣ ሀገራቸውን ከጥፋት፣ ወገኖቻቸውን ከእልቂትና ከባርነት ለማዳን ተነሣሱ። ለታሪክ ምርምር ከሚጠቅሙት ነገሮች አንዱ እነዚህ ጀግኖች የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ማጥናት ነው። እኛም ከአርበኝነት ሥልቶችና ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሥልቱ በወቅቱ ስም እንኳን አልነበረውም። ጐጃሜ የጠዘጥዝ ጦርነት አለው። ሸዋ ሸፍትነት አለው። የደቢብ ጦር ሀገር መከላከል

አለው። አድመኛ ያሉም ነበሩ። ግን የስም ልዩነት ሳያደናግራቸው ሁሉም አንድ ዓይነት ሥራ ሠሩ። ጠላትን በመግደል፣ ለሀገር መሞት። እየዋለ እያደረ አርበኝነት ተባለ። አርበኝነት ማለት ለሀገር፣ ለወገን ሲሉ ከውጭ ጠላት ጋር መጋደል ማለት ሆነ።

የአርበኝነትን ሥራ ለማንቀሳቀስ ወሣኙ ጉዳይ በዓላማው ሕዝብ እንዲያምንበት ማድረግ ነው። ሕዝብ ያመነበት ነገር ይዋል ይደር እንጂ ውጤት ማስገኙቱ አይቀርም። ስለዚህ የአርበኝነትን ሥራ ያቋቋሙ መሪዎች፣ ሕዝብ ሁኔታውን በትክክል እንዲያውቅ ጥረት አደረጉ። በተለይ በመጀመሪያው ወቅት ከባድ ሆነ። ብዙ ከባባድ ጥያቄዎች ነበሩ።

1ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ፣ ሠራዊቱ ያልቻሉትን እኛ ገበሬዎች እንደምን እንችለዋለን?

2ኛ. በምድር በሰማይ እሳት ለብሶ፣ እሳት ጉርሶ የመጣ ጠላት እንደምን ይቻላል?

3ኛ. ለማን ብለን እንሞታለን? /በተለይ ንጉሠ ነገሥቱን የሚቃወሙ/

4ኛ. መሸፈት ከእልቂት በስተቀር ምን ውጤት ያስገኛል?

5ኛ. ልጆቻችንና ቤተሰቦቻችንን ለማ ትተን እንሸፍት?

6ኛ. ሀገር ያለማን? የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እኔ በነበርኩበት ቡልጋ፣ ሙገሬ ዛላ፣ ሜጢ ከተባለው ቦታ የደረሰውን ሁኔታ እንደማስረጃ አድርጌ ባቀርብ ይሻለኛል። ብዙ ቀን ጥሩንባ እየተነፋ ስብሰባ ተካሄደ። የጉበዝ አለቆች ተመረጡ። ለገበሬ ሀገር ማለት ያለበት አካባቢ ማለት እንደ መሆኑ፣ ዋናው ጉዳይ ቤትን፣ ንብረትን፣ ሀገርን መጠበቅ ሆነ። ሀገር የሚለውን ከዚህ ጠባብ ስሜት አላቅቆ ወደ ኢትዮጵ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ችግር ሆነ። ከሜጢ ቢያልፍ፣ አካባቢው ከሚጠራበት ከሙገሬ ዛላ አላልፍም አለ። ከብዙ ምክር በኋላ ለጠላት ማመን እንዲቀር፣ የቻለ ለኢትዮጵያ እንዲከላከል፣ የማይችል አርፎ እንዲቀመጥ ስምምነት ተደረገ። በዚህም ሃሳብ አቶ ሀብተ ኢየሱስ የተባለ ሰው አልስማማም እንዳለ፣ ሰው እሳት እንዳያስጭረው፣ ከቤቱ ሰው ቢሞት ከቤተክርስቲያን እንዳይቀበር፣ ከንጉሥ መንገድ በስተቀር እሱም ከብቱም እንዳይረግጥ አድማ እንደ ተመታበት፣ እሱም የሰውን ማምረር ሲረዳ በሦስተኛው ቀን ምሕረት ጠይቆ ከሕዝብ ጋር መቆሙን ገልጫለሁ።

ሌላው ከፍተኛ ጉዳይ የመሣሪያ ጉዳይ ሆነ። በሀገሪቱ ውስጥ በቂ መሣሪያ አልነበረም። ከነበረው ጥቂት መሣሪያ አብዛኛው በልዩ ልዩ መንገድ ከጠላት እጅ ገባ። ከጠላት እጅ የገባው መሣሪያ ትክክለኛ ቁጥር



አልታወቀም። የተገኙት ማስረጃዎች ጥንቅር ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረውን ያመለክታል።

ልዩ ልዩ ጠመንጃ..........396,779
ቀላል መትረየስ................1,457
መድፍ...........................222
ሽጉጥ...........................2,428

ይህ ቁጥር በተወሰነ ጊዜ ገቢ የሆነውን እንጂ ሁሉን አያመለክትም። በጠላት እጅ ከገባው መሣሪያ በተለይ ጠመንጃ እጅግ ብዙ ነው። እኔ በበኩሌ ከ700,000 ያንሳል ብዬ አልገምትም።

በዚህ ዓይነት ባዶ እጁን የነበረው አርበኛ፣ ያለው ጠመንጃውን ይዞ ተነሳ። የሌለው ጐራዴ፣ ጩቤ፣ ጦር፣ አንካሴ፣ ዱላ ይዞ በጠላቱ ላይ ተንቀሳቀሰ። መሣሪያ ከጠላት ላይ መቀማት፣ መማረክ ትልቅ ጥበብ ሆነ። አርበኛው በተናጠልና በቡድን እየሆነ ይህን የመሣሪያ መንጠቅ ሥራ በልዩ ልዩ ዘዴ ተያያዘው። በአንድ ጠመንጃ ዙሪያ ሦስትና አራት ሆነው ይሰለፋሉ። አንዱ አነጣጥሮ የጠላት ወታደር ሲጥል ሁለት ሦስቱ ሮጠው መሣሪያውን ይገፍፋሉ። አርበኛ እንደዚህ እያደረገ መሣሪያ አከማቸ። ጠላቱን በገዛ መሣሪያው መልሶ ወጋው። ሳይጠቀምበት የቀረው በታንክና በአይሮፕላን ብቻ ነው።

## ጣልያን ከሕዝብ የነጠቃቸው መሣሪያዎች

| የመሣሪያው ዓይነት | ከአዲስ አበባ[2] | ከሐረርጌ[3] | ከአንኮበር[4] | ከኢትዮጵያ[5] | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ጠመንጃ | 11,353 | 1,420 | 447 | 383,559 | 396,779 |
| መትረየት | 191 | 24 | 4 | 1,238 | 1,457 |
| መድፍ | 53 | | | 169 | 222 |
| ሽጉጥ | 169 | | | 2,259 | 2,428 |

ሌላው ጥያቄ የሥልጠና ጉዳይ ሆነ። መሣሪያውን ማርኮ እንደምን እንደሚጉርስ፣ እንደምን እንደሚተኮስ ባለማወቅ ይቸገራል። ጥቂትም ልምድ ቢኖረው አንድ ጥይት ጉርሶ በሚተኩስ እንደ ውጅግራና መስኮብ ስለመሳሰሉ መሣሪያዎች ነው። ከጣልያን የሚማረከው ምንሽርና አንዳንድ ጊዜም አልቤን ጠመንጃ ነው። እነሱ ደግሞ አጐራረሳቸው ለየብቻ ነው። አልቤን ከቀኝ ወደ ግራ ሲፈለቀቅ፣ ምንሽር ከፊት ወደ ኋላ ይሞለቀቃል።

የመትረየስ አጐራረስና አተኳኮስ ደግሞ የረቀቀ ጥበብ ይጠይቃል። ይህንን ጥበብ ያወቀ ላላወቀ ያስጠናል።

እዚህ እከተማ የምናየው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለገበሬው የጦር ትምህርት መስሎ አይታየውም። እሱ ለጌጥ ለይስሙላ የሚደረግ ዘጥዘጥ ነው። በገበሬ ዘንድ ስሙ እርግጫ ነው። ለገበሬ የጦር ትምህርት ማለት ጥይት በትክክል በፍጥነት ማጉረስ፣ ጠመንጃ አነጣጥሮ መተኮስ ነው። ተኩሶ መሳት ውርደትም ራስንም ለአደጋ ማጋለጥ ነው። ስለዚህ ዓይኑን ያላጣራ ሰው እንዲተኩስ ከዋና ጦርነት ካልሆነ በስተቀር አይፈቀድለትም። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ጠመንጃ ፈትቶ፣ ጠርጐ፣ መልሶ መግጠም ማወቅ ያስፈልጋል። ራስን ከአደጋ የመከላከልና ጠላትን የማጥቃት ሥልት ማወቅ ይጠቅማል። ስለመሣሪያ አጠቃቀም በማስረዳት ረገድ ከጣልያን እየከዱ ከአርበኞች የተቀላቀሉ የኤርትራ ልጆች ረድተዋል። ሌላውን ዘዴ ባንድነት ገብቶ አጥንቶ መመለስ ነው። ዘዴአቸው የተለያየ ነው። እንቅልፍ በወሰደው ጊዜ አንዱ እንዳይመነትፈው ሰይፉን አገጩ ሥር አገዳውን ከጭንና ጭኑ መካከል አድርጐ፣ አፈሙዙን ወደ ቂጡ ዘቅዝቆ፣ ቃታውን ደረቱ ላይ ለጥፎት ይተኛል። ከማያምነው ሰው ጋር አይተኛም። ሲሄድም ሰይፉን ከፊቱ፣ እጁን ከቃታው ላይ አድርጐ ነው። ዝናም ሲመጣ ዘቅዝቆ ያነግተዋል። ወንዝ ሲሻገር ከፍ አድርጐ ይይዘዋል። ለአንድ ቤተሰብ አንድ መሣሪያ በቂ ነው። አያያዝና አጠቃቀሙን ሴቶቹም፣ ወንዶቹም፣ ልጆቹም ጭምር ያጠኑታል።

ዋናው የጦር ሥልት የፈለጉትን ሥራ በመረጡት ጊዜና ቦታ፣ አመች በሆነ ዘዴ መሥራት፤ ሳይቻል ሲቀር መተው ነው። በመደበኛ ጦርና በአርበኝነት ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። በአርበኞች ዘንድ እያንዳንዱ ጦርነት የተለየ ዓላማ አለው። ዓላማውም ተኩስ ከመከፈቱ በፊት ተመክሮ ይወሰናል። ጦርነቱ ያንን የተወሰነውን ዓላማ መምታት በሚያስችል ዓይነት ይካሄዳል። ለባንዳ ጦር መድኃኒት አነጣጥሮ በመተኮስ አለቅየውን መግደል ነው። አለቃው ሲወድቅ ጀሌው ይበተናል። መሣሪያ ለመንጠቅ ከሆነ ቀን መሸት ሲል ከኋላ ያለውን ጥቂት ወታደር ከወገኑ ቆርጦ መጨረስ ነው። ከወጥመድ ለማስገባት ከሆነ አስቀድሞ ቦታ ከያዙ በኋላ ጥቂት ሰዎች እየተኩሱ እንዲሸሹ ማድረግ ነው። ለማጥቃት ከሆነ ምቹ ቦታ ይዞ በርትቶ መዋጋት ነው። ስንቅና ጥይት ለመቀማት ከሆነ አጋሰሶቹን፣ አህዮቹን በጥይት መደብደብ ነው። ኃይሉን ማስጨረስ ከተፈለገ ከምሽቱ ወደ አንድ ሰዓት ላይ ዙሪያውን ከቦ ጥቂት ጥይት መተኮስ ነው። ሌሊቱን በሙሉ መድፍና መትረየሱን ሲያዥጐደጉደው ያድራል። አንድ መንገድ ይዞ እንዲሄድ



ለማስገደድ ከመንገድ ወጣ ያለውን በጥይት መዘንጠፍ ነው። ይህ ዘዴ የቤት ቃጠሎን ለመግታትና ሰላማዊ ሰዎችን ከእልቂት ለማዳን ብዙ ጊዜ ረድቶአል።

የሠራዊቱ የልብ አንድነት ለጦርነት አስፈላጊ ነው። በአንድ የጦር ግንባር የሚሠለፉ ሰዎች እርስበርሳቸው የሚተማመኑ መሆን አለባቸው። ወንድሙን ከጦር ላይ ትቶ የሚሄድ ሰው እንደ ከሀዲ ይቆጠራል፤ አቀብሎ ሸሸ ይባላል። ዳግመኛ አብሮት የሚሰለፍ አያገኝም። ጦርነት ከመጀመሩ በፊት የተጣሉ መታረቅ አለባቸው። ካልታረቁ ከጦርነት መግባት አይገባቸውም። ወገን ወገኑን እየጣለ በመሸሹ ብዙ ጉዳት ደርሶአል። ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ከሞት የደረሱት በዚህ ዓይነት ነው የሚል ከባድ ሀሜት አለ።

ቦታ የመምረጥ ችሎታ ታላቅ ነገር ነው። ሕዝብ እንዳይጐዳ ጦርነት የሚደረገው በመንደር ላይ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሥርጥ ይዞ መዋጋት፣ አንጥፎ ጠላት ከወጥመድ እስኪገባ መጠበቅ ጥበብ ነው። ለጠላት ምቹ ከሆነ ቦታ ላይ ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር መዋጋቱ ከንቱ ነው። በደጃዝማች ፍቅረ ማርያም የተመራው አርበኛ የተጠቃው ተስማሚ ቦታ ባለመምረጥ ነው። ደጃዝማቹ በማይጨውም የተሸነፍነው እንዲሁ እየተባለ ነው በማለት ምቹ ጊዜና ቦታ እንዲፈለግ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሳይቀበሉት ቀሩ።[6] የከሰምን አፋፍ ለቅቆ በጭለማ በመጓዝ ራምቡቲ ሜዳ ወጣ። ሃሳቡ በጠላት ላይ አደጋ ለመጣል ነበር። የጭለማና የጭቃው ጉዞ አዘገየው፣ አደከመው። ለጥቃት ተጋለጠ፤ አለቀ።

ለጦርነት አንዱ ዘዴ ሠራዊቱን መበተን ነው። ከመበተኛዎቹ መንገዶች አንዱ አለቅየውን መግደል ነው። ነገር ግን የጣልያን ጦር በዚህ ሥልት እምብዛም አይጠቃም። አለቅየው ሲወድቅ ምክትሉ በቦታው ተተክቶ የአዛዥነቱን ሥራ ይይዛል። ቢሆንም ጦሩ ይላላል።

የአርበኝነት ሥራ፣ ማዕከላዊ እዝ አይችልም። አስተባባሪ እንጂ አዛዥን አይቀበልም። ማዕከላዊ እዝ ድንግርግር ያበዛል። ከዚህ ይልቅ አርበኛው በቡድን በቡድን እየሆነ እንደተመቸው መዋጋትን ይመርጣል። አያድርስ እንጂ አንዱ ቡድን ቢያልቅ፣ ሌላው ቡድን ይድናል። በሌላው በኩል ደግሞ በቡድን ተከፋፍሎ መዋጋት ጠላትን ለመበተን ያግዛል። አንዱ ቢጠቃ ሌላው ያጠቃል። አርበኞችን ለድል ከአበቁአቸው ሥልቶች አንዱ ሁሉም በየፊናው መሥራቱ ነው።

ጠላትን አጠቁበት ቦታ መቀመጥ ደግ አይደለም። የተገኘውን ምርኮ ሰብስቦ ወደ ሌላ ቦታ ዘወር ማለት ነው። ያለዚያ ጠላት አጸፋዊ የማጥቃት እርምጃ ሊወስድ ይችላል። ጦርነት ብተደረገበት ቦታ ላለውም

ሕዝብ የእፎይታ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ለአርበኛው ቀለብ ለማግኘትና እንዲያገግም ለማድረግ ይረዳል። ከድል በኋላ መጀነን አያስፈልግም። ድምጥን አጥፍቶ መቀመጥ እንጂ። መግደርደር የሚያስፈልገው በተሸነፉ እንጂ ባሸነፉ ጊዜ አይደለም። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያውያን ባህልና ስሜት ጋር ሥምረት የለውም። ጀብዱ የሠራ ሰው መሸለል መፎከር ይወዳል። አይጠቅመውም። ለተከታታይ ጥቃት ያጋልጠዋል።

ጠላትን ማጥቃት ከተቻለ ማጥቃት፣ ከአልተቻለ መሸሽ ነው። ማመንታት አይጠቅምም። ከመጠን ካላለፈ በስተቀር በአርበኝነት ሥራ መሸሽ ነውር አይደለም። ከበዛ ግን ግምትን ዝቅ አድርጎ፣ ጠላትን ያደነድናል፤ ወገንም ይንቃል። የሸሸ አርበኛ በሌላ ጊዜ ጀብዱ ሠርቶ ክብሩን መልሶ ማደስ ነበረበት። በአንፃሩ ደግሞ ጀብደኝነት ከጥፋት ያደርሳል። በጀብድነት አሠራር ብዙዎች አደጋ ደርሶባቸዋል። ከጉራጌ አገር አርበኞች የደጃዝማች ገበረማርያምንና የሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያን አቋም ማመዛዘን ለዚህ አባባል የበለጠ ግንዛቤ ይሰጣል።

የጠላት ሃሳብና ዓላማ፣ እንቅስቃሴ አስቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ነው። የመሪውን ባሕርይ፣ ዓላማና ዕቅድ እንዲሁም የጦሩን ብዛትና የያዘውን መሣሪያ ማወቅ ጥሩ ነው። መሪው የራሱ የሆነ ዓላማ ከአለው አደገኛ ነው። ካልወደቀ በስተቀር ያንን ግቡን ሳይመታ አይመለስምና ያንኑ በቶሎ ማስተናገድ ይበጃል። ነገር ግን የሚንቀሳቀሰው ትዕዛዝ ለመፈፀም ያህል ከሆነ ራስን ከመንገዱ ማግለል እንጂ መተናነቅ አያስፈልግም። እፊት እፊቱ ጥቂት ሰዎች እየተኮሱ እንዲሸሹ ማድረግ፣ ድል አድርጌ መጣሁ ለማለት ይመቸዋል። በአንፃሩ ደግሞ በይበልጥ ማጥቃት ይህንን መሳዩን ነው የሚሉ አሉ፤ ግን ሲያጠቁት መከላከሉ አይቀርምና፣ ብርታት ይጠይቃል።

አገርን ከመጠበቅ አኳያ መተላለፊያ በሮችን ሁሌም መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ የታወቁ በሮች አሉአት። በጉንደር እንደ ሊማሊሞና ጣራ ገዳም፣ በትግሬ እንደ አምባለጌ፣ በወሎ እንደ አላማጣና መቅደላ፣ በሸዋ እንደ ጣርማ በር፣ በሐረርጌ እንደ ካራማራ፣ በባሌ እንደ ሰብሰቤ ዋሻ የመሳሰሉ በሮች አሏት። በ1928ቱ ጦርነት በተከፈተ ጊዜ በኢትዮጵያ ጦር ላይ ብዙ ጉዳት የደረሰው እነዚህ በሮች ላይ ባለመዋጋት ነው። በኋላ አርበኛው በአካባቢው ያሉ ሸንተረሮችን በደንብ ተጠቅሞባቸዋል። የማውቀውን ለመጥቀስ ያህል፡- እንደ መገዘዝ ያሉ ተራሮች የጠላትን እንቅስቃሴ በመመልከቻነት፣ እንደ ሙገሬ ዛላ ያሉ ደኖች በመደበቂያነት፣ እንደ ከሰም ያሉ ወንዞች የጠላትን ጉዞ በመግታት፣ እንደ ፍቅሬ ግንብ ያሉት ገደሎች በመከላከያነት አገልግለዋል።



በአርበኝነት ዘመን ካየሁትና ከተረዳሁት፣ የተኩስ አከፋፈትን መቆጣጠር ጠቃሚ መሆኑን ነው። ባልተገባ ጊዜና ቦታ ተኩስ መክፈት፣ ራስን ለጥቃት ማጋለጥ ነው። በማይጨው ጦርነት፣ ውድቀት ካስከተሉት ነገሮች አንዱ የተኩስ አከፋፈቱ ትክክል ካለመሆኑ የተነሣ መሆኑን አርበኛው ዘወትር በምሬት ሲያስታውስ ኖሯል። ተኩስ በጠላት ከተከፈተ፣ የመከላከል ሥልት መከተል ይቀላል። ለማጥቃት መሞከር ውጤት ላያስገኝ ይችላል። የመረዳዳት ጉዳይ ወሣኝ ነው። እርስበርሳቸው ከማይስማሙ በአንደኛው ላይ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ሌላው እየደረሰ ያዳነበት ጊዜ በአርበኝነት ሥራ ውስጥ ብዙ ነው።

ጠላትን የማጥቃት ዘዴ ማወቅ ጠቃሚ ነው። አንዱ የሚጠቃበት ዘዴ ሌላ ከሚያጠቃበት የተለየ ነው። እንደተኛ በመጥረቢያ አንገቱን የቀረጠፉ አሉ። ከዛፍ ላይ ተንጠልጥለው ለሚያጠቁ አሞራው /ራስ/ ውብነህ ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሰላማዊ ሰው የሰለበውን የጠላታ ወታደር መልሰው ስላሰለቡ ራያው /ደጃዝማች/ ከፈለው ተባሉ። በዱላ ደብድበው የገደሉ፣ ድንጋይ ወርውረው የፈነከቱ ብዙ ናቸው። ከጠላቱ ጋር በአንድ ጊዜ ተኩሶ ጠላቱ ሲሞት እሱ ወድቆ የዳነ አለ። ጠላቶቻቸው ነቅሎ የወረወረባቸውን የእጅ ቦምብ ቀልበው መልሶ በመወርወር የገደሉ በርካታ ናቸው። በዚህ ዓይነት እሱም፣ ጠላቱም ሰባት፣ ሰባት ጊዜ ተወራውረው፣ በሰባተኛው የገደለው አርበኛ በታሪክ ተመዝግቦአል። ተአምር ነው። ነገር ግን መጤን ያለበት ቁም ነገር ውጤት የሚገኘው እያንዳንዱ በራሱ ዘዴ ሲሠራ መሆኑ ነው።

በአንፃሩ በኅብረት መሥራት አስፈላጊ ነው። በተናጠል ብዙ ጠላትን ማጥቃት አይቻልም። ጠላት ብዙ መድፍ ነበረው፣ ከሩቅ እያሸጋገረ ይደበድባል። ስለዚህ አርበኞች ጠላታቸውን ለማጥቃት በቀረቤታ መዋጋት አለባቸው። በቀረቤታ ለሚደረግ ጦርነት ደግሞ ያሉት መትረየሶች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ለጥይት ቁጠባ ሲባል እነሱም የሚሠራባቸው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው። በሮምታ፣ በነፍስ ወከፍ መሣሪያ ተኩስ በመተኮስ፣ መትረየስ የሚሠራውን ሥራ መሥራት እንደሚቻል በብዙ የጦር ሜዳ ተረጋግጦአል።

ብዙ ጊዜ አያጋጥምም እንጂ፣ የጠላትን ወታደር እርስበርሱ ማዋጋት አስደሳች ውጤት ያስገኛል። በሁለት ወገን ከሚንቀሳቀስ የጠላት ጦር መካከል ገብቶ፣ ግራና ቀኝ እየተኮሱ መግደልና ጦርነቱ ሲጋጋም ተሾልኮ የመውጣትን ጥበብ ማወቅ ያስፈልጋል። የመሣሪያውም ዓይነት ጠላት ከያዘው የተለየ መሆን አለበት።

ከጠላት ጥበብ ራስን ማዳን ከጥበብ የበለጠ ጥበብ ነው። ከጠላት የተማረከ እህል ለውሻ መስጠትና ውጤቱ እስኪታወቅ መጠበቅ ያስፈልጋል። ጠላት የለቀቀውን ቦታ ተሽቀዳድሞ መያዝ አደገኛ ነው። ከጠላት የተላከ ልብስም አደጋ አስከትሎአል። በእርቅ ጊዜ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከጣልያን አንድ ሙሉ ገበርዲን ልብስ ተላከላቸው። ወደዱትና ለበሱት። ከጥቂት ቀን በኋላ ሁለቱም እጆቻቸው ሽባ ሆነ። እንኳን መሣሪያ ሊጨብጡ፣ ቆርሰው መጉረስ አቃታቸው። ከሦስት ወር በኋላ በሙገሬ ዛላ አማኑኤል ጠበል ዳኑ። ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱም ከአዲስ አበባ አዲስ የክብር ልብስ ተላከላቸው። የ1931 ዓ.ምን የመስቀል በዓል እሱን ለብሰው አከበሩ። ነገር ግን መስከረም 17 ቀን ተቀበሩ።

በሽሽት ጊዜ ዱካን ማጥፋት፣ ከጠላት ክትትል ያድናል። አርበኞች በዚህ ዘዴ ተጠቅመውበታል። አንዱ ዘዴ ጥቂት ሰዎች እየተታኮሱ ጠላት ወደሚሄድበት አቅጣጫ እንዲሸሹና ዋናው ሠራዊት ወደ ጀርባ እንዲዞር ማድረግ ነው። ቦታው አሸዋማ ከሆነ፣ በኋላ ያለው ሰው ጨሬቅ እንዲጐትት ማድረግም ይረዳል። ሣርና ሰንበሌጥ የሆነም እንደሆነ የተኛውን እየመለሱ ማቆም ይመረጣል። አንድ መሥመር ይዞ ከወንዝ መግባት፤ ውሃ ለውሃ ጥቂት ሄዶ ወደ ኋላ በሌላ መንገድ መመለስም ረድቶአል። ዋናው ዘዴ ግን አብሮ አለመጓዝ፣ መበተን ነው።

የአርበኝነት ሥልት በአንድ ጊዜ ጠላትን ማሸነፍ አይደለም፤ ይልቁንም ጊዜ በመውሰድና ጦርነቱን በማርዘም የጠላትን አቅም አሳጥቶና አስመርሮ ማባረር ነው። ለዚህም መሪዎቹን መግደል፣ ረዳቶቹንና ሰባቂዎቹን ማውደም፣ የጦር ሥልቱን ማዘበራረቅ፣ ሠራዊቱን በተለይም ባንዳውን መበተን፣ የሕዝብ አመኔታ ማሳጣት ያስፈልጋል። ስለዚህ ልበ ሰፊነት፣ ቆራጥነት፣ ትዕግስት ያስፈልጋል። ብዙ ሰው እልህ ይይዘውና ምንዳቤው፣ መከራው ያስመርረውና ራሱን ፈጥኖ አደጋ ላይ ይጥላል። ብዙ አርበኞች በዚህ ዓይነት ወድቀዋል። ፈተናው ብዙ ነው። ሁኔታው አስመራሪ ነው። ከወዳጅ ዘመድ ያራርቃል፤ ከሰው ይለያል። ወደ አውሬነትም ያቃርባል። ዕለት ዕለት መግደልና መሞትን በማሰላሰል ለእብደት ያዳርሳል። ረሀብ፣ ጥማት፣ እርዛት፣ የመጠለያ እጦት፣ በመዓልትና በሌሊት መንገላታት የዘወትር ጉዳዮች ናቸው። ተስፋ ሳይቆርጡ ሁሉን ችሎ መቀጠል ያስፈልጋል።

የአርበኝነት ሥራ ከተካሄደባቸው ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው። ለወደፊትም ሊጠቅሙ ስለሚችሉ ሊጤኑ ይገባቸዋል። ችግር ዳግመኛ አይደርስም ብሎ ማሰብ መታለል ነው። እነዚህ ስልቶች ያረጁ ያፈጁ ናቸው ብሎ መገመት ሞኝነት ነው። በሌላ



በኩል ደግሞ እነዚህ ሥልቶች በሁሉም ቦታ፣ ሁልጊዜ ተሠርቶባቸዋል ማለት አይደለም። ሌሎች ሥልቶች አልነበሩም ማለትም አይደለም። ከእነዚህ የተሻሉ ሌሎች ሥልቶች አይቻለው። እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ሥልቶች በመሥራት መሆኑን ለመግለጽ ያህል ነው።

በሰሜንና በምሥራቅ የተካሄዱትን የዋናዎቹን ጦርነቶች ሥልት መመልከት ደግ ነው። ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ለመከላከል የበኩላቸውን፣ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። ያልተደረገ ነገር ቢኖር ሳይቻል የቀረ ብቻ ነው። ነገር ግን የጦር ሥልትን በተመለከተ አንዳንድ ጉዳዮችን ማንሳትና መወያየት ግንዛቤን ለማዳበር ይረዳል። ወረራው ገሀድ በሆነ መንገድ የተጀመረው መስከረም 23 ነው፤ ኢትዮጵያ ድል የሆነችው መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ነው። እንደጨዋታ ሥርዓት ብናየው ከመስከረም 23 ቀን በፊት የነበረው እንደ እንቁርቁሶ፤ ከመጋቢት 22 ቀን በኋላ ያለው እንደ መንፈራገጥ የሚቆጠር ይሆናል።

በዋና ዋናዎቹ ጦርነቶች ላይ አንዳንድ ስህተቶች ተፈጽመዋል። በየትኛውም ሥልት ቢሠራ በጦርነቱ ኢትዮጵያ ታሸነፍ ነበር አይባልም። ነገር ግን በተሻለ ሥልት ቢሠራ ኖሮ የተሻለ ውጤት ይገኝ ነበር። የኢትዮጵያን አወዳደቅ የተፋጠነው፣ የጣልያን ኃይል ጠንካራ መሆኑ ብቻ አልነበረም። በዘዴ አለመሥራትና በሥልት አለመጠቀም ጭምር ነበር። እነዚህንም በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ከስሕተቶቹ አንዱ ጦር በማዕከላዊ ዕዝ ተቀፍድዶ መያዙ ነበር። ከሺህ አምስት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ተራርቀው ባሉ ሁለት ታላላቅ የጦር ግንባሮች አገሪቱ ተቀስፋ ሳለ፣ በዛን ጊዜ፣ ሁሉን በአንድ ዕዝ ለመምራት መሞከር ትክክል አልነበረም። ሌላው የአቤቶ ኢያሱ ሞትና መርዶ በጦርነቱ ዋዜማ መፈጸሙ፣ የተረጋጋው የሕዝብ ስሜት እንደገና በመበጥበጡ ታላቅ ጉዳት አድርሶአል። በወቅቱ ከአንድ መቶ የማይበልጡ ካሚዮኖች ለሚንቀሳቀሱባት ኢትዮጵያ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ መሥራት አስፈላጊ አልነበረም። በአንድ በኩል አላስፈላጊ ወጭ አስከተለ። እንዲቆፍር የተገደደውን ሕዝብ አስመረረ። ውጤቱ፣ የጣልያንን አገባብ ማፋጠን ሆነ። ሌላው ጉልህ ስሕተት፦ አፄ ምኒልክ አስመጥተው ኮረማሽ ያስቀመጡት መሣሪያ ለጦርነቱ እንዲሠራበት አለመደረጉ ነበር። በትዕዛዝ ረገድ፦ መጋቢት 21 ቀን ሰኞ ጦርነት እንዲደረግ ታዝዞ ጦሩ ከሠልፉ ከገባ በኋላ ወደ መጋቢት 22 ቀን ማክሰኞ እንዲዛወር መደረጉ፣ ጦሩን ለሙሉ ቀን የአይሮፕላን ድብደባ አጋለጠው። ማለትም፦ ለከንቱ እልቂት ዳረገው። ንጉሠ ነገሥቱ ለእቴጌይቱ ያስተላለፉት ደብዳቤ የጦርነቱን ምሥጢር ለጠላት አሳልፎ ሰጠ። ሠመልእክቱ መተላለፉ ራሱ

ትክክል አልነበረም። በዘመናዊ የጦር ሥልትም፣ በጥንታዊ ባህልም ቦታ የለውም። ከዚሁ ጋር ሲነሳ የሚገባው፣ የጦር በሮች አስቀድሞውኑ አልተጠበቁም። በሰሜን አምባላጌ፣ በምሥራቅ ካራማራ፤ በነፃ ለጠላት ተለቀቁ።

የጦርነቱ ምክር የሚመከረውና ዕቅድ የሚነደፈው በውጭ አገር ሰዎች መሆኑ ታላቅ ድክመት ነበር። ታላቅ ጉዳትም አድርሶአል። ሌላው ለጦሩ ስንቅ አልቀረበለትም። መሣሪያውም በዋሻ እንደታጨቀ መቅረቱን ብዙዎች በምሬት ያስታውሳሉ። በጥቃቅን ሽንገላ ከጠላት ጐን በመቆም፣ ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ብዙዎቹ የክህደት ሥራ አካሄዱ። በምሥራቅ ጦር ግንባር ነፋሻውን ደጋማ አገር መከላከል ሲገባ ጦሩ ዶሎና ቆራሄ ገብቶ እንዲያልቅ መደረጉ ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባውም።

ደግ ሥራ የተሠራው በደፕሎማቲክ ረገድ ነው ቢባልም፣ እሱም እንከን አላጣውም። ችግሩን ለዓለም ማህበር ማቅረብ፣ መከራከር፣ ዕርዳታ መጠየቅ ላይ ብቻ መመካት ተገቢ አልነበረም። ሌላው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ ከጣልያን ጋር ያካሄዱት የነበረው የምሥጢር ንግግር ነበር። ምንም ንጉሠ ነገሥቱ የተደረገባቸውን ተፅዕኖ በመቋቋም ኢትዮጵያን ከውርደት ቢያድኑ፤ ንግግሩ መደረጉ ራሱ በታሪክ ፊት አሳፋሪ ጉዳይ እንደሆነ ይኖራል። ሌላው ጉድለት ደግሞ ጣልያን ሲባረር አርበኞች አዲስ አበባ እንዳይገቡ መታገዳቸው ነው። በጣልያኖች ላይ ጉዳት ያደርሱ ነበር ከሚለው ከንቱ ወሬ ይልቅ፤ የከተማይቱን ጸጥታ በመርዳት ጠብቀው ሊያቆዩ ይችሉ ነበር ማለቱ የበለጠ እውነትነት አለው። የሚያሳዝና ደግሞ ኢትዮጵያ ፈጥና በጦርነት የወደቀችው በእነዚህ ምክንያቶች መሆኑ ነው።

<u>**ማጣቀሻ ፅሑፎች**</u>

1. ላጲሶ ጌ. ድሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ ገጽ 21።
2. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
3. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 154።
4. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 151። ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ።
5. Sabacchii, *Ethiopia under Mussolini,* p.180.
6. Greenfield, *Ethiopia*, p.238.



# ምዕራፍ አርባ
# የአርበኞች የርስበርስ ግንኙነት

የአርበኞች ዓላማ አንድ ነበር፤ ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት። የዚህ ዓላማ ሌላው አማራጭ ሞት፣ ቅኝ መገዛት ነው። በዚህ ጉዳይ የወላወለ ከአርበኛ አልተቆጠረም። በዚህ ዓላማ ጸንተው የዘለቁ እጅግ ብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት በትግል የሞቱት 78,500 እንደነበሩ ገምቶአል። ሳያንስ አልቀረም። ነገር ግን ሌላ ማስረጃ የለምና፣ በዚሁ መጽናቱ ይሻላል።

በዚህ ዓላማ ጸንተው የአምስቱን ዓመት ተጋድሎ የፈጸሙት 20,000 ይሆን ይሆናል። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲረዳ፣ ቃላቸውን ሲሰማ ከጣልያን እየከዳ የገባ ነው። የራሱን ጉዳይ ያካሄደ እንጂ ለሀገር እንደሞተ ለመቁጠር ያዳግታል። ቢሆንም እስከ መጨረሻይቱ የጣልያን ሕቅታ፤ ማለትም የተመደበበት ጦር እስኪፈርስ ሽንጡን ገትሮ ወገኑን ከተዋጋው በብዙ እጅ ይሻላል።

የሞተው 78,500 ከነበረና በሕይወት ቀን የወጣው 20,000 ከሆነ ወደ 100,000 ያህል አርበኛ ተንቀሳቅሶ ነበር ማለት ነው። ይህንን ያህል ሰው በአቀፈ ሠራዊት ውስጥ አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማጋጠሙ አይቀርም። አፍ ከእጅ ይጣላል እንዲሉ፣ በአርበኞች መካከልም እንደዚሁ ሆኗል። መስማማትና መጣላት፣ መረዳዳትና መጋጨት፤ በልዩ ልዩ መልክ፣ በልዩ ልዩ ጊዜና ቦታ ተከስተዋል።

መረዳዳቱ መልካም ነበር። አንዱ በተጠቃ ጊዜ ሌላው ገስግሶ ይደርስለታል። በዚህ ዓይነት የጦር ጓደኞቻቸውን ያዳኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ነገር ግን አደጋው ከአለፈ እምብዛም አይታሰብም፤ ይዘነጋል። ቢሆንም አርበኞች እርስበርሳቸው ይረዳዱ እንደነበረ፣ ከሚጋጩበት ጊዜ ይልቅ፣ የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ጊዜ ይበዛ እንደነበረ እሙን ነው።

ምንም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ክብርና ለወገናቸው ነፃነት መሥዋዕት ለማድረግ ቢቆሙ፤ ምንም የግል ጉዳያቸውን፣ ሕልውናቸውን ጭምር ወደ ጐን ቢተው፤ አርበኞች አልፎ አልፎ እርስ በርሳቸው መጋጨታቸው አልቀረም። ሥጋ ለባስያን ስለሆኑ የሚያጋጩአቸውም ነገሮች ነበሩ። በሴት ከንፈር፣ በልጅ ነገር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመሬት ድንበር ተጋጭተዋል። የጉርስና የልብስ ጉዳይ ያጋጫል። የክብርና የሥልጣን ውድድር፣ የመሣሪያ ቅብብሎሽ ያጣላል። አንድ አርበኛ የቀድሞ አለቃውን ትቶ ከሌላው ጋር ሲሰለፍ ሁለቱን አለቆች ያቃቅራል። የክልል ጉዳይም እንዲሁ፤ ለአንዱ መጥን ከሚወጣበት ቤት፣ ሌላው የጠየቀ እንደሆነ ያቃቅራል። የክፍለ አገር ክልልም እንደዚሁ ነው። አንዱ በደሙ ያስከበረውን አካባቢ፣ አገር ሌላው ልንካ ቢል አይሆንም። ነፃረ ሠሪዎችና አሰሪዎችም